አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና የፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች

በ

ፀዳለ ታደሰ

ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ጥር 2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና የፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ እምነቶች

በ

ፀዳለ ታደሰ

አማካሪ:- ዶ/ር አህመድ ሀሰን

ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ ፅሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ጥር 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**


ምስጋና ....................................................................................................i

ሙዳዩ ቃላት .............................................................................................ii

አጠቃሎ.......................................................................................................v

1. መግቢያ ..................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ .............................................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...............................................................................1

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች .......................................................................................2

1.4 በጥናቱ የሚመለሱ የምርምር ጥያቄዎች ...................................................................3

1.5 የጥናቱ ዘዴ .............................................................................................3

1.5.1 የመረጃ ምንጭ .........................................................................................3

1.5.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..........................................................................5

1.5.3 የመረጃ አተናተን ......................................................................................7

1.6 የጥናቱ ወሰን ...........................................................................................7

1.7 የጥናቱ ውሱንነት ........................................................................................7

1.8 የጥናቱ አስፈላጊነት ......................................................................................8

1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች......................................................................9

2 አካባቢያዊ ዳራ .............................................................................................10

2.1 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ.....................................................................................10

2.2 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ..........................................................................................11

2.3 አስተዳደራዊ ሁኔታ .........................................................................................11

2.4 ቋንቋና ሀይማኖት ..........................................................................................13

3. ክለሳ ድርሳናት...............................................................................................14

3.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት..........................................................................................14

3.1.1 የሀገረሰባዊ ዕምነት ምንነት.................................................................................14

3.1.2 የክበራ ምንነት ............................................................................................16

3.1.3 የክበራ መገለጫዎች .........................................................................................18

3.1.4 የክበራ አይነቶች.............................................................................................19

3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ......................................................................................21

4. ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 27
4.1 በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና ስርዓተ ክዋኔያቸው ........ 27
4.1.1 ጫት መቀቀል ........ 27
4.1.2 ጭዳ ........ 33
4.1.3 አድባር ........ 36
4.1.4 ቦረንትቻ ........ 43
4.1.5 አቴቴ (ፈጫሳ) ........ 45
4.2 ለሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ያለው አመለካከት በቀይት ንዑስ ወረዳ ........ 50
4.2..1 ሀይማኖታዊ ዕይታ ........ 50
4.2..2 ማህበረሰባዊ ዕይታ ........ 53
5. ማጠቃለያ ........ 56
ዋቢ ፅሁፎች ........ 59
አባሪዎች ........ ሀ

## ምስጋና

ከአምላኬ በመቀጠል ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ አቅጣጫዎችን በማሳየትና ስህተቶቼን በማቃናት እገዛቸው ሳልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር አህመድ ሀሰን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም በጥናት ስራዬ ውስጥ ከእኔ ባልተናነሰ መልኩ አብረውኝ ለደከሙት ሁሉ በተለይም ለአቶ ዘውዴ አሰፋ ከነቤተሰባቸው እና ለእናቴ እንዲሁም መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ እና በጥናቱ ውስጥ አሻራቸውን ላሳረፉ ሁሉ ጥልቅና የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**ሙዳዬ ቃላት**

ከዚህ ስር ያሰፈርኳቸው ቃላት በዚህ ጥናት ወረቀት ውስጥ የተካተቱና ለአንባቢ እንግዳ ይሆናሉ ብዬ ያሰብኳቸው ናቸው፡፡ ለቃላቱ ፍቺ የሰጠሁትም በዚሁ ወረቀት ውስጥ ባላቸው አገባብ መሰረት ነው፡፡

መቅሰፍት፡- በአምላክ ቁጣ ተፈጥሮ ላይ የሚደርስ ክፉ ነገር

ምድር ቤት፡- ከላዩ ላይ አንድ ፎቅ ያለው ቤት

ልዕለ ሀያል ተፈጥሮ፡- በተፈጥሮው ከሁሉም ተፈጥሯዊ ነገሮች የበለጠ ሀይል ያለው አካል

ሪሚጦ፡- ከገብስ ዱቄት የሚዘጋጁ በሎሚ ቅርፅና መጠን ተድቦልቡለውና ረመጥ ውስጥ ተጠብሰው ለመናፍስት የሚቀርቡ የግብር አይነቶች ሲሆን በቁጥር ሶስት ናቸው፡፡

ስለት፡- አንድን ችግር በተመለከተ ለልዕለ ሀያል ተፈጥሮ እንደዚህ ከተደረገልኝ እኔም እንደዚህ አደርጋለሁ ብሎ ቃል መግባት

ቆጥ፡- ለዶሮ ማደሪያ፣ ለእንጨትና ለብቅል መስቀያ የሚያገለግል ግድግዳ ላይ የሚሰራ የእንጨት ርብራብ

በረት፡- የከብቶች ማደሪያ ቤት

ቢያሸልበው (ማሸለብ)፡- ለአጭር ጊዜ የሚተኛ እንቅልፍ

ባለጡት ማሰሮ፡- በመያዢያ ጆሮው ትይዩ የጡት ጫፍ መሰል ጉብታዎች ያሉትና ለመጣጅያነት የሚያገለግል የሸክላ ቁስ

ባልጩት፡- በውሃማና በአሸዋማ አካባቢዎች የሚገኝ የተለያዩ ቀለሞች ያሉትና የሚያብረቀርቅ የድንጋይ አይነት

ተረክ፡- በቃል እየተነገሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ዝርው ቃላዊ ጉዳዮች

ትዕምርት፡- ለአንድ ነገር በወካይነት የቆመ ቁስ፣ ድርጊት፣ ቁጥር፣ ቀለም፣ ቅርፅ ወዘተ

አምልኮ፡- ለሚያምኑበት ልዕለ ሀያል ተፈጥሮ ልቦናን ማስገዛትና በመንፈስ ለመገኛኘት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ

አውዛ፡- ጫት ከተቀቀለ በኋላ ለመጠጥነት የሚውለው ፈሳሽ

እርኩሰት፡- የሰዎች ከመልካም ነገር መራቅ ወይም በሀይማኖቱ ከቅዱስነት በተቃራኒው ለቆሙ ነገሮች መገዛት

ከበራ፡- የተለያየ መነሻ ኖሯቸው ወቅት ጠብቀው በተለየ ዝግጅት የሚከበሩ

ክንብንብ፡- ነጠላ ወይም ጋቢ እስከ ጭንቅላት ድረስ ሲለበስ ጭንቅላት የሚያርፈው ክፍል ክንብንብ ይባላል፡፡

ክዋኔ፡- በከበራው ወቅት የሚደረግ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ

ወንፊት፡- ከብረትና ከሸቦ ወይም ስንደዶ ከሚባል ተክል የሚዘጋጅና ዱቄትን ካልደቀቁ ነገሮች ለመለየት የሚያግዝ ቁስ

ውቃቢ፡- የተለያዩ  የመናፍስት ወይም መንፈስ በሰዎች ላይ ማደር ሲሆን በላያቸው ላይ መንፈስ አድሮ እንዲደረግላቸው ስለሚፈልጉት ጉዳይ ከመናፍስቱ ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ባለውቃቢ ይባላሉ፡፡

ውድማ፡- በገጠሩ አካባቢ በብዛት ከቤት በስተጀርባ የሚሰራና ለእህል መውቂያ የሚያገለግል አነስተኛ ሜዳ

ዘረንጋ፡- ከእንጨትና ከጭቃ ግድግዳ ላይ የሚሰራ መደርደሪያ

የምፅዓት ጊዜ፡- በኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት እግዚአብሄር ወደ ምድር መጥቶ ፃድቃኖችንና ሀጥኖችን (ሀጢያተኞችን) ይለይበታል ተብሎ የሚታመን ጊዜ፤ በተለምዶ ስምንተኛው ሺህ እየተባለ ይጠራል፡፡

ያልተኮላሸ (መኮላሸት)፡- እንዳይራባ ያልተደረገ

ደብተራ፡- በኦርቶዶክስ ሀይማኖት የሚሰጥ ሀይማኖታዊ ስልጣን ነው፡፡ አንድ መሪጌታ መሪጌትነቱን ሲያገኝ አብራው የነበረችውን ሚስቱን ከፈታ ወይም ከሞተችበት ህጉን አፈረሰ ይባላል፡፡ ህጉን ያፈረሰ መሪጌታ ደግሞ ደብተራ ሲባል በተለያዩ የጥንቆላ መፅሃፍትበመታገዝ የሰዎችን እጣ ፈንታ የመተንበይና የመናፍስቱን ፍላጎት የመረዳት ችሎታ ያለው ሰው

ደንቃራ፡- ለመናፍስቱ በሚሰጥ ግብር ምክንያት የሰዎች ወይም የእንስሳት በሽተኛ መሆን

ድብዳብ፡- አደንብ ከደረቀና ከታሸ በኂላ ለመቀመጫነት የሚያገለግል የበግ ቆዳ

ዶቃ፡- በአብዛኛው ለአንገትና ለልብስ ማስጌጫነት የሚያገለግልና ውስጡ የክር ማስገቢያ ቀዳዳ ያለው ድቡልቡል ቅርፅ ያለው

ግብር (መገበሪያ)፡- ለመናፍስት የሚቀርቡ የተመረጡ የእህል ዘሮች ወይም ደም

ጠንቋይ፡- ቡና በማፍላትና እጣን በማጨስ ከመናፍስቱ ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት በማድረግ እንደ ደብተራ የሰዎችን ዕጣ ፋንታ የሚናገር ሰው

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱን ያደረገው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በባሶና ወራና ወረዳ ስር በሚገኘው የቀይት ንዑስ ወረዳ ውስጥ በሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ላይ ነው፡፡ የጥናት ወረቀቱ ርዕስ 'በቀይት ንዕስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች' የሚል ሲሆን በስሩ አምስት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህም ዕምነቶች ጫት መቀቀል፣ ጭዳ፣ አድባር፣ ቦረንትቻ እና አቴቴ/ፈጫሳ ሲሰኙ መነሻቸው፣ ፋይዳቸው፣ ሀይማኖታዊ ትስስራቸው፣ ከበራቸው እንዲሁም በአካባቢው ማህበረሰብ ለዕምነቶቹ ያለው አመለካከት በዚህ የጥናት ወረቀት ውስጥ ተዳሷል፡፡ ዋና አላማውም የእነዚህን ዕምነቶች መነሻ፣ ይዘትና አከባበር ማሳየት ነው፡፡

ለጥናቱ በግብዐትነት ያገለገሉት ከቀዳማይና ካልኣይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ሲሆኑ በመረጃ መሰብሰቢያነት ደግሞ በዋናነት አገልግሎት ላይ የዋሉት ምልከታና ቃለምልልስ እንዲሁም የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ በእነዚህ ሶስት ዘዴዎች ከ23 የመረጃ ሰጪዎች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን መረጃ ሰጪዎቹ የተመረጡት ባሳዩት ፈቃደኝነት ነው፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች ደግሞ ገላጭ በሆነ የትንተና ዘዴ ተተንትነው እና በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ቀርበዋል፡፡ መረጃዎቹ የተተነተኑት በCathrine Bell የከበራ አይነቶችን እና በPascal Boyer & Pierre Liénard የከበራ መገለጫዎች ፅንሰ ሀሳቦች ተቃኝተው ነው፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት በተጠኚው አካባቢ የተጠቀሱት አምስት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የሚከወኑት ራስን፣ ቤተሰብን፣ ንብረትን እንዲሁም ቀዬን ከክፉ ነገሮች ቀድሞ ለመከላከልና ከተከሰቱ በኋላ ምህረትን ለማግኘት ነው፡፡ ከዋኞቹ እነዚህን ክዋኔዎች በመከወናቸው ከተመላኪዎቹ አካላት ጥበቃን አግኝተናል ብለው ስለሚያምኑ ልቦናዊ ዕረፍትን ያገኛሉ፡፡

የክዋኔዎቹ መተላለፊያ መንገድ ፅሁፋዊ ባለመሆኑ የከበራ መልኮቹ ላይ በየጊዜው ለውጥ ይታያል፡፡ ከለውጡ ባለፈም ከተለያዩ አካላት በሚነሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት እየተቀዛቀዘ መጥቷል፡፡

# 1. መግቢያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በባሶና ወራና ወረዳ ስር በሚገኘው የቀይት ንዑስ ወረዳ በተለያዩ ጊዜያት የሚፈፀሙትን ሃገረሰባዊ ዕምነቶች መመርመርና ከበራቸውን በጉልህ ማሳየት ነው፡፡

ጥናቱ የተነሳበትን ጉዳይ በአግባቡ ለመመርመር ያመቸኝ ዘንድ ይህ የጥናት ወረቀት በአምስት ዋና ዋና እና በሌሎች በርካታ ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያው ክፍል የመግቢያ ነጥቦች የተነሱ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል አካባቢያዊ ዳራ ተዳሷል፡፡ በሌሎቹ ከሶስት እስከ አምስት ባሉት ክፍሎች ደግሞ ክለሳ ድርሳናት፣ የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ማጠቃለያ በቅደም ተከተል ተካተዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በረዥሙ የሰው ልጅ የህይወት ጉዞ ውስጥ አይቀሬ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ እምነት ነው፡፡ የዕምነት ደረጃዎቹና የመገለጫ መንገዶቹ የተለያዩ ቢሆኑ0ም በሁሉም ሰዎች ዘንድ የጋራ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ እምነት እንደሚከተሉት ሃይማኖት፣ እንደሚኖሩበት ማህበረሰብ ባህል፣ እንደየ ግለሰቦቹ ርዕዮተ ዓለም፣ ወዘተ ይለያያል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ የሰዎች የጋራ ጉዳይ በመሆኑ የየአካባቢው ማህበረሰብ በቡድን ወይም በተናጠል የሚከተሏቸውና የሚከውኗቸው በርካታ ሃገረሰባዊ ዕምነቶች አሉ (Sims እና Stephens 2011፡ 56-58)፡፡ በዚህ ጥናትም ውስጥ 'ሀገረሰባዊ ዕምነት' በሚለው ዕሳቤ ስር የተመለከትኳቸው ተተኳሪ በሆነው አካባቢ በቡድንም ሆነ በተናጠል፣ በቤት ውስጥም ይሁን ከቤት ውጪ በግዴታም ሆነ በውዴታ በማህበረሰቡ ዕውቅና ተሰጥቷቸውና ወቅትን ጠብቀው የሚከበሩት ዕምነታዊ ከበራዎችን እና ክዋኔዎችን ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በትምህርት መርሀ ግብሩ ኮርሱን ለማጠናቀቅ የመመረቂያ ፅሁፍ ማዘጋጀት ግዴታ መሆኑ ጥናት ለማድረግ እንደ አንድ አነሳሽ ምክንያት ሊጠቀስ ቢችልም ጥናቴን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለመስራት ያነሳሱኝ ግን ሌሎች ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት እኔም በልጅነቴ እምነቶቹን በሚከውን ቤተሰብ ውስጥ ያደኩ መሆኔ ነው፡፡ በጊዜው ስለ እምነቶቹ ምንም አይነት ግንዛቤ ባይኖረኝም ለእምነቶቹ ማስፈፀሚያነት የሚዘጋጁትን ዝግጅቶችና ክዋኔዎች በጉጉት እጠባበቅ ነበር፡፡ የሚዘጋጁት ምግቦች እና በከዋኞቹ የሚባሉትና የሚደረጉት ነገሮች

ከወትሮው የተለዩ መሆናቸው እምነቶቹ የሚፈፀሙባቸውን ቀናት ይበልጥ እንድናፍቅ ያደርጉኝ ነበር። በወቅቱ እነዚህን ጉዳዮች በጉጉት ጠብቄ የሚደረገውን ከማየትና የተሰጠኝን ከመብላት ባለፈ ብስለቱ ስላልነበረኝ ከእምነቱ ጋር በተያያዘ ድርጊቶቹ ለምን፣ በማን፣ መቼ፣ እንዴት፣ እና ለማን ይከወናሉ የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ አልቻልኩም። አሁን ግን እነዚህንና ተያያዥ ጉዳዮችን በጥልቀት የማወቅ ፍላጎት ስላደረብኝ እና ጥያቄዎቹን ለማንሳት የሚያስችል አቅምም ስላለኝ ርዕሰ ጉዳዩን ለጥናቱ ይሆን ዘንድ መርጬዋለሁ።

በሁለተኛ ደረጃ ምክንያት የሆነኝ ደግሞ የሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ስርዓተ ክዋኔ ከጊዜ ወደጊዜ እየተቀዛቀዘ መሄድ ነው። ለዚህም በምክንያትነት የሚነሱ ጉዳዮችን ከመፈተሽ በተጨማሪም ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ሙሉ በሙሉ ከመጥፋታቸው በፊት ማግኘት የምችላቸውን መረጃዎች ሰንዶ የማስቀመጥ ፍላጎት ስለ አሳደረብኝ ለጥናቱ ቀዳሚ ተመራጭ ርዕስ አድርጌዋለሁ።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የጥናቱ ዋና ዓላማ በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን መነሻቸውን፣ ይዘታቸውንና ከበራቸውን በጥልቀት ማሳየት ነው። ጥናቱ ከዋና ዓላማው በተጨማሪም የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቶ ይዟል።

- የአካባቢው ነዋሪዎች ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹን ለምን ዓላማ እንደሚከውኗቸው መመርመር።
- የሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ተከታዮች ዕምቶቹን በመፈፀማቸው ያገኟቸው ጥቅሞች እንዲሁም ቢያቋርጡ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መለየት።
- ዕምነቶቹን መፈፀም ወይም ማቋረጥ የፈለገ ሰው የሚከተላቸው ሂደቶችን በየደረጃው ማሳየት።
- የአካባቢው ማህበረሰብ ለዕምነቶቹ ያለውን አመለካከት እና የሚሰጣቸውን ግምት መለየት።
- ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆናቸውን መፈተሽ።

### 1.4 በጥናቱ የሚመለሱ የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የተነሳበትን ዓላማ በሚያሳካበት ሂደት ውስጥ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የአካባቢው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹን እንዴት ይረዳቸዋል?
- ሀገረሰባዊ ዕምቶቹ መቼ፣ በማን፣ ለምን እና እንዴት ይከበራሉ?
- በሀገረሰባዊ ዕምቶቹ ውስጥ ተመላኪው አካል ማነው?
- ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ማህበረሰቡ ከሚከተለው ሀይማኖት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ወይም ልዩነት ምንድነው?

### 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ለአንድ ጥናት ስኬታማነት መሰረታዊ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል የመረጃ አቀባዮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃ መተንተኛ መንገዶች ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ ጥናቱን ውጤታማ የሚያደርገው የእነዚህ ነገሮች የሶስትዮሽ ውህደት ነው፡፡

#### 1.5.1 የመረጃ ምንጭ

ጥናቱን ያከናወንኩት ጠቃሚ መረጃዎችን ከቀዳማይና ከካልኣይ የመረጃ ምንጮች በመሰብሰብ ነው፡፡ በዚህም ከቤተመፅሃፍት፣ ከተለያዩ ቢሮዎችና ስለ አካባቢው ከሚያውቁ ሰዎች እንዲሁም ስለነዚህ ሃገረሰባዊ ዕምነቶች ዕውቀት ካላቸውና ዕምነቶቹን ከሚከውኑ ሰዎች ቃላዊና ፅሁፋዊ መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ፡፡ መረጃዎቹን ከቀዳማይ መረጃ ምንጮች ለመሰብሰብ ከሚያዚያ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ጊዜያት ያህል የመስክ ጉዞ ለማድረግ አቅጄ የነበረ ቢሆንም የዕምነቶቹ ስርዓተ ክዋኔዎች ቋሚ የሆነ ቀን ስለሌላቸው ክዋኔ የሚደረግበትን ቀን እዛው አካባቢ ሆኜ ለመጠበቅ ተገድጃለሁ፡፡ በዚህም ከሚያዚያ 10 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 16/2006 ዓ.ም ድረስ በመስክ ስራ ላይ ቆይቻለሁ፡፡ ይህም ቆይታዬ ስለ ጫት ቅቀላ፣ ስለ ጭዳ፣ ስለ አድባርና ስለ ቦረንትቻ መረጃ የሰበሰብኩበት ሲሆን ስለ አቴቴ (ፊጫሳ) በተመለከተ ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ ደግሞ ከሐምሌ 08 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ የመስክ ቆይታ አድርጊያለሁ፡፡ እነዚህን መደበኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ጉዞዎች ከማድረጌ በፊት ደግሞ ስለ አካባቢው እና ስለ ዕምነቶቹ መከወኛ ጊዜ ቅኝት ለማድረግ በተመሳሳይ አመት በጥር ወር ውስጥ አንድ ጊዜ ወደ አካባቢው ሄጃለሁ፡፡

ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደጠቀስኩት በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው አካባቢ የቀይት ንዑስ ወረዳ ነው፡፡ ይህንን አካባቢ የመረጥኩበት ምክንያት የዚህን አካባቢ ሃገረሰባዊ ዕምነቶች ለማጥናት ባለኝ ፍላጎትና የአካባቢውም ተወላጅ በመሆኔ ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ለማግኘት ብዙም ችግር አይገጥመኝም ብዬ በማሰብ ነው፡፡ በዚህ ንዑስ ወረዳ ስር ከሚገኙት 11 ቀበሌዎች ውስጥ ቀይት፣ ጉዶበረት ከተማ፣ ባሶደንጎራ እና ጉዶበረት ዙሪያ የተባሉት 4 ቀበሌዎች የጥናቴ ዋነኛ ትኩረቶች ናቸው፡፡ ጥናቱን በንዑስ ወረዳው ብቻ እንዲቀነበብ ያደረኩበት ምክንያትም በአራት ቀበሌዎች ላይ ብቻ ጥናት በማድረግ በአቢይ ወረዳው (ባሶና ወራና ወረዳ) በ31 ቀበሌዎች ስለሚከወኑት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አያስችልም የሚል ዕምነት ስላደረብኝ ነው፡፡

በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት በመረጃ ሰጪነት የተመረጡት ሰዎች ከዕምነቶቹ ጋር ቀጥተኛም ሆነ ኢ-ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ሃገረሰባዊ ዕምነቶቹን የሚያከብሩት ሰዎች (ከዋኞች)፣ በፊት ያከብሩ የነበሩ አሁን ግን ክወናውን ያቋረጡ ሰዎች፣ የከበራው ተሳታፊዎች እንዲሁም የሃይማኖት መሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ አስራ ሶስት ከዋኞችን፣ አራት የሃይማኖት መሪዎችን፣ አራት ዕምነቶቹን ሲከውኑ ቆይተው ያቋረጡ ሰዎችን፣ ሁለት በከበራዎቹ ላይ የሚሳተፉ፣ በማነጋገሬ በጥቅሉ ሀያ ሶስት የመረጃ ሰጪዎች ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት ባሳዩት ፈቃደኝነት ነው፡፡ ይብዛም ይነስም ከሁሉም መረጃ ሰጪዎቼ ጠቃሚ መረጃዎችን የወሰድኩ በመሆኑ ያላቸውን ሚና በአቢይና በንዑስነት አልከፋፈልኳቸውም፡፡

የመረጃ ሰጪዎቹ የፆታ ስብጥር ሁለቱንም ፆታዎች ያማከለ ቢሆንም እኩል ስብጥር የሚታይበት ግን አይደለም፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ከዋኞቹ እንደ ተከዋኙ ሀገረሰባዊ ዕምነት እና እንደየ ቤቱ የከዋኞቹ ፆታ ስለሚለያይ ነው፡፡ በዚህም ወንዶች የሚከዉኗቸውን ሀገረሰባዊ ዕምነቶች በተመለከተ ዋና መረጃ ሰጪዎቹ ወንዶች ሲሆኑ በሴቶችም በሚከወኑት ላይ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት አስራ አምስት ወንዶችና ስምንት ሴቶች በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ አቀባይነት ተሳትፈዋል፡፡ የዕድሜ ስብጥራቸውን በተመለከተ በአካባቢው የዕምነቶቹ ከዋኞች አባወራዎችና እማወራዎች ቢሆኑም ያላቸው ግንዛቤና አመለካከት እንደየዘመናቸው ስለሚለያይ በተቻለ መጠን በወጣትነት፣ ከጎልማሳነትና በአዛውንትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መረጃ ሰጪዎችም እንዲካተቱ ቢደረግም አብዛኞቹ ግን በጎልማሳና በአዛውንት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ በሃይማኖት ረገድ አብዛኞቹ (99.2%) የንዑስ ወረዳው ነዋሪዎች

የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው በመረጃ ሰጪነት የተካተቱትም የዚሁ ሀይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡

### 1.5.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ከተተኳሪው አካባቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጠቃሚና ተገቢ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ሰብስቢያለሁ፡፡

ለጥናቱ ተስማሚ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለምልልስ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለጥናቱ ግብዓት የሆኑትን መረጃዎች ለመሰብሰብና በጥናቱ መመለስ የሚገባቸውን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ዋነኛ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

**ምልከታ**

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ በዋናነት የተጠቀምኩት የምልከታ ዘዴን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ያልተዛባ መረጃ ለማግኘት በማሰብ እና በፎክሎራዊ ጥናት በተለይም ደግሞ ክዋኔን የተመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስፈላጊና ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ በመገንዘብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሀገረሰባዊ ዕምቶቹን ስርዓተ ክዋኔ ለመረዳት ምልከታ ዘዴን ተጠቅሚያለሁ፡፡

የንዑስ ወረዳው ነዋሪዎች ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹን የሚፈፅሙት በተለያዩ ጊዜያት ነው፡፡ ምንም እንኳን የሚከውኑት በተለያዩ ወራት ቢሆንም ተገቢውን መረጃ ለማግኘት እያንዳንዳቸው ዕምነቶች በአብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚከወኑባቸውን ጊዜያት (በሚያዚያ፣ በግንቦትና በሐምሌ ወራት) በመለየትና በቦታው በመገኘት ምልከታ አድርጊያለሁ፡፡ ምልከታዬም ኢ-ተሳትፏዊ ነው፤ ለዚህም ምክንያቴ በክዋኔው ላይ የሚከወኑ ድርጊቶችን ሙሉ በሙሉ ለመከታተል እንዲያመቸኝ በማሰብ ነው፡፡

ይህን ዘዴ በመጠቀም በአካባቢው የሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ከበራዎች በሚደረጉበት ጊዜና ቦታ በመገኘት ከተፈጥሯዊው መቼት አስፈላጊዎቹን መረጃዎች ለመውሰድ ችያለሁ፡

## ቃለ ምልልስ

ከክዋኔ ውጪ የሆኑትን መረጃዎች (ከሃይማኖት ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ መነሻ ታሪኮች፣ ከዕምነቶቹ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ ያገኛቸው ጥቅሞች ወይም የደረሱባቸው ጉዳቶች እና ዕምነቶቹን ለምን ዓላማ እንደሚከውኗቸው) ለማሰባሰብ እንዲሁም ምልከታ በሚደረግበት ወቅት ግልፅ ያልሆኑልኝን ጉዳዮች ለመረዳት ስለ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ዕውቀት ካላቸውና ፍቃደኛ ከሆኑት መረጃ ሰጪዎች ጋር ቃለ ምልልስ አድርጊያለሁ፡፡

ለጥናቱ የፅሁፍ መጠይቅን ተግባራዊ ያላደረግሁት የዕምነቶቹ ከዋኞች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ መደበኛ ትምህርትን ያልቀመሱ በመሆናቸው ምክንያት ነው፡፡ የተወሰኑ የተማሩ (ማንበብና መፃፍ የሚችሉ) ቢኖሩም ከሚኖራቸው ጊዜና በፅሁፍ መጠይቅ ተገቢ ፎክሎሯዊ መረጃዎችን ከማግኘት አንፃር አመቺ ሆኖ ስላላገኘሁት መረጃን በፅሁፍ መጠይቅ ለማሰባሰብ አልደፈርኩም፡፡ ነገር ግን አንድ መረጃ ሰጪ ምላሾቻቸውን በፅሁፍ የመስጠት ፍላጎት ስላሳዩ አንድ የፅሁፍ መጠይቅ መልክ ያለው ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የፅሁፍ መጠይቅ ያልሆነ ዘዴን ተጠቅሚያለሁ፡፡

## የቡድን ውይይት

ዕምነቶቹን በተመለከተ በተለያዩ የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ባሉት ሰዎች መካከል ያለውን የአመለካከት ልዩነት ይበልጥ ለመረዳት እንደ መረጃ ሰጪዎቹ ፈቃደኝነት የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመጠቀም መረጃ የምሰበስብበት ሁኔታ ይኖራል የሚል ዕቅድ ነበረኝ፡፡ ይህንን ወደ ተግባር ለመቀየር ሰባት አባላት ያሉት ቡድን በማደራጀት ለዕምነቶቹ ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ መረጃ ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም ለአድባር በተሰበሰቡበት አጋጣሚ ቡድናዊ መረጃን ወስጃለሁ፡፡ የስራ ጊዜያቸውን ላለመሻማት የቡድን ውይይቱን ያደረኩት የበዓል ቀን ማለትም ግንቦት አምስት ቀንን በመጠበቅ ነው፡፡ ቀኑ የተመረጠው በሀይማኖታቸው ዕለቱ በዓል የሚውልበት በመሆኑና ስራ ስለማይሰራ ለተሳታፊዎቹ የሚመች ቀን በመሆኑ ሲሆን ለሁሉም አማካኝ በሆነው በባሶ ደንጎራ ቀበሌ ልዩ ስሙ ጅብ ዋሻ በመባል የሚጠራዉ አካባቢ አቶ ዘውዴ አሰፋ ውድማ ላይ ነው፡፡ ውይይቱ ከጠዋቱ 4:22 ሰዓት ተጀምሮ 5:56 ሰዓት ላይ የተጠናቀቀ ሲሆን በድምሩ 1:34 ሰዓት ፈጅቷል፡፡ በውይይቱ ከተሳተፉት ውስጥ ሁለቱ በሌላ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴም መረጃ የሰጡ ሲሆን አምስቱ በቡድን ውይይት ላይ ብቻ የተሳተፉ ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቦ ለመያዝ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ የድምፅ፣ የፎቶና የቪዲዮ መቅረጫያ መሳሪያዎች ዋናዎቹ ቁሳቁሶች ሲሆኑ እነዚህን ቁሳቁሶች በመጠቀም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ላልሆኑ መረጃ ሰጪዎች ማስታወሻ ደብተርን ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 1.5.3 የመረጃ አተናተን

ከላይ በጠቀስኳቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም ከመረጃ ምንጮች የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች የከበራ (Ritual) ፅንሰ ሃሳብ መነሻ በማድረግ ገላጭ በሆነ መንገድ ተንትኛለሁ፡፡ ከከበራ ፅንሰ ሀሳቦች መካከል ለዚህ ጥናት መቃኛነት የተጠቀምኩት የ Cathrine Bell የከበራ አይነቶችን እና የPascal Boyer & Pierre Liénard የከበራ መገለጫዎችን ነው፡፡ በነዚህ ነጥቦች ብቻ ለመወሰኔ ምክንያቱ ደግሞ በጠባብ መነፅር አጥርቶ ማየት የተሻለ ነው የሚል ዕምነት ስላለኝ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጊዜና በቦታ የተወሰነ ነው፡፡ ከጊዜ አኳያ ሲታይ በጥናቱ ውስጥ የተተነተኑት መረጃዎች በአንድ ዓመት ውስጥ ማለትም በ2006 ዓ.ም. በተጠኚው አካባቢ ከተደረጉት ከበራዎች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በዚህ ዓመት ከተደረጉት ከበራዎችም መካከል በሚያዚያ፣ በግንቦትና በሐምሌ ወራት የተከወኑት ሰፊ መረጃ የተሰበሰበባቸው ናቸው፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ የሚሆነው አካባቢ በወረዳው የሚገኝ አንድ ንዑስ ወረዳ ላይ ብቻ ነው፡፡ በንዑስ ወረዳው ስር ከሚገኙት 11 ቀበሌዎች መካከል 4 ቀበሌዎች (ባሶ ደንጎራ፣ ቀይት፣ ጉዶበረት ከተማና ጉዶበረት ዙሪያ) ብቻ በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች መረጃ በቀላሉ ይገኝባቸዋል ተብለው የተገመቱ ሲሆኑ ሌላ የተለየ መስፈርት ሳይወጣላቸው የተመረጡ ናቸው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

ጥናቱ የሚሞላቸው ክፍተቶች ቢኖሩም ውስንነቶችም አሉበት፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ የሚከወኑ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ቢኖሩም የእኔ ጥናት ትኩረት የሆኑት ግን ሁሉም አይደሉም፡፡ በጥናቱ የተካተቱት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች አቴቴ (ፈጫሳ)፣ ጭዳ፣ አድባር፣ ቦረንትቻና ጫት መቀቀል ናቸው፡፡ ከእነዚህ ዕምነቶች ውጪ ሌሎች ወቅት ጠብቀውም ሆነ በተለየ አጋጣሚ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ እነዚህ ተጠኚ

ሀገረሰባዊ ዕምቶችንም ቢሆን ከተለያዩ በርካታ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ማጥናት ቢቻልም በዚህ ጥናት ውስጥ ግን የተዳሰሱት ጉዳዮች ክዋኔዎች፣ ማህበረሰቡ ከሚከተለው ሀይማኖት ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ታሪካዊ መነሻቸው፣ የሚከበሩበት ዓላማና የአካባቢዉ ማህበረሰብ ለዕምነቶቹ ያለው እይታና ግንዛቤ ብቻ ናቸው፡፡

በተጨማሪም ጥናቱ መረጃ ሰጪዎች ውሱንነት ይታይበታል፡፡ በዚህም በንዑስ ወረዳው የሚኖረው አጠቃላይ ህዝብ ውስጥ ለጥናቱ መረጃ ሰጪነት የተሳተፉት ግን ሀያ ሶስት ብቻ ናቸው፡፡

ለእነዚህ ውሱንነቶች ዋነኛ ምክንያቶች መካከል የመጀመሪያው የሚጠናው ጉዳይ ዕምነት በመሆኑና ዕምነትን የተመለከቱ መረጃዎችን መስጠትም ሆነ በክዋኔዎቹ ላይ የውጪ ሰው መጋበዝ የሚፈጥረው ችግር አለ የሚል እሳቤ በከዋኞቹ ዘንድ መኖሩ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለት ምክንያቶች ያሉ ሲሆን አንዱ ለመርሀ ግብሩ ጥናቱ በቂ ነው ብዬ ማሰቤ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከዚህ በላይ ለማስፋት ዩኒቨርሲቲው ጥናቱን ለማከናወን የመደበው ገንዘብ በቂ አለመሆኑ ነው፡፡

### 1.8 የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱን ለማድረግ አስፈላጊም አስገዳጅም የሚሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ አስገዳጅ የሚያደርገው ጉዳይ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ በአካባቢው የሚከወኑበት ሁኔታ እየቀዘቀዘና እየቀረ መምጣቱ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ደብዛቸው ሳይጠፋ መሰነድ ያለባቸው በመሆኑ አስፈላጊነቱ አያጠራጥርም፡፡

ጥናቱ የሚሞላው ክፍተት እንዳለ ሆኖ ለሚከተሉት ጉዳዮችም አስፈላጊ ነው ማለት ይቻላል፡-

- ስለ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡
- በዕምነቶቹ ዙሪያ ያለውን ፎክሎራዊ ለውጥ በተወሰነ መልኩ ያሳያል፡፡
- ሰፊ ጊዜ እና ገንዘብ በመመደብ ጥናቱን ደግፈውም ሆነ ነቅፈው ወይም ከሌሎች ጉዳዮች ጋር አያይዘው ለማጥናት ለሚፈልጉ ሰዎች መነሻ ሃሳብ ይሰጣል፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ይህንን ጥናት በማደርግበት ወቅት በርካታ ችግሮች ቢያጋጥሙኝም በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የማነሳው ግን ዋና ዋናዎቹን ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ችግሮች እና ለችግሮቹ የተወሰዱ መፍትሄዎች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል፡፡

- አብዛኞቹ የሃገረሰባዊ ዕምነቶቹ ከዋኞች የሚከውኑት በውርስ የተቀበሉትን በመሆኑ ክዋኔው የተመለከቱ ጉዳዮች ጥልቀት ያለው መረጃ የላቸውም፡፡
- የዕምነቶቹ ክዋኔዎች ከባዕድ አምልኮ ተመድበው ከሀይማኖት ተቋማት አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚደርስባቸው የበለጠ ችግር ይደርስብናል ብለው በማሰብ መረጃ ለመስጠት የተቆጠቡ በርካታ ሰዎች አጋጥመውኛል፡፡
- አድባር በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት በተለያየ ቦታ የሚደረግ በመሆኑ ከአንድ በላይ በሆኑ ክዋኔዎች ላይ ተገኝቼ ስርዓተ ክዋኔውን ለመመልከት ችግር ገጥሞኛል፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እነዚህን ዋና ዋና እንቅፋቶች ለመቅረፍ እንደየችግሩ አይነት መፍትሄዎችን በማደራጀት ስራውን የተቃና ለማድረግ የተቻለኝን ሁሉ ሞክሪያለሁ፡፡ በዚህም መሰረት በከዋኞቹ ዘንድ የታየው የመረጃ ክፍተት ለዚህ ጥናት ዋነኛው ችግር የነበረ ሲሆን ይህንን ለመሙላት የታሪክ እውቀት ያላቸውን ሰዎች በመረጃ ሰጪነት ተጠቅሚያለሁ፡፡ በሁለተኛነት ለተጠቀሰው ችግር ሁለት መፍትሄዎችን ወስጃለሁ፡፡ የመጀመሪያው ለዚህ ጥናት መረጃ በመስጠታቸው የሚገጥማቸው ችግር እንደሌለ እነርሱን በጥንቃቄ ማሳመን ሲሆን ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ የሚያውቁኝ እና የሚያምኑኝን ሰዎች ማነጋገር ወይም በሚያውቁት ሰው በኩል ወደ መረጃ ሰጪዎቹ መድረስ ነበር፡፡ ለሶስተኛው ችግር የወሰድኩት መፍትሄ የአንደኛው አድባር ስርዓተ ክዋኔ ሲጠናቀቅ ሌላኛው ስርዓተ ክዋኔ ላይ መገኘት ነው፡፡ ምንም እንኳን ይኸኛው መፍትሄ የሁለተኛውን የአድባር ስርዓተ ክዋኔ ከጅማሬ እስከ ፍፃሜ ያለውን ሂደት ለመመልከት ባያስችለኝም የጎደለውን መረጃ በአንደኛው አድባር ባደረኩት ምልከታና በቃለ ምልልስ ለማሟላት ብርቱ ጥረት አድርጊያለሁ፡፡

## 2 አካባቢያዊ ዳራ

### 2.1 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ

በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው አካባቢ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኘው የባሶና ወራና ወረዳ ስር የሚተዳደረው የቀይት ንዑስ ወረዳ ነው፡፡ አቢይ (የባሶና ወራና) ወረዳው በስሩ 31 ቀበሌዎችን ይዟል፡፡ ወረዳውን የሞጃና ወደራ፣ የሞረትና ጅሩ፣ የጣርማበር፣ የአንጎለላና ጠራ፣ የአንኮበር እና እንሳሮና ዋዩ በጥቅሉ ስድስት ወረዳዎች ያዋስኑታል፡፡




ካርታ 1፡- ባሶና ወራና ወረዳ (በባሶና ወራና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ ካርታ፣ 2006 ዓ.ም.)

የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ በ2006 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ባወጣው መረጃ መሰረት ወረዳው የሚገኝበት አካባቢ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታው 50% ያህሉ ደጋማ ነው፡፡ ቀሪው ደግሞ 46% ወይናደጋማ፣ 2% ቆላማ፣ 2% ውርጭ ነው፡፡

የአቢይ ወረዳው የህዝብ ብዛት ጠቅላላ ድምር 132,55 ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 67,865 ወንዶች ሲሆኑ 64,688 ሴቶች ናቸው፡፡ ይህ የህዝብ ብዛት በዕድሜ ክልል ተከፋፍሎ ሲታይ ከ0 — 14 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት 53,228 ሲሆኑ ከ15 — 64 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ደግሞ 69,234 ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 1,0091 የሚሆኑት 65 እና ከዚያ በላይ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

### 2.2 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የማኅበረሰቡ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ግብርና ነው፡፡ በዚህ መሰረት ማኅበረሰቡ ለአካባቢው አየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ የእህል ዘሮችን ያመርታል፡፡ በአካባቢው በብዛት የሚመረቱት የእህል ዘሮች ገብስ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ አተር፣ ተልባ፣ ምስር፣ ጤፍ እና ጓያ ሲሆኑ ለምግብነት የሚጠቀሙትም እነዚሁኑን የተለያዩ ጥራጥሬዎች ነው፡፡ በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወረዳው ግብርና ፅህፈት ቤት ትምህርትና ድጋፍ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ቀይስር፣ ቲማቲም፣ ካሮት፣ ቆስጣ፣ ጥቁር ጎመን፣ ሰላጣና ጥቅል ጎመን የመሳሰሉ አትክልቶች ምርት በብዛት እየተስፋፋ መጥቷል፡፡

የማኅበረሰቡ ዋነኛ መተዳደሪያ ግብርና ይሁን እንጂ እንደሌሎቹ አካባቢዎች ሁሉ ከብትን በማርባት ለምግብነትና ለሌሎች አገልግሎቶች መጠቀም በአካባቢው የተለመደ ነው፡፡ የጋማ ከብቶች፣ የቀንድ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎችና ዶሮች በአካባቢው የሚረቡ የቤት እንስሳት ናቸው፡፡ የጋማ ከብቶች ለአብዛኛው የአካባቢው የማህበረሰብ ክፍል ከፍተኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን በተለይ ዕቃ ከቦታ ቦታ ለመጓጓዝ እጅጉን ተመራጭ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ የአካባቢው ምርቶችን ለገበያ በማቅረብ አጋዥ የገቢ ምንጭን በመፍጠር ይተዳደራሉ፡፡

### 2.3 አስተዳደራዊ ሁኔታ

የባሶና ወራና ወረዳ በአንድ ወረዳና በአንድ ንዑስ ወረዳ የተዋቀረ ነው፡፡ ቀይት በዚህ ስር ከሚገኙ ቀበሌዎች መካከል አንዱ ሲሆን ራሱን ቀይትን ጨምሮ በአቅራቢያው ለሚገኙ 11 (ቀይት፣ ባቄሎ፣ መሃል አምባ፣ ጉዶበረት ከተማ፣ ጉዶበረት ዙሪያ፣ ባሶ ደንጎራ፣ አዲስጌ፣

ናስና ቁም አምባ፣ አባሞቴ፣ ጎሹ አገርና ጭራሮ ደብር) ቀበሌዎች በንዑስ ወረዳነት ያገለግላል፡፡ ንዑስ ወረዳው ከ1989 ዓ.ም በፊት በነበረው አሰራር ወረዳ የነበረ ቢሆንም ከ1989 ዓ.ም በኋላ ግን በባሶና ወራና ወረዳ ስር ሆኖ በአቅራቢያው ለሚገኙ ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት ቀበሌዎች በንዑስ ወረዳነት እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡ ከወረዳው መቀመጫ ደብረብርሃን በ17 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ጤና ጣቢያ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ትምህርት ቤት፣ ፍርድ ቤትና የመሳሰሉት አስተዳደራዊ ተቋማት ተሟልተውለት ተጠሪነቱን ለአቢይ ወረዳው በማድረግ የተለያዩ መንግስታዊ ግልጋሎቶችን በስሩ ለሚገኙት ቀበሌዎች እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ንዑስ ወረዳ ስር የሚገኙት ቀበሌዎች የመንገድ፣ የንፁህ ውሃ፣ የመብራት፣ የአፀደ ህፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና የትራስፖርት መሰረተ ልማቶችን እንዲሁም የጋራ መፀዳጃ ቤቶች በየአቅራቢያቸው እየተሟሉላቸው ነው (የባሶና ወራና ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽህፈት ቤት፣ 2006ዓ.ም.)፡፡




ካርታ 2፡- ቀይት ንዑስ ወረዳ (በባሶና ወራና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀ ካርታ፣ 2006 ዓ.ም.)

## 2.4 ቋንቋና ሀይማኖት

በቋንቋ ረገድ በወረዳውም ሆነ በንዑስ ወረዳው የሚነገረው ቋንቋ አማርኛ ሲሆን የስራ ቋንቋውም አማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ አንዳንድ የኦሮምኛና የትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቢኖሩም በህዝብና ቤቶች ቆጠራ በቋሚ ነዋሪነት የተመዘገቡ አይደሉም፤ በስራ ምክንያት ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ የተለያዩ ስራዎችን የሚሰሩ ናቸው፡፡

የወረዳው ኗሪዎች ከሚከተሉት ሀይማኖት አኳያ ሲታይ ከወረዳው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ውስጥ 93% የሚሆኑት የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 7% ደግሞ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ የንዑስ ወረዳውን ሀይማኖታዊ መረጃ ስንመለከት ደግሞ 99.2% ኦርቶዶክሶች ሲሆኑ 0.8% ደግሞ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መረጃ እንደሚያሳየው አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ የሚከተለው ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ክርስትናን ነው፡፡ ከዚህ ሃይማኖት ጎን ለጎንም ገሚሱ የማኀበረሰቡ አባላት የሚያምንባቸውና የሚያከብራቸው ሌሎች ሃገረሰባዊ ዕምነቶች አሏቸው፡፡ ዕምነቶቹ እንደ ተቋማዊ ሀይማኖት በቅዱሳን መጽሀፍት የታገዙ ትዕዛዛትና መመሪያዎች ባይኖሯቸውም ማህበረሰባዊ ዕውቅና አግኝተው እየተከበሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ለዚህ ወቅት የደረሱ ናቸው፡፡

ከተጠኚው ንዑስ ወረዳ ጋር የተያያዙ መልክዓ ምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ እንዲሁም ቋንቋን የተመለከቱ የተደራጁ መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን በአቢይ ወረዳው ስር የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን በአንድም በሌላም መንገድ የሚጋራቸው የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ስላሉ ወረዳውን በተመለከተ የተገኙን መረጃዎች በዳራው ስር መጥቀሱ ጠቃሚ ነው ብዬ በማሰብ በዚህ ክፍል ስር አስፍሬያቸዋል፡፡

# 3. ክለሳ ድርሳናት

## 3.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 3.1.1 የሀገረሰባዊ ዕምነት ምንነት

በጥናቱ ውስጥ የሚነሱትን ነጥቦች ይበልጥ ለመረዳት ያመች ዘንድ በቅድሚያ ቁልፍ የሆኑትን እሳቤዎች መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ተተኳሪ የሆነው ዋነኛ ጉዳይ ዕምነት በመሆኑ በመጀመሪያ ምንነቱን ብሎም የሀገረሰባዊ ዕምነትን ምንነት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የእነዚህ ነጥቦች ምንነትና የትኩረት ነጥቦች እንዲሁም ምድቦች እንደሚከተለው ባጭሩ ተዳስሰዋል፡፡

ፈቃደ አዘዘ 'የስነቃል መመሪያ' በተሰኘው መፅሀፋቸው ውስጥ Dorsonን ጠቅሰው እንደገለፁት የፎክሎር የጥናት ዘርፎችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህ አራት ዋና ዋና ክፍሎች ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህልና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በስራቸው በርካታ ንዑሳን የጥናት ዘርፎችን የያዙ ናቸው (1991፡ 10)፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ሀገረሰባዊ ዕምነት ከሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚመዘዝ ነው፡፡ ፌስቲቫልና ክብረ በዓል (ከበራ)፣ መዝናኛና ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት እና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚጠኑ መሆናቸውን ፈቃደ በድጋሚ Dorsonን ጠቅሰው ገልፀዋል (1991፡13)፡፡ በሀገረሰባዊ ሃይማኖት ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑትን ጉዳዮች በተመለከተም የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፡-

> የሀገረሰባዊ ሃይማኖት ምርምር÷ በልዩ ልዩ በዓላት ላይ፣ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በሃይማኖት (መስጊድ፣ ቤተክርስቲያን፣ ምኩራብ ወዘተ) የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፤ በልደት፣ በግርዘት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን (interactions) ያጤናል፡፡ የጥናቱ ልዩ ትኩረት ግን ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን እመመርመር ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በሃይማኖት ሥርዓቶች ላይ በሚደረገው ጥናት ትኩረቱ በሚታወቁት የሃይማኖት መፅሀፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጪ ሰዎች በየራሳቸው (የሃይማኖቱ አማኝና ተከታይ መሆናቸውን ሳያቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምነቶችና በሚፈፅሟቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው (1991፡14)፡፡

በፈቃደ ገለፃ መሰረት ሀገረሰባዊ ዕምነት የአንድ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚተገብራቸው ዕምነታዊ ድርጊቶችን የሚመለከት ሲሆን የጥናት ዘርፉም እነዚህን ድርጊቶች ከተለያዩ ጉዳዮች አኳያ የሚመረምር ነው፡፡ ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ ዕምነት በሀገረሰባዊ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኝና የሚጠና ነው፡፡ 'ሀገረሰባዊ ዕምነት' የእንግሊዘኛውን 'folk belief' የሚተካ ስያሜ ነው፡፡ በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ከፈቃደ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ 'folk belief' እና 'folk religion' የመጀመሪያው በሁለተኛው ውስጥ የሚጠቃለል ሆኖ የሚጠቀስ ሲሆን በተወሰኑ የአማርኛ ፅሁፎች ውስጥ ግን 'ሀገረሰባዊ ዕምነት' እና 'ሀገረሰባዊ ሃይማኖት' የሚሉት ፅንሰሃሳቦች እየተተካኩ ግልጋሎት ላይ ሲውሉ ይስተዋላል፡፡ ይህ ሁኔታ በተመሳሳይ በድህረ ምረቃ ጥናቶች ላይም ጎልቶ የሚታይ ከመሆኑም በተጨማሪ በሰዎች ንግግር ውስጥ ኢ-ተቋማዊ ሃይማኖት፣ ሀገር በቀል ሃይማኖት፣ አምልኮ ወዘተ. የሚሉት ስያሜዎች ይኸንኑን ፅንሰ ሃሳብ ለመግለፅ ሲውሉ ያጋጥማል፡፡ የመፅሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም "**ሃይማኖት፤** ቃሉ እምነት ማለት ነው፡፡" (1992፡ 11) በማለት የሁለቱን ፅንሰሃሳቦች (ሀገረሰባዊ ዕምነትና ሀገረሰባዊ ሀይማኖት) ተመሳስሎን ያጠናክራል፡፡

እኔ በዚህ ጥናት ውስጥ የምዳስሳቸው ጉዳዮች በአብዛኛው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከወኑ በመሆናቸው እና በተቋማዊ ሃይማኖት (Institutional religion) ስር የሚገኙ ዕምነቶች በመሆናቸው 'ሀገረሰባዊ ዕምነት' የሚለውን ስያሜ ተጠቅሜያለሁ፡፡ ዕምነቶቹ በፅሁፍ የሰፈሩ መመሪያዎችና የተደነገጉ ትዕዛዛት የሌላቸው እንዲሁም ተስተላልፏቸው በቃልና በድርጊት የሆኑ ናቸው፡፡

የጥናቱ ማጠንጠኛ ሀሳብ ስለሆነው ዕምነት ሰፊው ትንታኔ ለመስጠት ከቃሉ ብያኔ መጀመር ተገቢ ነው፡፡ **'ዕምነት'** የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ተቋም ባዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት 'ሀይማኖት፣ አምልኮ፣ እርግጠኝነት፣ ሀላፊነት፣ ታማኝነት' የሚሉ ፍቺዎች ተሰጥተውታል (1993፡ 305)፡፡ የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ደግሞ ለቃሉ የሚከተሉትን ሁለት ፍቺዎች ያስቀምጣል፡- እምነት ሁለት ነገሮችን ይይዛል፡፡

1. ስለ አምላክ ወይም ስለሰው ዕውቀት ወይም አሳብ፡፡
2. በአምላክ ወይም በሰው ፍፁም ተስፋ ማድረግ (1992፡178)፡፡

ደስታ ተክለወልድም በበኩላቸው ቃሉ ሃይማኖት፣ ማመን፣ መታመን የሚሉ ትርጓሜዎች እንዳሉት ባጋጁት መዝገበ ቃላት ውስጥ ጠቁመዋል፡፡ 'ማመን' የሚለውንም ቃል መቀበል፣ መውደድ፣ ማክበር፣ እውነት ነው ብሎ መቀበል ነው በማለት ይፈቱታል (1962፡108-109)፡፡

ለ 'ዕምነት' የእንግሊዘኛ ቋንቋ አቻው የሆነውን 'belief'ን ደግሞ Oxford የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት "a strong feeling that someone or somebody exists or is true; confidence that something or somebody is good or right." (2006፡122) ይህንን ብያኔ ወደ አማርኛ ቋንቋ ስንተረጉመው "አንድ ነገር ወይም ሰው አለ ወይም እውነት ነው፤ ጥሩ ነው ወይም ትክክል ነው ብሎ ልበ ሙሉ የመሆን ጠንካራ ስሜት ነው፡፡"

ከእነዚህ ፍቺዎች መገንዘብ የሚቻለው ዕምነት አንድ ነገር ይሆናል ወይም ይፈፀማል ብሎ ማሰብ እንዲሁም አምላክን ወይም ሰዎችን ከጥርጣሬ ነፃ ሆኖ አስተሳሰባቸውን ወይም ድርጊታቸውን መከተል ነው፡፡ ዕምነት የጠነከረ ልቦናዊ ሂደት ቢሆንም በልቦና የሚታሰበውን ብቻ ሳይሆን ዕምነቱን የተመለከቱ ሌሎች ድርጊቶችንም ያካትታል (Sims and Stephens (2011፡ 56)፡፡ በጥቅሉ ዕምነት ማለት ሰዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ የሚተገብሩት ሲሆን ይፈፀምልናል ወይም ይከሰትብናል ብለው በማሰብ በጎ የሚሉትን ነገር እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁበት ክፉ ነገር ደግሞ እንዳይከሰትባቸው የሚከላከሉበት (የሚለማመኑበት) መንገድ ነው፤ ቃሉ ሂደትን የሚያሳይ ሲሆን በሚታመነው አካል እና በአማኙ መካከል የሚደረግ መንፈሳዊ ግንኙነት ነው፡፡

ሰዎች በሚከተሉት ሀይማኖት ውስጥ ጤንነታቸውን፣ ምጣኔ ሃብታቸውን፣ ማህበራዊ ኑሯቸውን ወዘተ በተመለከተ የተሻለ ነገር ከአንድ ልዕለ ሀያል ከሆነ አካል ይሰጠናል የሚል ዕምትነት ያሳድራሉ፡፡ ለግላቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለማህበረሰባቸው ብሎም ለሀገራቸው መልካም ነገር እንዲገጥማቸው ከሚያምኑበት ልዕለ ተፈጥሮ አካል የሚጠይቁበት፣ ምስጋና (መስዕዋት) የሚያቀርቡበትና ዕምነታቸውን የሚያፀኑበት አውድ በመፍጠር ጊዜን ጠብቀው ያከብራሉ፡፡ በተፈጠረው አውድ አስፈላጊውን ስርዓተ ክዋኔ ያደርጋሉ፡፡ ስርዓቱን በመጠበቅም ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፉታል፡፡

### 3.1.2 የከበራ ምንነት

ከበራ (Ritual)ን በተመለከተ በርካታ ፎክሎረኞች ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ ከበራ ምንድነው፣ ምን ላይ ያተኩራል፣ እንዴት ይጠናል፣ አይነቶቹ ምን ምን ናቸው እና ከመሳሰሉት ጉዳዮች

ጋር በተያያዘ ሃሳባቸውን በፅሁፉ ካሰፈሩት በርካታ ፎክሎሪኞች መካከል የተወሰኑት ከሰነዘሩት ሃሳብ ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑት ነጥቦች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

ፅንሰ ሃሳቡን በተመለከተ ሃሳብ ካሰፈሩ ፅሁፎች መክከል አንዱ የሆነው Encyclopidia of Social and Cultural Anthropology ከተለያዩ ትወራዎች በመነሳት ከበራ በድርጊትም ሆነ በፋይዳ ከሰዎች የዕለት ተዕለት ህይወት የተለየና በውስጡ የሚደረጉት ድርጊቶች የተለየ ፋይዳና ትርጉም ኖሯቸው የሚከወኑ መሆናቸውን ይጠቁማል (2002፡ 738)፡፡ መመገብ፣ መልበስ፣ ንግግር፣ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ጉዳዮች የሰው ልጅ የእለት ተዕለትና የማይቋረጡ ተግባራት ቢሆኑም በከበራ ውስጥ ግን የተለየ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

Milton Cohen የWallaceን ሀሳብ ተንተርሶ የሚከተለውን ብያኔ ሰጥቷል፡- “Ritual is behavior; it is “religion in action”. It is personal and private behavior, as it is social.” (የገፅ ቁጥርና ዓመተምህረት አልተጠቀሰበትም) ይህን ብያኔ ወደ አማርኛ አቻው ሲተረጎም የሚከተለውን ይመስላል፡፡ “ከበራ ባሕርይ ነው፤ ሃይማኖት የሚተገበርበት፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለ የግለሰብና የግል ባሕርይ ነው፡፡” ከበራን ከበራ ከሚያሰኙት ጉዳዮች አንዱ ድግግሞሽ ነው፡፡ ድግግሙም ወቅትን ጠብቆ ተደግሞ በመከወን እና በአንድ የከበራ አውድ ላይ አንድን ድርጊት ወይም ንግግር ደጋግሞ ማቅረብን የሚገልፅ ነው፡፡ ተመሳሳይ አከዋወን በተደጋጋሚ ሲከወን የግለሰብ ብሎም የማህበረሰብ መለያ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳ ከዋኝ በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀያየር ቢችልም የክዋኔ ስርዓቱ ግን አንዴ በተፈጠረው እና በማህበረሰቡ ዘንድ በተለመደው መልኩ የሚቀጥል ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲደጋገም ባህሪ ይሆናል፡፡ በጥቅሱ ውስጥ የሰፈረውም ሃሳብ ይህንን የሚያመላክት ሲሆን Sims እና Stephens ባዘጋጁት መፅሃፋቸው ውስጥም ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ “… rituals are performances that are repeated and patterned and frequently include ceremonial symbols and actions’’ (2011፡ 98). በማለት ሃሳባቸውን አስፍረዋል፡፡ ይህ ሀሳብ በቀጥታ ወደ አማርኛ ቋንቋ ሲተረጎም “ከበራዎች የሚደጋገሙ፣ ቅደምተከተል ያላቸውና ተከታታይ የክብረ በዓል ትዕምርቶችን እና ድርጊቶችን ያካተቱ ክዋኔዎች ናቸው፡፡” የሚል ይሆናል፡፡ ይህም ብያኔ የከበራን ተደጋጋሚነት፣ በድርጊት የሚገለፁ ክንውኖች ያሉበት እንዲሁም ድርጊቶቹ ትዕምርታዊ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ከላይ ከተሰነዘሩት ብያኔዎች በመነሳት ከበራ ታስቦባቸው ተደጋግመው የሚከወኑና የግለሰብ ብሎም የማህበረሰብ ባሕርይን የሚያመላክቱ የክንውኖች ስብስብ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

### 3.1.3 የከበራ መገለጫዎች

Pascal Boyer እና Pierre Liénard የከበራን የሰው ልጅ ባህርይነት በጥልቀት ያሳዩ ሲሆን የከበራ አጠቃላይ መገለጫዎች ናቸው ያሏቸውን አምስት ነጥቦች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

**ሀ. አስገዳጅነት** /Compulsion/፡- ከበራ በተለመደበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር አንድ ሰው እንደሌሎቹ የማህበረሰቡ አባላት እርሱም እንዲያከብር ይገደዳል፡፡ የሚያስገድደው ከበራውን ባለመከወኑ ሊደርሱብኝ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸው ነገሮች በሚፈጥሩበት ስጋት ነው፡፡ ከስጋት ነፃ የሆነ ኑሮ ለመምራት ሌሎቹ የማህበረሰቡ አባላት የሚከውኗቸውን ከበራዎች መከወን እና ከማህበረሰቡ ጋር መመሳሰል ይኖርበታል፡፡

**ለ. ጥብቅነት /ኢ-ተለዋዋጭነት** /Rigidity, adherence to script/፡- ይኸኛው መገለጫ የሚያመለክተው ከበራ መከወን ያለበት ከዚህ በፊት ይከወን በነበረበት መንገድ ነው የሚለውን የሰዎች እሳቤ ነው፡፡ ቀድሞ ከነበረው የከበራ ስርዓት ማፈንገጥ አደገኛና ለመቅሰፍት ያጋልጣል የሚል እምነት በልቦናቸው ያሳድራሉ፡፡ ስለዚህ በፊት የነበረውን ሰርዓተ ክዋኔ ሳይለቁ አጥብቀው በመያዝ ከበራውን ያከናውናሉ፡፡ እነርሱም ለቀጣይ ከዋኞች ያንኑ የማይለዋወጥ ስርዓተ ክዋኔን ያስተላልፋሉ፡፡

ሐ. **ግብ ቅነሳ** /Goal-demotion/፡- በከበራ ክዋኔ ውስጥ የሚታዩት ድርጊቶች ከተለመደው የሰው ልጆች እንቅስቃሴ የተቀዱ ድርጊቶች ናቸው፡፡ የእነዚህ ተለምዷዊ ድርጊቶች በክዋኔው ውስጥ ተደጋግሞ መታየት የከበራውን ግብ ዝቅ ያደርጉታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በትክክል ግባቸው ያልተለዩ ስለሆኑ ወይም ግባቸው ስውር (ሰዎች በቀላሉ ሊረዱት የማይችሉት) በመሆኑ ነው፡፡

**መ. ውስጣዊ ድግግሞሽና አላስፈላጊ ድግግም** /internal repetition and redundancy/፡- ቀደም ባሉት ትርጓሜዎች ውስጥ ድግግሞሽ አንዱ የከበራ መለያው እንደሆነ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ከበራ አንድ ወቅት ላይ ወይም አንድ ጊዜ ብቻ ተከውኖ የሚያቆም አይደለም፡፡ የሰው ልጆች ባህርይ እንደመሆኑ መጠን እየተደጋገመ የሚከወንና ከአንዱ ትውልድ ወደሌላኛው የሚተላለፍ ነው፡፡ ይህ አንዱ የድግግም መልኩ ሲሆን በተጨማሪም በአብዛኛው በአንድ የከበራ ክዋኔ ውስጥ አንድ ድርጊት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም አባባል ተደጋግሞ ይቀርባል፡፡

**ሠ. የመልዕክት /የጭብጥ መገደብ**/A restricted range of themes/፡- በዚህ የከበራ መገለጫዎች በሰፈሩበት መጣጥፍ ውስጥ Dulaney & Fiske (1994)ን በመጥቀስ

እንደተገለፀው አብዛኞቹ ከበራዎች ትኩረታቸው ከእርኩሰት መንፃት፣ አደጋ መከለልና የመሳሰሉት ጉዳዮች ነው፡፡ የሚከወኑትም ከእነዚህ ነጥቦች ጋር በተያያዘ ልቦናንና አካልን ወይም ቁስን ከእርኩሰት ማንፃት ወይም ሊከሰት ከሚችል አደጋ መጠበቅ ነው (Boyer & Liénard፣ 2006፣4)፡፡

የከበራ አይነቶችና ዘውጎች እንዲሁም የአከባበር ሂደቶቻቸው በርካታ ቢሆኑም እነዚህ አምስት ነጥቦች በአብዛኛዎቹ ከበራዎች ላይ የሚታዩና የጋራ መገለጫዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በሚዳስሳቸው የከበራ አይነቶች ውስጥ እነዚህ መገለጫዎች የሚታዩ መሆን አለመሆናቸው በትንታኔው ውስጥ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

### 3.1.4 የከበራ አይነቶች

በአንዳንድ ድርሳናት ውስጥ የከበራ አይነቶች በአራት ተከፍለው ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህም ድርሳናት መካከል ለአብነት ያህል Living Folklore የተሰኘውን የSims እና Stephens መፅሀፍ መመልከት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል Catherine Bell መሰረታዊ የከበራ አይነቶች ናቸው በማለት የሚከተሉትን ስድስት ነጥቦች ከበርካታ ምሳሌዎች ጋር በጽሁፏ ውስጥ አብራርታለች፡፡ አያይዛም የከበራ ዓይነቶችን እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነና በርካታ አይነቶች እንዲሁም መገለጫዎች እንዳሏቸውም ጠቅሳለች፡፡

1. **የመሸጋገሪያ ከበራ** (Rites of Passage) ፦ ይህ የከበራ አይነት ሰዎች ከአንድ የማህበራዊ ህይወት ወይም ከአንድ የስነህይወት ደረጃ ወደ ሌላ ሲሸጋገሩ የሚያከብሯቸው የከበራ አይነቶች ሲሆኑ በውልደት፣ በልደት፣ በጋብቻና በሰርግ ላይ የሚከወኑ ናቸው፡፡ የህይወት ደረጃዎች መሸጋገሪያ በመሆኑም የህይወት ዑደት በመባል ይታወቃል፡፡ ሰዎች የነበሩበትን አንድ ደረጃ ጨርሰው ቀጣዩን አዲስ ደረጃ ሲጀምሩ የማህበረሰቡ ባህል በሚፈቅደው መልኩ አስፈላጊ የሆኑ ክዋኔዎች ይደረጋሉ፡፡
2. **ቀነ ቀመራዊ ከበራ** (Calendrical Rites)፦ በዚህ ስር የሚመደቡት ከበራዎች ከጊዜ ሽግግር ጋር የተያያዙ ወይም ከወቅት ጋር በተያያዘ የሚከወኑ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሽግግሮች መገለጫ ከብርሃን፣ ከአየር ንብረት፣ ከግብርና ሥራ እና ከሌሎች ወቅት ላይ የተመሰረቱ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለውጥ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ቀነ ቀመራዊ ከበራዎች ፀሐይን ወይም ጨረቃን የተከተሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፀሐይ ቀመርን የሚከተሉ ከበራዎች በየ ዓመቱ በተመሳሳይ ቀን የሚከሰቱና የሚከወኑ ናቸው፡፡ የጨረቃ ቀመርን የሚከተሉት ደግሞ ቋሚ የሆነ ቀን የሌላቸውና የጨረቃ መውጣትን (የጨረቃ ብርሃንን) ተከትለው የሚከበሩ ናቸው፡፡ ቀነ ቀመራዊ ከበራዎች ወቅታዊና

የመታሰቢያ በማለት በሁለት ጎራ ከፍሎ መመልከት ይቻላል። ወቅታዊው ወቅትን ጠብቀው በሚሰሩ ስራዎች (እርሻ፣ አጨዳ፣ ውቂያ ወዘተ.) ላይ የሚከበሩ ከበራዎችን የሚያካትቱ ሲሆኑ አንደየ አካባቢውና እንደየ አዝዕርቱ ዓይነት በሰብል መዝሪያና መሰብሰቢያ ወቅቶች የሚደረጉትን የተለያዩ የከበራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከት ነው። ሁለተኛው ጎራ የመታሰቢያ ከበራ ሲሆን ያለፉ ታሪካዊ ክስተቶችን ለማስታወስ የሚደረጉ ከበራዎችን የሚያካትቱ ናቸው።

3. **የልውውጥ እና የትስስር ከበራ** (Rites of Exchange and Communion)፡- በሰዎችና በመለኮታዊ ሀይል መካከል ያለው ግንኙነት የሚገለፅባቸውና የሚጠናከርባቸው የከበራ ዓይነቶች በዚህ ውስጥ ይመደባሉ። እነዚህ ሁለት አካላት (ሰዎችና መለኮታዊ ሀይል ያላቸው) እርስ በርሳቸው የሚለዋወጡት ነገር ይኖራቸዋል፤ ሰዎች ሲያመልኩ፣ መስዕዋት ሲያቀርቡ፣ ምስጋና ሲያቀርቡ፣ በፀሎት ሲተጉ ወዘተ. በምትኩ ከመለኮታዊ ሀይል የሚጠብቁትና የሚቀበሉት ነገር ይኖራቸዋል። ሰዎች ከመለኮታዊ ሀይል የሚፈልጉትን ነገር (ይቅርታ፣ ጥበቃ፣ ድህነት ወዘተ. ለማግኘት በሚያደርጓቸው የተለያዩ ክንውኖች በሁለቱ አካላት መካከል የጠበቀ ትስስርን ይፈጠራሉ። ነገር ግን ሁሉም ሰው ወይም ማህበረሰብ ለዚህ ተገዢ ነው ማለት አይደለም። ለአምላካቸው ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ ብቻ የተለያዩ ስጦታዎችን የሚሰጡም አምልኮ የሚፈፅሙ አሉ።

4. **የመከራ ጊዜ ከበራ** (Rites of Affliction)፡- ሰዎች በህይወት ዘመናቸው በሽታ፣ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ረሀብ እና ሌሎችም ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ የሆኑ በርካታ አስከፊ ነገሮች እንደ ግለሰብም እንደ ማህበረሰብም ይገጥሟቸዋል። እነዚህን መከራዎች ለማስወገድ፣ እርኩስ መንፈስን ለማስለቀቅ እና ከእርኩሰት ለመንፃት የሚከውኑ ከበራዎች የመከራ ጊዜ ወይም የመቅሰፍት ጊዜ ከበራዎች ይባላሉ። እንደየ ባህሉ የመከራ ወይም የመቅሰፍት ትርጓሜና አረዳድ ቢለያይም በባህሉ ውስጥ ከዚህ ወገን ለሚመደቡ ክስተቶች ማህበረሰቡ ቀድሞ ለመከላከል ወይም ምህረት ለማግኘት የተለያዩ ከበራዎችን ይከውናል። ምህረትን ለማግኘት ከሚደረጉት ነገሮች አንዱ ልቦናን ወይም አካልን ከእርኩሰት ማንፃት ነው። በዚህ የከበራ አይነት ውስጥ እሳትና ውሃ ዋነኛ እራስን ማንጫ ሲሆኑ እንደየባህሉ ሌሎች በርካታ ነገሮች ለዚህ ግልጋሎት ይውላሉ።

5. **ግብዣ፣ ፆምና ክብረ በዓል** (Feasting, Fasting, and Festivals)፡- ፆምና ግብዣ ሰዎች በሀይማኖታቸው ያላቸውን ቁርጠኝነትና ፅኑ ዕምነት የሚገልፁበት ከመሆኑም

ባለፈ እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅርና አንድነት የሚያንፀባርቁበትም ጭምር ነው። ይህንን ማህበራዊ አንድነት ይበልጥ የሚያጠናክሩት ደግሞ ከበራዎች ናቸው። በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ለማህበረሰቡ አባላት ወይም አባል ላልሆኑ እንግዶች በሚደረግ ግብዣ፣ ወቅትን ጠብቆ የሚደረግ በግለሰብ ወይም በማህበረሰብ ደረጃ እራስን ከምግብና አካልን ከሚያነቃቁ ነገሮች በመራቅ የሚደረግ አፅዋማት እንዲሁም ከሀይማኖት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እና በሀይማኖቱ ውስጥ የተከሰቱ አቢይ ክስተቶች በተከታዮቹ የሚታወሱባቸው ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት ሳይኖራቸው በማበረሰቡ ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች ተፈጥረው የሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይ የሚደረጉ ከበራዎች በዚህ ምድብ ስር ይካተታሉ።

6. **ፖለቲካዊ ከበራ** (Poletical Rites):- የዚህ አይነቶቹ ከበራዎች በተለያዩ ተቋማት የሚገኙ የስልጣን አይነቶችንና እርከኖችን ለመገንባት፣ ለማሳየትና ለማስተዋወቅ የሚደረጉ ናቸው። ከተራ የእሴትና መልዕክት መተላለፊያነትም ባለፈ በአስተዳዳሪውና በህዝቡ መካከል ያለውን መስተጋብር ተጨባጭ በሆነ መንገድ የሚቀርቡበት የከበራ አይነቶችን የያዘ ክፍል ነው። (1997፣ 93-137)

ቀደም ባሉት ብያኔዎች ውስጥ ከበራ የሰዎች ብሎም የማህበረሰብ ባህርይ እንደሆነ ለማሳየት ተሞክሯል። ባህሪ ደግሞ መገለጫው ብዙ እንደመሆኑ መጠን የከበራ መገለጫዎች በርካታ ናቸው። የመገለጫዎቹ መለያየትም ከበራ የተለያዩ ዘውጎች እንዲኖሩት ያደርጋል። የእነዚህ ስድስት ነጥቦች መዘርዘርም የዚህ ውጤት ሲሆን በየባህሉ ከዚህ የተለየ መገለጫ ያላቸውም የከበራ አይነቶችም ይኖራሉ።

## 3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ሀገረሰባዊ ዕምነትን በተመለከተ በተለያዩ አካባቢዎችና በሀገረሰባዊ ዕምነቶች ዙሪያ ከዚህ ጥናት የቀደሙ ሌሎች ጥናቶች ተሰርተዋል። እነዚህ ጥናቶች በአብዛኛው ለባችለር ዲግሪ እና ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጁ ሲሆኑ ሌሎቹ መጣጥፎች (articles) ናቸው።

በዚህ ክፍል ስር በተዛማጅ ፅሁፍነት እንዲቃኙ የመረጥኳቸው ከእኔ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ ብቻ የሚዛመዱ ፅሁፎች ሲሆኑ ሁሉም ዲማጾች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ ስር በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም በአማርኛ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ተመራቂ ተማሪዎች የተዘጋጁ ናቸው። እኔ ጥናቴን ባካሄድኩበት ንዑስ ወረዳ ላይ ሌሎች ጥናቶች ተሰርተው ከሆነም በአካባቢ በመዛመዳቸው ብቻ በተዛማጅ ፅሁፍነት

አልተጠቀምኩባቸውም፡፡ በዚህም መሰረት ይህ ጥናት በሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የተሰሩትን መጣጥፎችና ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች) የሚያትቱትን ጉዳይ እንደሚከተለው ቃኝቻቸዋለሁ፡፡ ቅኝቴንም ያደራጀሁት ጥናቶቹ በተዘጋጁበት የትምህርት ደረጃ በመከፋፈልና በተሰሩበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከቀረቡት በመጀመር ነው፡፡ መጣጥፎቹ ግን የተዘጋጁበት ጊዜ ያልተጠቀሰ በመሆኑ በታተሙበት ቅፅ (bulletin) ባላቸው ቅደምተከተል መሰረት ሰፍረዋል፡፡

ሀገረሰባዊ ዕምነትን ዋነኛ ጉዳያቸው አድርገው ከተዘጋጁት ፅሁፎች መካከል በቀዳሚነት በዚህ ጥናት ውስጥ የዳሰስኳቸው መጣጥፎች ናቸው፡፡ መጣጥፎቹ ሶስት ሲሆኑ በAddis Abeba University በተዘጋጀውና በAlula Pankhurst በድጋሚ ታድቶ በታተመው Ethnological Society Bulletin vol. I no. 1-10 & vol. II no. 1 የመጣጥፎች ስብስብ ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡

በስብስቡ ውስጥ ከተካተቱት የሀገረሰባዊ ዕምነትን ከተመለከቱ መጣጥፎች መካከል አንዱ *'Omens in Ethiopia'* በሚል ርዕስ በ Behailu Gebrehiwot የተዘጋጀው አንዱ ነው፡፡ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ከዚህ ቀደም በጌምድርና ሸዋ ተብለው ከሚጠሩት የኢትዮጵያ አካባቢዎች 183 ሀገረሰባዊ ዕምነት መገለጫ የሆኑ የአማርኛ አባባሎች ከእንግሊዘኛ አቻቸው ጋር ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ 183 አባባሎች መልካም፣ መጥፎ ፣ በሽታና መልካም ጤንነትን የሚገልፁ፣ ሞትን የሚመለከቱ፣ ድርቅን ወይም ዝናብን የሚጠቁሙ እንዲሁም አዝመራንና ከብትን የተመከለከቱ በሚሉ ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ የመጣጥፉ አዘጋጅ ለአባባሎቹ የሚሰጣቸው ትርጓሜ ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ በመጠቆም ፅሁፋቸውን ያጠቃላሉ (268 — 284)፡፡

በዚህ የመጣጥፎች ስብስብ ውስጥ ከተካተቱት ሀገረሰባዊ ዕምነትን ከተመለከቱ መጣጥፎች ውስጥ ሌላኛው *'GENBOT LEDÄTA'* በሚል ርዕስ በ Yoftahie Kebede የተሰናዳው ፅሁፍ ነው፡፡ በፅሁፉ ውስጥ የግንቦት ልደታን የተመለከቱ ጉዳዮች በጥልቀት የተዳሰሱ ሲሆን ከስያሜው ትርጓሜ ይጀምራል፡፡ ግንቦት ልደታ ቅድስት ማሪያም የተወለደችበት ቀን መሆኑን በመግለፅ በበጌምድር አካባቢ ለዘመናት ሲከበሩ ከቆዩ በዓላት መካከል አንዱ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ መጣጥፉ ግንቦት ልደታ ሀይማኖታዊ ፋይዳ ያለው መሆኑን በመጠቆም የአከባበር ስርዓተ ክዋኔው ተገልጧል፡፡ ምንም እንኳን ሃይማኖታዊ ፋይዳ ቢኖረውም ሁሉም ሰው እንደማይከውነውና ከባዕድ አምልኮ የሚፈርጁትም እንዳሉ መጣጥፉ ይጠቁማል፡፡

ሶስተኛው መጣጥፍ 'ATETE' ሲሆን የተዘጋጀውም በ Fiseha Hailemeskel ነው፡፡ አቴቴ በአማራው ማህበረሰብ ዘንድም ጭምር የሚከበር ቢሆንም መነሻው ግን ከደቡብ የ'ፓጋን' ዕምነት ተከታዮች እንደሆነ በመጥቀስ እንዴት መከበር እንደጀመረ መነሻ ታሪኩ ተጠቅሷል፡፡ የሀገረሰባዊ ዕምነቱን ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል እንዲሁም የሚያስፈልጉና የሚባሉ ጉዳዮች በፅሁፉ በጥልቀት ተዳስሰዋል፡፡ መጣጥፉ የአቴቴ አምልኮ በአሁኑ ወቅት በቄሶች (የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን) ተጽዕኖ፣ በህብረተሰቡ የዕውቀት አድማስ መስፋትና በዘመናዊ ትምህርት ዕድገት ምክንያት በፍጥነት እየጠፋ መሆኑን በመጥቀስ ያጠቃልላል፡፡

ሀገረሰባዊ ዕምነት የሚታመንበት አካል፣ የሚታመንበት ምክንያት እንዲሁም ዕምነቱ የሚካሄድበት ስርዓተ አምልኮ እንደየአካባቢው ወይም እንደየባህሉ ይለያያል፡፡ ከዚህም ዕሳቤ በመነሳት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን በማጥናት ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ማሟያነት የቀረቡ 4 ጥናቶችን ማግኘት ችያለሁ፡፡

ከእነዚህ ለድህረ ምረቃ ማሟያነት ከቀረቡት ጥናቶች መካከል የመጀመሪያው በ2005 ዓ.ም *'የበሪ ሀገረሰባዊ ዕምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ'* በሚል ርዕስ በኮማንደር መሀመድ የተዘጋጀው ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት በአሪ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከወነውን የበሪ ዕምነት ከከበራ (Ritual) ፅንሰ ሀሳብ አኳያ መመርመር ሲሆን በዕምነቱ ስር ያሉትን ባቢ፣ ሳድሚያዎችና አንጀት የማንበብ ስርዓት ምንነታቸውን እና ስርዓተ ክዋኔያቸውን እንዲሁም የክዋኔ ጊዜያቸውን ይገልፃል፡፡ የዕምነቶቹ ክዋኔ የሚደረገው እህል ሲዘራ፣ የሰብል ወረርሽኝ ሲከሰት፣ ምርት ሲሰበሰብ፣ አዲስ እህል ሲገባ (ሲቀመስ)፣ የበሪ መገለጫ ቀን፣ በወሊድ ጊዜ ብሎ በመከፋፈል በእያንዳንዱ ገጠመኝ ጊዜ የሚደረጉትን ነገሮች ጥናቱ በዝርዝር ያስዳስሳል፡፡ በአካባቢው ዕምነቶቹ የሚከበሩባቸው ሶስት ዋና ዋና ቦታዎች ሲኖሩ አካ፣ አብዳር (አድባር) እና ማል በመባል ይታወቃሉ፡፡ ጥናቱ የሀገረሰባዊ ስርዓተ ክዋኔና የክዋኔ መቼት ከማሳየት ባለፈም የዕምነቶቹን ስነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነምግባራዊ ፋይዳዎችን አሳይቷል፡፡

ሁለተኛው የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ማሟያ ጥናት በ2003 በግርማ ቡኬ ጨዳ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ዕምነት በሚል ርዕስ የተደረገው ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት በቡርጂ ልዩ ወረዳ ስር የሚገኙ ስምንት የ'ቢያ' አስተዳደር ስርዓት የሚከተሉትን ህዝቦች የአስተዳደር ስርዓታቸውንና አስተዳተሩን በተመለከተ የሚንፀባረቁትን ሀገረሰባዊ ዕምነዊ ድርጊቶችን ማሳየት ነው፡፡ የቡርጂ ህዝቦች በጎሳ፣ በሀግና በክልል አስተዳደራዊ ተቋማት

እንደሚመሩ በመጠቆም ለእነዚህም ሶስት ተቋማት መመስረት ምክንያትና አጋጣሚዎች ናቸው ተብለው የታሰቡ ነጥቦች የህብረተሰቡን አፈታሪክና ሌሎች መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ሀሳብ እንደተሠጠባቸው ጥናቱ ይጠቅሳል፡፡ በአስተዳደር ስርዓቱ ውስጥ የሉባ፣ የሀግ እና የዳይና የስልጣን እርከኖች በጥልቀት የተዳሰሱ ሲሆን የማህበረሰቡ አጠቃላይ አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሁም የመሪዎቹ አመዳደብና የስልጣን ሽግግር ምን እንደሚመስል በጥናቱ ተዳስሷል፡፡ በአካባቢው *'ጋን'* የተሰኘው ሀገረሰባዊ ዕምነት ለህብረተሰቡ ቀዳሚና ለሌሎች ዕምቶችም ፈር ቀዳጅ እንደነበረ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም 12 የጋን አይነቶች እንዳሉ በመጥቀስ የዕምነቱ ስርዓት ከባህላዊ አስተዳደር ስርዓቱ ጋር ያለውን ትስስር ጥናቱ ዳስሷል፡፡

ሌላው በተመሳሳይ የትምህር ደረጃ የተደረገው ጥናት በ2002 ዓ.ም በመኸር *'ወቅት የሚፈፀሙ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ፋይዳና የቃል ግጥሞች ትንተና'* በሚል በማሞ ተፈራ የተጠናው ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ በዳንግላ ወረዳና አካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች በመኸር ወቅት የሚያከናውኗቸውን ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መግለፅና በሚያዜሟቸው ቃል ግጥሞች ውስጥ የሚነሱትን አበይት ጭብጦች መተንተን ነው፡፡ በተጠቀሰው አካባቢ የሚከወኑትን ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ከእንስሳት፣ ከመከወኛ ቁሶች፣ ከስያሜ፣ ከሚበሉና ከሚጠጡ ነገሮች፣ ከተከለከሉ ነገሮች፣ ከአቅጣጫዎች፣ ከቁጥሮች ፣ ከሴቶች ጋር የተያያዙ እና ሌሎች በሚሉ ክፍሎች ከፋፍሎ አቅርቦታል፡፡ በጥናቱ ውስጥ በጥቅሉ 22 ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የተሰበሰቡ ሲሆን 15 ዕምነቶች ተመርጠው ገለፃና ትንተና እንደተደረገባቸው ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢው ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚያዜሟቸውን በርካታ ጉዳዮችን የተመለከቱ 152 የቃል ግጥሞችን በመሰብሰብና 46ቱን በመምረጥ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

በዚህ መርሃ ግብር ውስጥ ከዳሰስኳቸው አራተኛውና የመጨረሻው ጥናት በ2001 ዓ.ም *'ባህርዳር አካባቢ በወንዞች ዳር የሚፈፀሙ የአምልኮ ስርዓቶችና ክዋኔያቸው'* በሚል ርዕስ በሙሉቀን ዘውዱ የተዘጋጀው ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገው በባህርዳር አካባቢ በሚገኙት ጥቁሪት፣ ታንኳ በር፣ ባሩድና አባይ ከንፈሮ በተባሉት ወንዞች ዳርቻ የሚደረጉትን አምልኮዎች በመለየት ለምን፣ እንዴትና በማን እንደሚከወኑ መግለፅ ላይ ነው፡፡ በዚህም አምልኮዎቹን የሚከውኑት ሰዎች በአብዛኛው ከገጠሩ አካባቢ የሚመጡ ሲሆኑ እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲሁም ሰብላቸውንና ከብቶቻቸውን ከክፉ ነገር ለጠመበቅ ወይም ክፉ ነገር ሲደርስባቸው ከደረሰባቸው ነገር ለመውጣት በጥር ወር፣ በግንቦት ወር፣ በህዳርና ሰኔ ሚካኤል እንዲሁም ለዘመን መለወጫ በቋሚነት አምልኮ ይፈፅማሉ፡፡ በተጨማሪም ከነዚህ ቋሚ ጊዜያት

በተጨማሪ መሃን ስትወልድ፣ ዝናብ ሲጠፋ፣ ንብረት ሲጠፋ ወዘተ በተለያዩ ጊዜያት የወንዝ ዳር አምልኮ እንዲፈፅሙና አምልኮውንም የሚፈፅሙት መስዕዋት በማቅረብ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቅሷል። በጥናቱ ውስጥ የነጋዴ ማህበረሰብን የአምልኮ ስርዓትም ከሌሎቹ ለይቶ ተመልክቷል።

ሃገረሰባዊ ዕምነትን ጉዳያቸው አድርገው ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተሰሩ ሶስት ጥናቶችን ማግኘት እንደቻልኩ በቀደመው ክፍል ለመጥቀስ ሞክሪያለሁ። ከነዚህ ጥናቶች መካከል በ1996 ዓ.ም በነፃነት ሰጠኝ *"በደብረዘይት ከተማ በጎሬት ገበሬ ማህበር በ 'ወራአያና' ባልማ ውስጥ የሚከበሩት ዕምነታዊ ስርዓቶች ክዋኔ"* በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ነው። የጥናቱ ትኩረት የ‹ወራ አያና› ዕምነት ክዋኔን የጎዴት ገበሬ ማህበርን ተተኳሪ በማድረግ ማሳየት ነው። ከዕምነቱ ትርጓሜንና ታሪካዊ አመጣጥን ጨምሮ ክዋኔው የሚፈፀምበት ቦታ፣ የሚፈቀዱና የሚከለከሉ ነገሮች በጥናቱ ተዳስሰዋል። በዕምነቱ ስር የሚከወኑት የአመቺሳ/ማሳቀፍ/፣ ኛቲና ኩጻ አፍሪ ስርዓቶች የአከባበር ስርዓተ ክዋኔ እንዲሁም በክዋኔው ወቅት የሚኖሩትን ቃላዊ አባባሎችም (በጥናቱ አዘጋጅ አጠራር ዝየራ) በጥናቱ ተካተዋል።

ሌላው በቅድመ ምረቃ መርሀግብር የተዘጋጀው ጥናት በ1982 ዓ.ም *"የአቴቴዎች ፈጫሳ ክዋኔዎችና ስነቃላዊ ግጥሞች በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ"* በሚል ርዕስ በመኮንን ለገሰ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ከተዳሰሱት ጉዳዮች አንዱ የአቴቴ ምንነት ነው። አጥኚው ፍሰሀ ኃይለመስቀልን ጠቅሶ አቴቴ የተለያዩ መጠሪያዎች እንዳሏት አብራርቷል። በአማራው ነዋሪዎች ዘንድ አቴቴዎች በርካታ እንደሆኑና ማህበረሰቡ ስለ አቴቴዎቹ ርኩስነት ወይም ቅዱስነት ጥርት ያለ ግንዛቤ እንደሌለው በጥናቱ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ በጥናቱ የአቴቴ/ፈጫሳ አጀማመር፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚኖራቸው ተስተላልፎ፣ ዓላማቸው እና ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተዳሰሱ ሲሆን በተጨማሪም ከአምልኮው ጋር በተያያዘ የሚባሉ የቃል ግጥሞች ትንተና ተካቷል።

በሶስተኛነት በዚህ ጥናት የተቃኘው በ1973 ዓ.ም በመኮንን በቀለ *"በአማርኛ የሚነገሩ አምልኳዊ ዕምነቶች"* የሚል የተዘጋጀው ጥናት ነው። በጥናቱ ሰዎች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ውስጥ የሚናገሯቸውና የሚያምኑባቸው አባባሎች ተሰብስበው ትንታኔ ተደርጎባቸዋል።

እነዚህ ጥናቶች እኔ በጥናቴ ከተዳሰሰው ርዕስ ጉዳይ ጋር ተቀራራቢ ሀሳቦችን የሚያነሱ ናቸው። ይሁን እንጂ ጥናቴ ከእነዚህ ጥናቶች በርዕስ ጉዳይ የሚቀራረቡ ቢሆንም

የሚለይባቸው የተለያዩ ነጥቦች አሉት፡፡ ከሚለይባቸው ነጥቦች የመጀመሪያ የሆነው የተጠኚ አካባቢ ልዩነት ነው፡፡ ከመኮንን ለገሰ ጥናት በስተቀር ለመጀመሪያ ዲግሪም ሆነ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡትት ጥናቶች በእኔ ጥናት ተተኳሪ ከሆነው ከቀይት ንዑስ ወረዳ አካባቢ ውጪ ሲሆኑ በአዲስ አበባ፣ በደብረዘይት፣ በባህርዳር፣ በዳንግላ፣ በቡርጂ፣ በአሪና በሀረርጌ አካባቢዎች የተሰሩ በመሆናቸው በእኔ ጥናት ተተኳሪ ከሆነው አካባቢ ጋር በጣም የተራራቁ ናቸው፡፡ የመኮንን ለገሰ ጥናት በተተከኳሪ አካባቢና የሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ አቴቴን የተመለከተ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይበልጥ ይቀራረባል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ጥናቶች የተጠኑባቸው ጊዜያት የተራራቁ በመሆናቸውና የክዋኔ ልዩነት ስላላቸው ጥናቶቹን የተለያዩ ያደርጋቸዋል፡፡

ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ የስፋት (scope) ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከስፋት አንፃር ሲታይ በተለይም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ከተዘጋጁት ጥናቶች የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ጥናቶች አንዱን የዕምነት አይነት ብቻ በመውሰድ ከክዋኔ ጋር የተያያዙ ገፅታዎቹን በማሳየትና ከዕምነት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃላዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ ተነጣጥለው የተጠኑትን ጥናቶች በአንድ ላይ አሰባስቦ በማካተቱና በሌሎቹ ጥናቶች ያልተዳሰሱትን ጫት ቅቀላ፣ ቦረንትቻና ጭዳ የተሰኙትን ሀገረሰባዊ ዕምቶች አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ከእነዚህ ጥናቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

## 4. ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.1 በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና ስርዓተ ክዋኔያቸው

በዚህ ክፍል ስር ጫት መቀቀልን፣ ጭዳን፣ ቦረንትቻን፣ አድባርንና አቴቴን (ፈጫሳን) በተመለከተ በምልከታ እና በቃለ ምልልስ እንዲሁም በቡድን ውይይት ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች በመከፋፈል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በአካባቢው ሰውንና እንስሳትን ለደዌ ይዳርጋሉ ወይም ለሞት ያደርሳሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ስድስት ዋና ዋና መናፍስት አሉ፡፡ እነዚህም ጠቋር፣ አዳል ሞቴ፣ ወሰን ገፊ፣ አዳኝ ወርቁ፣ ብር አለንጋና ቸሩ በዶስ ናቸው፡፡ እነዚህ መናፍስት ቀደም ባሉት ጊዜያት እንደ አማልክት ይታዩ ስለነበረ ጌታዬ፣ አበባዬ፣ በላዬ ላይ ያደርከው አምላክና የአያት የቅድመ አያቴ አምላክ እያሉ ያሞካሿቸው ነበር (ከወ/ሮ እቴነሽ ባዩ ጋር በ30/03/2006 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የቤተክርስቲያን አስተምህሮት በፈጠረው ተፅዕኖ ምክንያት ጌታዬ ከማለት ይልቅ እርኩስ መንፈስ፣ ሰይጣን፣ ጋንጨር፣ አጋንንት፣ ምናምንቴ፣ ጋኔን፣ ዳቢሎስ በሚሉና በመሳሰሉት ስያሜዎች የሚጠሯቸው በርካቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስማቸውን ላለመጥራት እሱ ወይም እነርሱ በማለትም የሚጠቅሷቸው አሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መናፍስት በክፋት ተነሳስተው ጉዳት እንዳያደርሱ የአካባቢው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹን በመከወን ይለማመናቸዋል፤ የሚፈልጉትን ግብርም ያቀርብላቸዋል፡፡

#### 4.1.1 ጫት መቀቀል

የአካባቢው ማህበረሰብ አካላት በሚከተሉት ኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ውስጥ ካላቸው ዕምነት በተጨማሪም ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ከብቶቻቸውንና ቀዬያቸውን ከላይ በተጠቀሱት መናፍስት አማካኝነት ሊደርሱ ከሚችሉ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሚከላከሉባቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች አንዱ የጫት መቀቀል ስነ ስርዓት ነው፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት የጥናቱ ትኩረት በሆነው አካባቢ ጫት የመቀቀል ስነስርዓት የሚያከናውኑት በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም መነሻው ግን ይህ ሀይማኖት ሳይሆን ከእስልምና ሃይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑን ከሚገልፁ ተረኮች መካከል አንዱ የሚከተለው ነው፡፡

ነብዩ መሀመድና አባ ኖብዕ የተባሉ ሁለት የሀይማኖት ሰዎች በአንድ ዋሻ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ነብዩ መሀመድ በግራ አባ ኖብዕ ደግሞ በቀኝ በኩል ይኖሩ የነበረ ሲሆን በየሶስት ቀኑ ይገናኙም ነበር፡፡ ሁለቱም ለፈጣሪያቸው መስዕዋት ለማቅረብ በማሰብ አባ ኖብዕ ስንዴ ዘሩ፡፡ ስንዴው በደረሰም ጊዜ ከላይና ከታች ድንጋይ በማድረግ ፈጭተው ሶስት ጢቢኞችን ጋግረው አቀረቡ፡፡ ቅዱስ ገብርኤልም ጢቦኞቹን አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በመሰየም አሳረጋቸው፡፡ ነብዩ መሀመድም በበኩላቸው ቡና ፀሀይ ላይ በማስጣት አድርቀው በመፍጨት ሶስት ጊዜ አፈሉት፤ ከአንድ እስከ ሶስት ድረስ የተፈላውንም ቡና አቦል ጀባ፣ ቶና ጀባ፣ በረካ ጀባ ብለው ሰየሙት፡፡ ቅዱስ ገብርኤልም መጥቶ መስዕዋቱን ተመለከተላቸው፡፡

አንድ የታመመች/ያበደች በግ ነበረች፡፡ ይህቺ በግ በአካባቢው የነበረውን የጫት ቅጠል በበላች ጊዜ ከህመሟ ተፈወሰች፡፡ ከተፈወሰች በኋላ ወደ ነብዩ መሀመድ ዘንድ ሄደች፡፡ ነብዩ መሀመድም ይህንን በተመለከቱ ጊዜ ፈጣሪያቸው ሌሎች ድውያንን እንዲያድንላቸውና ስውራንን እንዲያበራላቸው በማሰብ በጓን አርደው በጓን ያዳነውን ጫትንም እንደቡናው ሶስት ጊዜ አፍልተው መስዕዋት አቀረቡ (ከመሪጌታ ይልማሸዋ ቃለ ምልልስ በ05/09/2006 ዓ.ም.)፡፡

ይህ አፈታሪክ ጫት መቀቀል እና ጭዳ እንዴት ተጀመረ ለሚለው ጥያቄ የአካባቢው ማህበረሰብ በተለይም ደግሞ በክርስትናው በኩል ያሉ ሰዎች ምላሽ የሚሰጡበት ነው፡፡ ከአፈታሪኩ እንደምንረዳው ጫት መቀቀል የተጀመረው በእስልምና ሃይማኖት ተከታይ በሆኑት በነብዩ መሀመድ ሲሆን ለመስዕዋትነት ተመርጦ የቀረበ እፅዋት ነው፡፡ ለመስዕዋትነት የመረጡትም ደዌን የመፈወስ አቅም ያለው ቅጠል መሆኑን በመገንዘባቸው ነው፡፡

ጫትን ከሌሎች ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ከተጠኑ ጥናቶች መካከል የ Ezekiel Gabissa እና የ Nardos Seifu ዲማፆች ይጠቀሳሉ፡፡ ሁለቱም ጥናቶች ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ነጥቦችን አንስተዋል፡፡ በEzekiel ጥናት ውስጥ በዋናነት የተነሳው የጫት ታሪክና ለሀገር ምጣኔ ሀብት ያለው አስተዋፅዖ ነው፡፡ አጥኚው ታሪኩን ሲዳስስ ጫት ከመካከለኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቀይ ባህር አካባቢ ለመድሃኒትነት እንዲሁም በሀይማኖታዊና በባህላዊ ከበራዎች ጠቀሜታ ላይ መዋል እንደጀመረ ይጠቁማል፡፡ በወቅቱ በካቡል እና በደቡባዊ አረብ አካባቢዎች በሻይና

በሌሎች የመጠጥ አይነቶች መልክ በማዘጋጀት ለመድሃኒትነት ይጠቀሙበት እንደነበረ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ጫት መቃም የተጀመረው በሙስሊም ኦሮሞዎች እንደሆነና ይቃም የነበረውም ለማህበራዊ፣ ለባህላዊና ለሃይማኖታዊ ግልጋሎት መሆኑን በጥናቱ አሳይቷል (1997፡73-85)፡፡

የNardos ጥናትም በበኩሉ ጫት በሰዎች ጤናና በሀገር ፀጥታ ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ መመርመር ዋና ጉዳዩ አድርጎ በሀገሪቱ ውስጥ ወንዶችም ሴቶችም ለማህበረ-ኢኮኖሚያዊና ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች እንደሚጠቀሙት ይጠቁማል (2013፡16)፡፡ በሁለቱም ጥናቶች ውስጥ እንደተንፀባረቀው የጫት ቅጠል በሰዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የዋለው ፈዋሽ ቅጠል መሆኑ በቤት እንስሳት (በተለይም ፍየል) የተረጋገጠ መሆኑን የሚያመላክቱ ተረኮችን ለማሳያነት ተጠቅሰዋል፡፡ ጫት የአደንዛዥ ዕፅነት ይዘት እንዳለውና በሰዎች ጤና ላይ ችግር እንደሚያስከትል በNardos ጥናት ውስጥ በስፋት ቢጠቀስም በእኔ የጥናት አካባቢ ግን ተዘውትሮ የማይወሰድና በፈዋሽነቱ ለሃይማኖታዊ ግልጋሎት ብቻ የሚውል ነው፡፡ ጫትን በመቀቀልና ፈሳሹን በመጠጣት ለዕምነታዊ ተግባር ከማዋል ባለፈ እንደ ዕፅ መቃም እንብዛም ተቀባይነት የለውም፡፡

አካባቢው ጫት የመቀቀል ስርዓት የሚከናወነው በመስከረም፣ በጥቅምት፣ በጥር፣ በሚያዚያና በሰኔ ወራት ሲሆን በስፋት የሚዘጋጀው ለመስቀል በዓልና ለፋሲካ በዓል (በመስከረምና በሚያዚያ) ነው፡፡ እኔ ምልከታዊ መረጃ የወሰድኩት ለፋሲካ በዓል ከተደረገው ከበራ ላይ ነው፡፡ ከበራው ለተከታታይ ሶስት ቀናት የሚቆይ ሲሆን ለበዓላቱ የሚቀቅል ሰው ከበራውን የሚጀመረው በዋዜማው ነው፡፡ የፋሲካ በዓል ምንጊዜም እሁድ ስለሚውል ቅዳሜ ተጥዶ ሰኞ ይጠረጋል፡፡ ነገር ግን ማክሰኞ ለመጥረግና እግረ መንገዳቸውን ጭዳ ለማድረግ ሲሉ በበዓሉ ዕለት (እሁድ) የሚጥዱ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ የበዓሉን ዋዜማ አሳልፎ መጣድ ከስርዓቱ ያፈነገጠና መሆን የሌለበት ነው (ከወ/ሮ እቴነሽ ባዩ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ 22/08/2006 ዓ.ም.)፡፡

ጫት የመቀቀል ሂደቱ የሚከናወነው ለዕምቶች መከወኛ በተለይም ደግሞ ለጫትና ለጭዳ መባያነት በተዘጋጀ አንድ አነስተኛ የሳር ጎጆ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ይህ ቤት ከዋኞቹ የዋና ቤታቸውን አቅጣጫ በመከተል የላይ ቤት፣ የታች ቤት ወይም ትንሿ ቤት በማለት የሚጠሩት ሲሆን አብዛኞቹ ቡና ቤት ይሉታል፡፡ ቤቱ አንድ ምሰሶ እንዲኖረው ተደርጎ በክብ ቅርፅ

ይሰራል፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚሰራው ለዕይታ እንብዛም ባልተጋለጠ መልኩ ከሌሎች ቤቶች ጀርባ ነው፡፡ የቤቱ ስፋት እንደየሰዎቹ ፍላጎት የሚለያይ ቢሆንም ከማምለኪያነት በስተቀር ለሌሎች ተግባራት ስለማይውል ሰፊ አይደረግም፡፡

ጫት ቅቀላን በተመለከተ ምልከታ ያደረኩበት በባሶ ደንጎራ ቀበሌ ውስጥ በተለምዶ አንሳስ በሚባለው አካባቢ የሚገኘው የአቶ ዘውዴ ቤት ሲሆን የሚከተለው መልክ አለው፡፡ የቤቱ የውስጥ ክፍል በግድግዳው ስር ዙሪያውን ለመቀመጫነት የሚያገለግል መደብ (ከድንጋይ፣ ከጭቃና ከእበት የሚሰራ መቀመጫ) አለው፡፡ መካከል ላይ የሚገኘው ምሰሶም እንዲሁ ለማጨሻ ማስቀመጫነትና ለሰንደል መሰኪያነት በሚያገለግል መደብ የተከበበ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለማብሰያ የሚሆን ምድጃ ከበሩ በስተግራ ይገኛል፡፡ በዙሪያውም መደብ የሚገኝ ሲሆን ለከዋኝ መቀመጫ በመሆን ያገለግላል፡፡ ከበሩ በስተግራ አነስተኛ ዘረንጋ (ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ መደርደሪያ) የሚገኝ ሲሆን በቤቱ ውስጥ ለሚደረጉት ክዋኔዎች የሚያገለግሉት ዕቃዎች የሚቀመጡበት ነው፡፡ እዚህ ቤት ውስጥ የሚያገለግሉት ቁሳቁሶች ለዘወትር አገልግሎት የማይውሉ ስለሆኑ ክዋኔው ከተጠናቀቀ በኋላ እስከቀጣዩ ክዋኔ ድረስ ዘረንጋው ላይ ተደርድረው ይቀመጣሉ፡፡

ቤቱ የቤተክርስቲያን ያህል ክብር ስለሚሰጠው በከበራ ወቅት ቤቱ ውስጥ ሲገባ ጫማ ተወልቆ ነው፡፡ ከተገባም በኋላ የመናፍስቱ ማደሪያ ነው ተብሎ የሚታመነው ምሰሶ ይሳማል፡፡ ይህም ክብርንና ምስጋናን ለመግለፅ የሚደረግ ሲሆን ሴቶች ንፁህ ካልሆኑ (የወር አበባ የሚያዩበት ወቅት ከሆነ) እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡

ይህ ቤት ከበዓሉ መዳረሻ ጀምሮ አስፈላጊው ፅዳት ይደረግለታል፤ በእበት (የቀንድ ከብቶች የሚፀዳዱት ቆሻሻ) መሬቱና ግድግዳው ይለቀለቃል፤ ለመስቀል በዓል የሚቀቅል ሰው ጊዜና ጉልበት ካለው ግድግዳውን ዙሪያውን ጭቁኝ የሚባል ነጭ አበባና አደይ አበባ በመለጠፍ እንዲሁም ቀይና ነጭ ብክካ አፈር በማቡካትና በመቀባት ያስውባል፡፡ ጫቱ የሚጣድበት ቀን አመሻሽ ላይ ፅዳት ሲደረግበት በከረመው የሳር ቤት ወለሉ እርጥብ ሳር ይጎዘጎዛል፤ መደቡም ድብዳብ ይነጠፍበታል፡፡ ቡና ቤቱ በዚህ መልኩ መዋቡ መናፍስቱን ደስ ያሰኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ለቤቱ የሚደረገው ተገቢ ዝግጅት ከተጠናነቀ በኋላ የጫት ቅቀላው ከበራ ይጀመራል፡፡ ሸንኮራ ተቀጥቅጦ ወይም ተከረታትፎ ለዚሁ በተዘጋጀው ባለስድስት ጡት ማሰሮ ውስጥ ተጨምሮ

የጫቱ ቅጠልና ተደርጎ ውሀ ይሞላና ይጣዳል፡፡ ሲጣድ ሁለት ጊዜ ጉልቻ እየነካው ይወርድና በሶስተኛው ይጣዳል፡፡ ከበራው በሶስተኛው ቀን እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተጣደው ጫት እሳትና ጥበቃ አይለየውም፡፡ እሳት የማይለየው የጫቱ መልክ ቀይ እስኪሆን ድረስ እንዲበስል ሲሆን በዚህ መልኩ መብሰሉ መድሀኒትነቱ እንዲጨምር ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ጥበቃ የሚደረግለት በሁለት ምክያቶች ሲሆን ጠባቂው የግድ ከዋኝ ሰው እንዲሆን አይገደድም፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ለመንፈሱ የሚሰጠውን ክብር ለመግለፅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ባዶ ቤት ትተውት ሄደው ሲመለሱ ይጣላቸዋል/ይለክፋቸዋል የሚል ዕምነት ስላለ ነው፡፡ የሚጠብቀውም ሰው ነቅቶ እንዲጠብቅ ይገደዳል፡፡ ድንገት እንቅልፍ ቢያሸልበው 'አጋንንት ይመታዋል'፤ ለአካላዊና ለስነልቦናዊ ጉዳቶች ይጋለጣል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ አዕምሮው የታወከ ሰው በአካል እንደሚያውቁ አቶ ዘውዴ ገልፀውልኛ፡፡

በዚህ መልኩ ሌሊቱን በሙሉ ጫቱ ከተቀቀለ በኂላ በማግስቱ ጠዋት ቡና ይዘጋጃል፡፡ ቡናው ፈልቶ ከመጠጣቱ በፊት አውዛ እየተባለ የሚጠራው የተቀቀለው ጫት ፈሳሽ በተለየ (ጡቶች ባሉት) ጀበና ይቀነስና ማር እየተጨመረበት በሲኒ እየተቀዳ የቤተሰቡ አባላት ይጠጡታል፡፡ ይህ ጫቱ በተጣደበት ማግስት ጠዋት ላይ የሚጠጣው አውዛ አቦል (አንደኛ) ይባላል፡፡ አውዛው መድሃኒት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የሚጠጣው በባዶ ሆድ ነው፡፡ በሚጠጣበት ወቅት ጠጪው ሰው ፊቱን ወደ ምስራቅ አቅጣጫ አዙሮ ቢያንስ ሶስት ሲኒ መጠጣት አለበት፡፡ ነፍሰጡር ሴት ከሆነች ግን ፅንሱን በቆሻሻ መልኩ ያስወግደዋል ተብሎ ስለሚታመን ብዙ እንድጠጣ አይመከርም፡፡ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የሚዞረው አንድም በሀይማኖቱ ቅዱስ መፅሃፍ ውስጥ የገነት መገኛ አቅጣጫ በመሆኑ በተጨማሪም በምፅዐት ጊዜ እግዚአብሄር ወደ ምድር የሚመጣው በምስራቅ በኩል ነው የሚለውን ዕምነት መነሻ በማድረግ ሲሆን ሁለትም አቅጣጫው የብርሀን መውጫ አቅጣጫ በመሆኑ የተስፋና የመልካም ነገር መሻትን ያመላክታል (ከመሪጌታ ይልማሸዋ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ 19/10/2006 ዓ.ም.)፡፡

አውዛው ከተጠጣ በኂላ የተፈላው ቡና ይጠጣል፡፡ ከተጋገሩት ሶስት አነስተኛ ድፎ ዳቦዎች ውስጥ አውዛው በሚጠጣበት ወቅት አንድ እየተቆረሰ በማር ተቀብቶ እየተበላ እንዲሁም የተለያዩ ጭሳጭሶችና ሰንደል ምሰሶው ስር እየተጨሰ ቡናው ይጠጣል፡፡ ጭሳጭሶቹ ድኝ፣ ከርቤ፣ ወይራ፣ የአደን እጣን የሚባሉ ሲሆኑ ለእያንዳንዱ የጭሳጭስ አይነት አንድ ማጨሻ በማድረግ ምሰሶው ስር ባለው መደብ ላይ ተደርገው ይጨሳሉ፡፡

አቦሉ በተጠጣ በኋላ ጫቱ ውሃ ተሞልቶበት ድጋሚ ይጣድና ሙሉ ቀን እሳት ሲነድበትና ሲጠበቅ ይውላል። በዚሁ ዕለት ማታ ላይ ደግሞ ቶናው (ሁለተኛው) አውዛ ይጠጣል። እንደ አቦሉ ሁሉ ቡናው ተፈልቶ ከመጠጣቱ በፊት አውዛ የሚጠጣ ሲሆን ሌሎቹ ክዋኔዎች ተመሳሳይ ናቸው። ብቸኛው ልዩነቱ አቦሉ በባዶ ሆድ ሲጠጣ ቶናው ምግብ ቢበላም የሚጠጣ መሆኑ ነው።

ሶስተኛው ቀን ጫት የመቀቀሉ ስርዓት የሚጠናቀቅበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ጠዋት በባዶ ሆድ በረካው (ሶስተኛው) አውዛ ይጠጣል። ከዚህ በኋላ የተቀቀለው የሽንኩራውና የጫቱ ገለባ በአሮጌ ዕቃ ላይ ተገልብጦ ሶስት ሪሚጦዎች፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣ ዳቦ፣ የተወቀጠ ኑግ፣ ማር፣ አረቄ፣ ትርንጎ፣ ብርቱካን እና ሌሎችም ቤት ያፈራቸው ወይም ከገበያ የተገዙ ጥራርሬዎችና ፍራፍሬዎች በአንድ ላይ ተደርገው ጫቱን ሲቀቅል የነበረው ሰው (እማወራ ወይም አባወራ) ከግቢ ውጪ ሰው የማይረግጥበት ቦታ ላይ ይጥላል። ይህ ሂደት ጠረጋ ይባላል። እነዚህ የተዘረዘሩት የምግብ አዝዕርቶች ለመናፍስቱ መገበሪያዎች ሲሆኑ አብረው የሚጣሉት ድርሻቸውን በመውሰዳቸው እና ሰዎች የቀመሱትን ሁሉ በመቅመሳቸው ቀሪው ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ለመከላከል ነው። በተለይም ትርንጎና ዳቦ ዋነኛ የመንፈሱ ምግቦች በመሆናቸው በዝግጅቱ ውስጥ አይቀሬ ናቸው።

በጠረጋው ወቅት ጥራጊውን ሊጥል የሚሄድ ሰው ሲሄድ ማጭድ፣ ቢለዋ ወይም ሌላ ብረት ነገር በእጁ መያዝ አለበት። ይህም የሚደረገው ርኩስ መንፈስ (ሰይጣን) እንዳይከተለው ማባረሪያ ነው ተብሎ ይታመናል። ወደቤት ሲመለስም ቤት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ቤት ባለ ሰው (ወንድም ሆነ ሴት) ሶስት ጊዜ ግንባሩን በውሀ መረጨትና እጁን በውሃ መታጠብ አለበት። መረጨቱና መታጠቡ ከእርኩስ መንፈስ ንክኪ እንደመንፃት ይቆጠራል። ሊጥል የሄደው ሰው እነዚህን ሂደቶች ጨርሶ ቤቱ ውስጥ ከተመለሰ በኋላ አቦሉና ቶናው ላይ የተደረጉት የቡና ከበራዎች ይቀጥላሉ (ከ11/08/2006-13/08/2006 ዓ.ም የተደረገ ምልከታ)።

የዚህ ሀገረሰባዊ ዕምነት ከዋኞች ውቃቢ ያለባቸው ወይም የሌለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ውቃቢ ያለባቸው ሰዎች ከሆኑ የሚመሩት በውቃቢው ፍላጎት መሰረት ነው። ውቃቢው እንዲደረግለት የሚፈልገውን ነገር ሁሉ የማድረግ እና የማይፈልገውን ነገር የማራቅ ግዴታ አለባቸው። ውቃቢ ኖሮባቸው ጫት የሚቀቅሉ ሰዎችም ሆኑ በዝግጅት ቤቱም የሚገቡ ሰዎች የምግብ ገደብ ሊኖርባቸው ይችላል። እንቁላል፣ የፍየል ስጋ፣ ያረሰ በሬ ስጋ፣ ዶሮ፣ ተልባ፣ ጎመን እና

ሌሎችም እንደ ውቃቢው ፍላጎት የሚከለከሉ የምግብ አይነቶችን የሚመገብ ሰው በከበራው ላይ እንዲሳተፍ አይፈቀድለትም፡፡ ከተሳተፈ ውቃቢው ተቆጥቶ ክፉ ነገር (መቅሰፍት) ሊያስከትልበት ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ መንፈሱን ስለሚያስቆጣውም በግብር ሰጪና ተቀባይ መካከል የሚኖረውን የመገናኘት ሂደትም እንደሚያውክ ይታሰባል (ከአቶ ዘውዴ አሰፋ ጋር በ12/08/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

በዕምነቱ ውስጥ በሶስት ቁጥር የሚወከሉ ብዙ ነገሮች ይስተዋላሉ፡፡ ማሰሮው ሶስት ጊዜ ጉልቻ እንዲነካው መደረጉ፣ ለሶስት ቀናት መጣዱ፣ ሶስት ሲኒ መጠጣቱ፣ ሶስት ሪሚጦዎች መጨመራቸው እና ሶስት ድፎዎች መጋገራቸው ነብዩ መሀመድ ጫቱን ሶስት ጊዜ ከመጣዳቸው እና አባ ኖብዕ ሶስት ጢቢኞችን ጋግረው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ከመሰየማቸው ጋር በተያያዘ እንደሆነ ይታመናል፡፡

### 4.1.2 ጭዳ

ጭዳ በአካባቢው የሚደረገው እንደሌሎቹ ዕምነቶች ሁሉ በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ የተጠቀሱት መናፍስት ሰውንና የቤት እንስሳቱን እንዳይተናኮሉ ነው፡፡ መናፍስቱ በቀዬው ተገኝተው የሚቀምሱት ነገር ካጡ እንስሳቱን እየገደሉ ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህ አለፍም ሲል ሰዎችን ይተናኮላሉ፡፡ ወቅቱን ጠብቆ እንደ ሰው አቅም የበግ ወይም የዶሮ ደም ከፈሰሰላቸው ግን ሳይተናኮሉ ደሙን ብቻ ቀምሰው ይሄዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

ስለ ጭዳ ለመገንዘብ ሁለት የተለያዩ ቤቶች ውስጥ ምልከታ አድርጊያሁ፡፡ ሁለቱም ስርዓተ ክዋኔያቸው ተመሳሳይ ቢሆንም ክዋኔዎቹ የተደረጉበት ቦታ በቡና ቤትና ከቡና ቤት ውጪ በመሆኑ ይለያያሉ፡፡ በቡና ቤት የተደረገው በጫት ቅቀላ ስር የጠቀስኩት መቼት በመሆኑ በድጋሚ አልገልፀውም፡፡ ሁለተኛውን ምልከታ ያደረኩበትን መቼት እንደሚከተለው በአጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ ይህ ቦታ ከመጀመሪያው ጋር በተመሳሳይ አካባቢ የሚገኘው የአቶ ብዙአየሁ ቤት ነው፡፡ ከበራው የተደረገበት ቤት ግቢው ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ቤቶች መካከል አንዱ የሆነው ለመመገቢያ፣ ለመኝታና ለእንግዳ መቀበያነት የሚጠቀሙበት ቆርቆሮ ቤት ነው፡፡ ጠቅላላ ስፋቱ በግምት 10 ሜትር በ12 ሜትር ይሆናል፡፡ መግቢያ በሩ በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ቤቱ ከዋናው ክፍል በተጨማሪ ወደውስጥ ሲገባ በስተግራ በኩል ለመኝታ ቤትነት የሚጠቀሙበት አንድ ክፍል ቤት አለው፡፡ በዋናው ክፍል ውስጥ ለእንግዳ መቀመጫ በግድግዳው ስር ከተቀመጡት ሁለት አግዳሚ ወንበሮች በተጨማሪ አንድ የእንጨት አልጋ ይገኛል፡፡ ከአልጋው ቀጥሎ ያለው ክፍት ቦታ ደግሞ ለቡና ማፍያነት የሚያገለግል ነው፡፡

የስርዓተ ክዋኔው የመጀመሪያ ተግባር ቤቱን በማፅዳት የመናፍስቱን ቀልብ እንዲስብ ማድረግ ነው፡፡ ቤቱ ተፀድቶ ቡናውና የሚታረደው በግ ወይም ዶሮ ከቀረበ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው የቤተሰቡን አባላት ማሰባሰብ እና ጭዳ የሚባልበት ቤት ውስጥ እንዲገኙ ማድረግ ነው፡፡ የቤተሰቡ አባላት ተሰብስበው ቡና ተፈልቶ ዳቦ በማርና ቂጣ በኑግ እየተበላ ቡናው ከተጠጣ በኋላ በጉ ወይም ዶሮው ይታረዳል፡፡ የዶሮው ወይም የበጉ ክፍል እንደማንኛውም ጊዜ በሚፈለገው መልኩ ተዘጋጅቶ ይበላል፡፡ ለጭዳ ከታረደው ስጋ ላይ ዘመድ ላልሆነ ሰው የማያስቀምሱና እነርሱም ቢሆኑ በርበሬ ሳያስነኩ በልተው የሚጨርሱ ከዋኞች አሉ (ከወ/ሮ እቴነሽ ጋር በ30/03/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡ ጫት የማይቀቅል ሰውም ቢሆን ከቡናው ጀምሮ ያለው ስነስርዓት ተመሳሳይ ነው፡፡ ዳቦ በኑግና በዳቦ የሚበላበት ምክንያት ኑግ መንፈሱ በጣም የሚፈልገው ስለሆነና የመንፈሱን ትኩረት የመሳብ አቅም ስላለው ወደሌላ ቦታ ሄዶ ጉዳት ሳያደርስ ከቀረበው ላይ ብቻ እንዲቀምስ ያደርገዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ለመንፈሱ ከደሙ ለማቅመስ ዶሮውን ወይም በጉን የሚባርከው ሰው ከባረከ በኋላ ከሁሉም በፊት ወደደጅ ወጥቶ በባረከበት ቢለዋ የበሩ ግራና ቀኝ ቋሚ ላይ ደሙን ማስነካት አለበት፡፡ የባረከው ሰው ቀድሞ ወደ ውጪ ሳይወጣ ቤቱ ውስጥ ያሉትም መውጣት የለባቸውም፤ ውጪ ያለ ሰውም መግባት የለበትም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ደንቃራ እንዳይገባ ነው፤ ደሙን ለመቅመስ የመጣው መንፈስ ስለሚረብሽ ጉዳት ይጥልበታል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በተለይም የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ጭዳ በማለት ሆነ ብለው ሰው ወይም እንስሳ ደንቃራ እንዲገባ ያደርጋሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት በጠንቋይ ወይም በመሪጌታ ትዕዛዝ ሲሆን ጭዳ ባሉበት ቀን ቤታቸው ድንገት የመጣ ሰው ደንቃራ እንዲገባ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤ ወይም እንደ ደም፣ ሪሚጦ፣ ኑግ፣ አተላ የመሳሰሉትን መንፈሱን የመጥራትና የመሰብሰብ አቅም ያላቸውን መገበሪያዎች አንድ ላይ በማድረግ ሰው ወይም እንስሳ በሚተላለፍበት መንገድ ላይ በመጣል ደንቃራ ይከታሉ፡፡ በእርዱ ወቅት ቤታቸው የሚመጣውና ለደንቃራ የሚዳረገው ሰው ማን ወይም ምን አይነት እንደሆነ በጠንቋዩ ወይም በመሪጌታው ሊነገራቸውም ይችላል፡፡ ደንቃራ በገባላቸው ጊዜ የእነሱ በሽታ ይለቃቸዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ደንቃራ የገባው ሰው ወይም እንስሳ ይታመማል፤ እስከሞትም ሊደርስ ይችላል (ከአቶ ብዟየሁ፣ ከአቶ ዘውዱና አቶ ከአዲሱ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ 23/08/2006 ዓ.ም.)፡፡

የቤቱ ምሰሶ ዋነኛ የመንፈስ ማደሪያ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ የጭዳ ስነስርዓቱ የሚፈፀመው በምሰሶው ስር ነው፡፡ ምሰሶው ማር፣ ቅቤና ደም ይቀባል፤ ሰንደልና እጣንም እስሩ

ይጨሳል፡፡ ይህም መንፈሱን እንደመንከባከብ የሚቆጠር ሲሆን ለመናፍስቱ የሚሰጥ ክብርን ከፍታ መግለጫም ነው፡፡ አንዳንድ ቤት ውስጥ ለጭዳ የቀረበው በግ ከሆነም ከታረደ በኋላ የበጉ ቀንድ ምሰሶው ላይ ታስሮ ለረጅም ጊዜ ይቆያል፡፡ ይህም እስከቀጣዩ የጭዳ ወቅት ድረስ የሚፈለገውን ጥበቃ በአስተማማኝ ሁኔታ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመጨማሪም ለመናፍስቱ ክብር ምን አይነት በግ ጭዳ እንዳሉ ማሳያም በመሆን ያገለግላል፡፡ ጭዳ ባዮቹ የቡና ቤት ከሌላቸው በምሰሶ ስር የሚደረጉት ክዋኔዎች ሲቀሩ ሌሎቹን ክዋኔዎች በተመሳሳይ መልኩ ይከውናሉ፡፡

የሚታረደውን በግ ወይም ዶሮ መልኮች (ቀለማት) የተመረጡ እና የቀለማቱ ምርጫም ጭዳ እንደሚደረግባቸው ወራት የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ቀለማት የሚለያዩት እንደመናፍስቱ ፍላጎት ስለሚለያይ ነው፡፡ የጥቁር ቡሃ በግ (ግንባሩ ነጭ ሆኖ ሌላው ሰውነቱ ሙሉ ጥቁር የሆነ) ጠቋር ለተባለው መንፈስ የሚሰጥ የግብር ቀለም ሲሆን ጥቁር በግ ደግሞ ለጭፍሮቹ የሚሰጥ ነው፡፡ ሌሎቹ ቀለማት ከጠቋር ውጪ ለሁሉም መናፍስ ይሆናል፡፡ መናፍስቱ የሚፈልጉት አይነት መልክ /ቀለም ያለው በግ ወይም ዶሮ ካልታረደ መስዕዋቱ ተቀባይነት ስለማይኖረው የቤት እንስሳት አይባረኩም፤ ለሞት ይዳረጋሉ፡፡ በተጨማሪም ለመስዕዋትነት የሚቀርበው ዶሮ ከሆነ ወንድና ኳንኪያ (ጭንቅላቱ ላይ የሚገኘው ላባ ያልለበሰ ክፍል) ዱልዱም መሆን አለበት፡፡ የሴት ፆታና ኳንኪያ ዝርዝር/ነጠላ ዶሮ ለግብርነት ስለማይሆኑ አይቀርቡም፡፡ ሁለቱም (ሴትና ኳንኪያው ዝርዝር ዶሮ) እርባናቢስ እና በረከት የማያስገኙ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በግ ከሆነ ደግሞ ፀጉሩ ያልተቆረጠና ያልተኮላሸ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ምክንያት መናፍስቱም ግብሩን አይቀበሉትም፡፡ ቆዳውም ለቡና ቤቱ መቀመጫ ምንጣፍ እንዲሆን ይደረጋል እንጂ ለሽያጭ አይቀርብም፡፡

የጭዳ ወራቱና የሚመርጡት የበግ ወይም የዶሮ ቀለም እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡-

- መስከረም፡- የጥቁር ቡሃ በግ (ግንባሩ ነጭ ሆኖ ሌላው ሰውነቱ ሙሉ ጥቁር የሆነ) ወይም ቀይ ዶሮ
- ጥቅምት፡- ነጭ ወይም አዳል በግ ወይም ነጭ ዶሮ
- ህዳር፡- ቀይ ወይም አዳል በግ ወይም ቀይ ዶሮ
- ታህሳስ፡- አይመርጥም
- ጥር፡- አራቱም እግሩ ነጭ የሆነ የጥቁር ቡሀ በግ ወይም ቀይ/ ገብስማ ዶሮ

- የካቲት፡- ቀይ ወይም አዳል በግ ወይም ቀይ ዶሮ
- መጋቢት፡- በአብዛኛው በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ለ55 ቀናት የሚቆይ የሁዳዴ ጾም የሚጀመርበት ወር ስለሆነ ጾሙ እስኪፈታ ድረስ ጭዳ አይባልም፡፡
- ሚያዚያ፡- ነጭ ወይም ቡሃ በግ ወይም ነጭ ዶሮ
- ግንቦት፡- ጥቁር በግ (ዶሮ በዚህ ወር ለጭዳ አይታረድም)
- ሀምሌ፡- ነጭ ዶሮ - በዚህ ወር ጭዳ የሚል ሰው በአዘቦት ቀናት ማክሰኞና ሀሙስን ጠብቆ ማድረግ የሚችል ሲሆን አቴቴ (ፈጫሳ) የሚያደርግ ሰው ከሆነ ግን ቀኑን ጠብቆ አቅም ካለው ቀይ ሴት በግ ማረድ ይችላል፡፡
- ነሐሴ፡- ነጭ በግ ወይም ነጭ ዶሮ

ጭዳ የሚባልበት ቋሚ ጊዜ ባይኖረውም አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ ጭዳ የሚለው በሚያዚያ ወር ነው፡፡ ነገር ግን በከብቶቹ ወይም በጤናው ላይ የተለየ ችግር ካለበት በጠንቋይ ወይም በደብተራ (ህጉን ያፈረሰ መሪጌታ) ትዕዛዝ በየወሩ ጭዳ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ጭዳ የሚሰጠው ማክሰኞ ወይም ሀሙስ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ሙሉ ቀናት ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሙሉ ቀናት በመሆናቸውም ግብሩን ያለምንም እንከን ለመንፈሱ ይደርሳል (ከአቶ ብዟየሁና ከወ/ሮ ሙላቷ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ 26/08/2006 ዓ.ም.)፡፡

### 4.1.3 አድባር

'አድባር ሃሳብህን ትሙላልህ'፣ 'አድባር ትከተልህ'፣ 'አድባር ትጠብቅህ' እያሉ በገጠሩ አካባቢ የሚገኙ የዕድሜ ባለፀጋዎች ሲመርቁ ይሰማል፡፡ ቃሉ ለብዙ ሰው እንግዳና ብዙም ትኩረት የማይሰጠው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ስርዓቱ በሚከወንበት ማህበረሰብ ውስጥ በሚኖርና ስርዓቱን በሚከተል የማህበረሰብ ክፍል ዘንድ ጠንካራ ዕምነት የሚገለፅበትና ትልቅ መንፈሳዊ ስንቅ ነው፡፡

**አድባር** ቃሉ የግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም ተራራማ ቦታን የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማሪያም የተወለደችበትን ቦታ የሚጠቁም ነው፡፡ ነገር ግን በመስክ ቆይታዬ ወቅት እንደተረዳሁት የአካባቢው ማህበረሰብ የሚረዳው አድባር ማለት የአንዲት ሴት መንፈስ ስያሜ እንደሆነ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላትም ይህንኑ እሳቤ በመደገፍ እንደሚከተለው ይተረጉመዋል፡-

1. ብዙን ጊዜ በሴት የምትጠራ የመንፈስ አይነት ወይም ቆሌ
2. የአካባቢው ቆሌ ወይም መንፈስ የሚኖርበት ነው በሚል ዕምነት ሰዎች ቅቤ በመቀባት፣ ቡና በማፍላት ወዘተ የሚያከብሩትና አምልኮ የሚያደርጉበት ዛፍ፣ ድንጋይ፣ ወዘተ ነው (1993፣464)፡፡

ምንም እንኳን ከነዚህ ትርጓሜዎች የቃሉ ፅንሰ ሃሳብ የተቀየረ መሆኑን መረዳት ቢቻልም ስለምንነቱ ለመገንዘብ የአካባቢው ማህበረሰብ በሚገለገልበት መልኩ መጠቀሙ የተሻለ ነው ብዬ ስለማስብ ማህበረሰቡ በተረዳበት መንገድ ለማንፀባረቅ እሞክራለሁ፡፡

አድባር በአንድ መንደር ውስጥ በተመረጠና በተከበረ ዛፍ ወይም ድንጋይ ስር ለአንዲት በሴት ፆታ ለምትታወቅ መንፈስ ክብር በየዓመቱ የመንደሩ ሰዎች ተሰብስበው የሚያከብሩት ሀገረሰባዊ ዕምነት ነው፡፡ በአካባቢው ጎልታ የምትታወቀው ሴቷ አድባር ብትሆንም በወንድ ፆታ የሚጠራ አድባርም አለ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ነገር ግን ወንዱ አድባር የሴቷ ያህል ፋይዳ ወይም መለኮታዊ ሀይል ስለሌለው ማህበረሰቡ አያመልከውም፤ አያከብረውምም፡፡ መኖሩንም የሚያምኑትም ጥቂት ሰዎች ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በዚህ ጥናት ውስጥ የሚዳሰሰው ሴቷን አድባር የተመለከተ ጉዳይ ብቻ ይሆናል፡፡

መንፈሷ ብቻ ሳትሆን ዕምነቱ የሚከበርበት ቦታም በዚሁ አድባር በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ የአድባሯ ከበራ እንደየ አካባቢው በድንጋይ ስር ወይም በዛፍ ስር ሊሆን ይችላል፡፡ በድንጋይ ስር ወይም በዛፍ ስር እንዲሆን የሚወስነው በመንደሩ በቅርበት የማይነቃነቅ ድንጋይ መኖር ወይም ለአድባርነት ተስማሚ የሆኑ የዛፍ አይነቶች (ግራር፣ አስታ፣ ሾላ፣ የሀበሻ ጥድ፣ ቀጋ፣ ኮሽም፣ ብሳና፣ ዋርካ ወዘተ) በአንድ ቦታ ላይ የመገኘት አጋጣሚ ነው፡፡ ባህር ዛፍና የኮሶ ዛፍ ለአድባርነት አይመረጡም፡፡ ምክንያቱም ኮሶ የሰይጣን ማረፊያ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ባህር ዛፍ ደግሞ መጤ በመሆኑና ለሌላ አገልግሎት የሚውል (ለገበያ የሚቀርብ) በመሆኑ ነው፡፡ ይበልጥ ተመራጭ የሚሆነው ከላይ ከተጠቀሱት የዛፍ አይነቶች (ከኮሶ እና ከባህር ዛፍ ውጪ) ተቀላቅለው የበቀሉበት ቦታ ነው (ከአቶ ዘውዴ አሰፋና ከወ/ሮ እቴነሽ ባዩ ጋር በተለያዩ ግዜያት የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡



ምስል 4፡- በድንጋይ ስር የሚከወን አድባር



ምስል 5፡- በዛፍ ስር የሚከወን አድባር

አድባሯ በድንጋይ ስር የምትከበር ትሁን በዛፍ ስር ተመላኪዋ (መንፈሷ) አንድ ስለሆነች የዕምነቱ ስርዓተ ክዋኔም ሆነ የሚሰጣት ክብር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ ለአድባርነት የተመረጠ ዛፍ ወይም ድንጋይ ያለበት ቦታ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ነው፡፡ ቦታውን ከመንከባከብ ውጪ ለግል ጥቅም ከዙሪያው እንጨት መልቀም፣ ሳር ማጨድ፣ ከብት ማሰማራት፣ ከእፅዋቱ ላይ መቀንጠስ ወይም ሌሎች በአድባሯ ስም ከየቤቱ መጥተው የተረሱ፣ የተቀመጡና የወዳደቁ ነገሮችን ከስሩ ማንሳት ክብሯን ከመቀነስም ባለፈ ለትልቅ መቅሰፍት ይዳርጋል ተብሎ ስለሚታን መነካት የለባቸውም፡፡

ምንጊዜም ከበራው የሚደረገው ግንቦት 1 ቀን ሲሆን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ድንግል ማሪያም የተወለደችበትን ቀን ለማሰብ የተጀመረ ነው፡፡ አድባር የሚደረግበት ዛፍ ወይም ድንጋይ የሚገኝበት ቦታ ከመንደሩ በአንፃራዊነት ከፍ ብሎ የሚገኝ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የድንግል ማሪያም ቤተሰቦች ይኖሩ ከነበረበት ቆላማ ስፍራ ሊባኖስ ወደሚባል ተራራማ (ደጋማ) ስፍራ መሰደዳቸውን መነሻ ያደረገ ሲሆን በዚሁ ደጋማ ስፍራ ስትወለድ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩትም ሰዎች ቤታቸው ያለውን የሚበላ ነገር ይዘው ወደተወለደችበት ስፍራ መሄዳቸውን ለማሰብ ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢም የሚገኙ

ሰዎች ተመሳሳይ ተግባርን ያከናውናሉ (ከሊቀ ህሩያን ሀ/ማርቆስ ዘለቀ ጋር በ11/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

የአድባርን አጠቃላይ ሁኔታ ለመረዳ በዕለቱ የተገኘሁት በባሶ ደንጎራ ቀበሌ ልዩ ስሙ ዋኒ ገደል በሚባለው አካባቢ በድንጋይ ስር የሚደረገው ከበራ ላይ ነው፡፡ የአድባሯ አካባቢ በርካታ ትልልቅ ድንጋዮች የሚገኙበትና አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከመንደሩ ከፍታ ያለው ቦታ ነው፡፡ ከድንጋዮቹ መካከል አንዱ የማይነቃነቅ ድንጋይ ተመርጦ በአድባርነት ያገለግላል፡፡ ቦታው ከፍታ ያለው በመሆኑ ከፍተኛ ንፋስ ያለበት ነው፡፡ ይህንን ለመቀነስ በዙሪያው በባህር ዛፎች የተተከሉበት በመሆኑ ለንፋስ መከላከያነት እና ለአድባሯ ቡና ማፍያ ማገዶ ለመልቀም ያገለግላል፡፡

ከምሽቱ 10:00 ሰዓት አካባቢ የዓመቱ ተረኛ አባወራ ሚስትና ልጆች ለአድባርነት ከተመረጠው ድንጋይ የተወሰነ ርቀት (በግምት 3 ሜ.) ላይ ለቡና ማፍያ የሚሆን እሳት የማያያዝና ቡና የማቀራረብ ስራ ይሰራሉ፡፡ የመንደሩ ሰዎችም ጭሱንና ሰው መኖሩን ተመልክተው በስፍራው ይሰበሰባሉ፡፡ በዚህ ዕለት አድባርን ለማክበር 24 ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡ በእለቱ ተሳታፊ ከነበሩት ውስጥ አንዱ የሆኑት አቶ ሀይሉ እሩፌ ይህ ቁጥር ቀደም ካሉት ጊዜያት ጋር ሲነፃፀር አናሳ እንደሆነና እርሳቸው ወጣት በነበሩበት ጊዜ ብዙ ሰዎች ተገኝተው በሬ ወይም ላም ታርዶ ይሸኙ እንደነበረ ገልፀውልኛ፡፡ ከእነዚህ 24 ሰዎች መካከል 18ቱ (10 ወንዶችና 8 ሴቶች) አባዎራዎችና እማወራዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 6ቱ ህፃናት ናቸው፡፡ ልጆችና ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው አይቀሩም፡፡ ምክንያቱም እነርሱም የአድባሯን በረከት ተቋዳሽ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ስርዓቱን ተረካቢና ለቀጣዩም አስተላላፊ በመሆናቸው ከመንደሩ ሰዎች ጋር በመሆን ከበራውን ይሳተፋሉ፤ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንም በማቀራረብ ስራ ያግዛሉ፡፡ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ከብቶችም በቅርብ ርቀት ይገኛሉ፡፡ ይህ የሚሆነው በሁለት ምክንያት ሲሆን አንደኛው ምክንያት የከብቶቹ ጠባቂዎች (እረኞች) አድባር ስለሚሳተፉ ሲሆን ሁለተኛው እነርሱም (ከብቶቹ) የአድባሯን በረከት እንዲያገኙ በሚል እሳቤ ነው፡፡

ጀርባን ወደ አድባሯ አዙሮ መቀመጥ እንደ ንቀት ስለሚቆጠር ሁሉም ሰዎች ፊታቸውን ወደ አድባሯና ወደ ቡናው በማዞር ለመቀመጥ አመቺ በሆነላቸው መልኩ ድንጋዮቹ ላይ ወይም ድንጋዮቹን ተደግፈው ከስር ባለው ሳር ላይ ይቀመጣሉ፡፡ በዕለቱ የነበሩትም ይሽንኑ በመከተል ሁሉም ፊታቸውን ወደ አድባሯ ለማዞር ያመቻቸው ዘንድ የፈረስ ኮቴ ቅርፅን ተከትለው ነው

የተቀመጡት። ሌላ ሰው ሲመጣ ቀድመዉ የተገኙት ሰዎች ክንብንባቸውን በማውለቅ ሰላምታ በማቅረብና የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክትን በመለዋወጥ ይቀበላሉ።

የአድባሩ ተሳታፊዎች ባወጡት የተራ ድልደላ መሰረት ተረኛው ሰው ከተሳታፊዎቹ ውስጥ ጥቂት ሰዎች በቦታው ከተገኙ በኂላ ለዕርድ ያቀረበውን ነጭ ወይም አዳል በግ ወይም ፍየል (መንፈሷ ሴት ስለሆነች ለዕርድ የምትቀርበው ሴት ብትሆን ይመረጣል) ያርድና ደሙ የአድባሯ ድንጋይ ላይ እንዲፈስ ያደርጋ። በዚህ መልኩ ለመንፈሷ ግብር ከተሰጠ በኂላ በጉ ተገፎ ጨጓራና ስጋ ይከተፋል። ሴቶች ቡናውን ሲያፈሉ ወንዶቹ ስጋውን በብረት ምጣድ ይጠብሱና የተሰበሰቡት ሰዎች እንዲበሉ ያደርጋሉ። ስጋው ከተረፈም አድባር በሚወጡት አባወራዎች ቁጥር ልክ ይከፋፈልና ከበረከቱ ወደ የቤታቸው ይዘው እንዲሄዱ ይሰጣቸዋል።

ወደ አድባር የሚወጡ ሰዎች በተለይ ደግሞ ሴቶቹ ባዶ እጃቸውን አይሄዱም። አቅማቸው በፈቀደ መጠን በቤታቸው ያለውን ወይም ለአድባር ብለው ያዘጋጁትን እንጀራ፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣ ዳቦ፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ቅቤ፣ እጣን፣ ሰንደል ይዘው ይመጣሉ። ምክንያቱም ይህ ሁሉ በእርሷ በረከት የተገኘ በመሆኑ በጋራ መቋደስ አለባቸው። ያመጡትን የሚበላና የሚጠጣ ነገር አንድ ሰው እንዲያከፋፍል በመምረጥ ለሚያከፋፍለው ሰው ያስረክባሉ። ከሚበላውና ከሚጠጣው ነገርም በተሳታዎቹ ከመቀመሱ በፊት ድርሻዋ እየተቆነጠረ ወደ አድባሯ ይፈነጠቃል (ይበተናል)። በመቀጠል አከፋፋዩ ሰው ከየቤቱ የመጣውን ነገር ለተሰበሰበው በሚያዳርስ መልኩ አከፋፍሎ እንዲታደል ያደርጋል።

ሴቶቹ ይዘው ከሚመጡት የሚበላና የሚጠጣ ነገር በተጨማሪም ለአድባሯ ክብር ቅቤና ጭሳጭስ (እጣንና ሰንደል) ይዘው ይመጣሉ፤ "እንኳን በሰላም አደረስሽን ለዓመቱም ከቁጥር ሳንጎድል እንደዚሁ እንድንሰባሰብ አብቂን" እያሉ ቅቤውን የአድባሯ ድንጋይ ላይ ይቀቡታል ሰንደልና እጣኑም እስኩ ያጨሱታል፤

ቀኑ የፆም ቀን ከሆነ እርድ የማይከናወን ሲሆን ተረኛው ሰው አቅም ከሌለውም እንዲያርድ አይገደድም፤ እንደሌሎቹ ተሳታፊዎች ሁሉ ቂጣ፣ ቆሎ፣ ጭሳጭስ፣ ቡናና የመሳሰሉትን ነገሮች የማቅረብ ግዴታ ግን አለበት። ይሁን እንጂ ከተሳታፊዎች መካከል ባለተራው ለዕርድ የሚሆን ነገር ባለማቅረቡ ከበራውን እንደአስተጓጎለ የሚቆጥሩት አሉ።

በተሰባሰቡበት አጋጣሚ የሚያነሷቸውን ማህበራዊ ጉዳዮች ሲጨርሱና ቡናው ሲከትም የከበራ ስነስርዓቱ መጠናቀቂያ ተቃረበ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረው ነገር ስለትና ምርቃት ነው፡፡ ከተሳታፊዎቹ መካከል ችግር የገጠማቸው ሰዎች ካሉ ለአድባሯ ችግራቸውን እንድትፈታላቸው በመማፀን ስለት ይሳላሉ፡፡ በመቀጠልም የከበራው ማጠናቀቂያ የሚሆነው የአባቶች እና የእናቶች ምርቃት ነው፤ ሶስት ትልልቅ ሰዎች በዕድሜ ቅደም ተከተላቸው መሰረት ይመርቃሉ፡፡

"በእንጀራ ላይ እንጀራ ትስጣችሁ አድባሯ ትጠብቅልን እኛንም እንደዚሁ ለመደበር ታብቃን፡፡"

"ሁላችንንም እንደዚሁ ታቆየን የተወለደውንም ታሳድግል፤ የተዘራውን ትባርክልን፤ ልጆቻችንንም የተማሩትን ለዕድገት ታድርግልን፤ ያልተማሩትን እንዲማሩ ታድርግልን፤ ለዓመቱ ደግሞ ታድርሰን፡፡"

"የቀዬዋ አድባር ከብቶቹንም ልጆቹንም እኛንም ሰብሉንም ትጠብቅልን፤ ዝናብም ፀሐይም ይሁነን፤ ላሞች ይውለዱ፤ የተወለዱት ይደጉ፤ ጤና ትስጠን፡፡" እያሉ ተራ በተራ ይመርቃሉ፡፡

ከሽማግሌዎች ምርቃት በኋላ 'አሜን' በማለት ከበራውን በማጠናቀቅ ወደየቤታቸው ይበታተናሉ (በ01/09/2006 ዓ.ም ምልከታ፣ ባሶ ደንጎራ ቀበሌ)፡፡

አብዛኛው የከበራ ስነስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ የደረስኩበት ሁለተኛ ምልከታዬም መተመሳሳይ ቀበሌ ውስጥ ልዩ ስሙ አንሳስ የሚባል አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ከበራ ላይ ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ ከድንጋይ ስሯ አድባር ጋር ተመሳሳይ ነገር ነው የተመለከትኩት፡፡ በሁለቱ የአድባር ከበራዎች ላይ ያለው ልዩነት ሁለተኛ በዛፍ ስር የሚደረግ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ የዛፍ ስር አድባሯ ያለችበት አካባቢ ከመንደሩ ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን የተለያዩ የዛፍ አይነቶች በአንድ ላይ የበቀሉበትና በአንድ በኩል ጎንበስ ተብሎ የሚገባበት በመግቢያ ያለው ነው፡፡ ወደ ውስጥ ስፋት የሌለው በመሆኑ በመግቢያ ገብተው ውስጥ ሚቀመጡት ቡና የሚያፈሉትና ምግብ የሚያከፋፍሉት ሰዎች ናቸው፡፡ በዚህ አድባር የተሳተፉት 11 ሰዎች ሲሆኑ 7 ሴቶችና 4 ወንዶች ነበሩ፡፡ ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መሄዱን በዚህም የሚገኙ ተሳታፊዎች ገልፀውልኛል፡፡

እንደነርሱ ዕምነት አድባር ለችግራቸው አንዷ መፍትሄ ሰጪ በመሆኗ ችግራቸውን ለአድባሯ ነግረው እንድትፈታላቸው ይማፀናሉ፡፡ ከተፈታላቸው ስጦታ (ስለት) እንደሚያቀርቡም ቃል ይገባሉ፡፡ ስለት የሰመረለት (ችግር ደርሶበት ለአድባሯ ተስሎ ችግሩ የተቀረፈለት) ሰውም ካለ

የተሳለውን (ቃል የገባውን) ነገር በዕለቱ ይዞ በመቅረብ ለተሰበሰበው ተሳታፊ እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡ ቀጣዮቹ ጥቅሶችም ለዚህ ሃሳብ ማስረጃ ይሆናሉ፡፡

> አድባር ሁሉንም ችግር ሰሚ ነች፡፡ የተቸገረ ሰው እንደታቦት ይሳላታል፡፡ እኔም ያመኝ ነበር፡፡ በየ 15 ቀኑ ክፉኛ ያመኝ ስለነበረ እንደሰው አድርገሽ እወሩ ካደረስሽኝ አንድ ጠርሙስ አረቄ አድላለሁ ብዬ ተሳልኳት፡፡ ስለቴን ሰምታ ወሩን ሙሉ ምንም ስላላመመኝ ስለቴን አስገባሁ፡፡ እያደር ጭርሱኑ እየተወኝ ስለመጣ ሶስት ጊዜ በግ አርጃለሁ ዳቦም ደፍቼ ወስጄ አብልቻለሁ፡፡ ሌሎችም ሰዎች እንዲሁ እየተሳሉ ስለታቸውን ስትሰማቸው በግም ሌላም ብርም ያመጡ ነበር፤ አንዳንዴ እስከ አራት በግ ድረስ ይታረዳል፤ በስለት የገባ (ከወ/ሮ አፀደ ኪዳኔ ጋር በ08/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

> አድባራችን ሰሚ ሰሚ ነች! የነገሯትን ችግር አትዘነጋም፡፡ ላሜ አልታለብ ብላ ነበር፤ ወተት አልወጣ እያላት፡፡ ለአድባሯ ላሜ ከታለበች ከቅቤው አምጥቼ እቀባሻለሁ አልኳት፡፡ እሷም ሳትረሳኝ የጠየኳትን ፈጠመችልኝ እኔም ቅቤዋን አምጥቼ ቀብቻታለሁ፡፡ ችግር ሲገጥመኝ እሷኑ ነው የማዋየው፤ ስለምትሰማኝ እኔም አምንባታለሁ፡፡ ይኸው ስንት አመቴ ስማጠናት! (ከወ/ሮ ተኛኜ ሀይሉ ጋር በ12/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)

አድባር ችግር እንዳይደርስባቸው ቀድመው የሚከላከሉበት ዕምነታዊ ድርጊታቸው ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ከአቅማቸው በላይ የሆነ (የልዕለ ሰብዕ ዕርዳታን የሚጠይቅ) ችግር ሲገጥማቸውም ምህረት እንዲወርድ የሚለማመኑበት መድረክም ጭምር ነው፡፡ የሰብል ወይም የእንስሳት ወረርሽኝ ቢከሰት መፍትሄ ፍለጋ ከሚሄዱበት ቦታ አንዱ አድባር ነው፡፡ የአድባሩ ከበራ በሚጠይቀው መልኩ የሚያስፈልገውን ነገር አሟልተው ስሩ ተሰብስበው በቀዬው ምህረት እንዲወርድ ይማፀናሉ፡፡ ችግር በተከሰተ ጊዜ የሚደረገው የአድባር ስርዓተ ክዋኔ ከመደበኛው የሚለየው ከሚቀርቡት ምግቦች መካከል ቆሎ አለመካተቱ ነው፤ በቆሎ ምትክ የሚቀርበው ንፍሮ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትርጓሜው ቆሎ ከንፍሮ አንፃር ሲታይ ጠንከር ስለሚል ለማድቀቅ አቅም ይጠይቃል፡፡ መከራ በዝቶብን አቅም ነስቶናል፡፡ በመሆኑም ችግራችንን እንደቆሎ የምናደቅበትና የምንላቀቅበት አቅም አጥተናል እንደማለት ነው (ከወ/ሮ እቴነሽና አቶ ከአዲሱ ጋር በ13/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

ተሳታፊዎቹ እንደሚገልፁት አድባር ልጆቻቸውና ከብቶቻቸው ክፉ ነገር እንዳይደርስባቸው መስዕዋት የሚያቀርቡበት ብቻ አይደለም፤ ተገናኝተው የሚጠያየቁበት፣ ለጋራ ችግሮቻቸው መፍትሄዎች የሚያፈላልጉበት እንዲሁም የተጣላ የሚያስታርቁበት ማህበራዊ መድረካቸውም ጭምር ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ በግብርና ስራ የሚተዳደር በመሆኑ በየጊዜው ለመገናኘት እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ሰፊ ጊዜ የለውም፡፡ በመሆኑም ለግልም ሆነ ለጋራ ጉዳዮች መፍትሄ በጋራ ለመፈለግ የዚህ አይነት ማህበራዊ አጋጣሚዎች ወሳኝ ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ የተጣላን ሰው ለማስታረቅ ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ተጣልቶ አንድ አድባር ስር መሰብሰብም ሆነ በዚህ ቦታ የተጀመረን ሽምግልና አልቀበልም ማለት አድባሯን ያስቆጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ የተጣላ ሰው ያለው አማራጭ በአድባሯ ፊት መታረቅ ወይም አድባር አለመውጣት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ከአድባሯ በረከት መራቅ ስለሆነ እንደ ትልቅ ቅጣት የሚቆጠር ነው፡፡ (በ05/09/2006 ዓ.ም የቡድን ውይይት፣ ባሶ ደንጎራ)

### 4.1.4 ቦረንትቻ

ቦረንትቻ ግንቦት ወር ከገባበት ቀን ጀምሮ ወሩ እስኪጠናቀቅ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ማክሰኞ፣ ሀሙስና ቅዳሜ ቀናትን በመጠበቅ የሚከወን ሀገረሰባዊ ዕምነት ነው፡፡ ዕምነቱ ጠቋር በተባለ መንፈስ ለሚታዘዙ 'ቦረን'ና 'ትቻ' ለተባሉ አባትና ልጅ ጭፍራ መናፍስት የሚቀርብ ግብር ሲሆን ቦረን ልጅ ትቻ ደግሞ አባት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ 'ቦረንትቻ' የሚለውም ስያሜ ከነዚሁ ሁለት መናፍስት ስያሜ የተወሰደ ነው፡፡ እነዚህ እርኩስ መናፍስት ከብትን ብቻ የሚተናኮሉ ናቸው፡፡ ከብቶች እንዳይሞቱና እንዲረቡ እንዲሁም ጤነኛ እንዲሆኑ ለማድረግ በግንቦት ወር ጥቁር በግ ይታረዳል፡፡

ለግብሩ የሚያስፈልጉት ጥቁር በግ (አቅሙ ለፈቀደለት ሰው)፣ ድፎ ዳቦ፣ ቂጣ፣ የሽንብራ ቆሎ፣ በሶ፣ የስንዴ ቆሎ፣ የጠመዥ ቆሎ፣ የተወቀጠ ኑግ፣ ጉሽ ጠላ (ያልፈላ ጠላ) እና ብትን በርበሬ ናቸው፡፡ እነዚህ ዝርዝሮች የአካባቢው ማህበረሰብ በዋናነት የሚመገባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ መናፍስቱም ሰዎቹ ከሚመገቧቸው ነገሮች ማግኘት ስላለባቸው እነዚህ ነገሮች በአግባቡ ተሰናድተው ለከበራው ይቀርባሉ፡፡

ቦረንትቻ የሚከበረው ከቤት ውጪ በከብቶች በረት አካባቢ ስለሚደረግ አስፈላጊው ዝግጅትም የሚደረገው በዚሁ ቦታ መሆኑን ምልከታ ባደረኩባቸው ሶስት ከበራዎች መረዳት ችያለሁ፡፡

ቦታው ከተጠረገና ቁጤማ ከተጎዘጎዘበት በኋላ ከላይ ቡናና የተጠቀሱት አስፈላጊ ነገሮች ይቀራርባሉ፡፡ ለሰዎች መቀመጫ የሚሆኑ መቀመጫዎች በክብ ቅርፅ ይዘጋጃሉ፡፡ ለቡና ማፍያና ለስጋ መጥበሻ የሚሆን ጊዜያዊ ምድጃ ይዘጋጃል፡፡

በረንትቻ እርድ በማድረግ (ደም በማፍሰስ)ና ያለ እርድ ሊከናወን የሚችል ሲሆን ስነስርዓቱ የሚከናወነው ከብቶች ወደበረት ከገቡ በኋላ ነው፡፡ እርድ የሚያከናውን ሰው ቤቱ ውስጥ ጥቁር በግ ከተወለደ ከቤት ካልተወለደ ደግሞ ከገበያ ገዝቶ ያርዳል፡፡ የእርድ ስነስርዓቱ ከመከናወኑ በፊት አባወራው በጉን ተሸክሞ ሶስት ጊዜ ቤቱን ይዞራል፡፡ ይህም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ታቦት ወደማደሪያው ከመግባቱ በፊት በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ሶስት ጊዜ መዞሩን ተምሳሌት ያደረገ ነው፡፡ በመቀጠልም በጉ ከብቶች በረት አካባቢ ታርዶ ስጋው ውጪ በብረት ምጣድ ተጠብሶ ውጪ ይበላል፡፡ ውጪ የሚጠበሰው መናፍስቱ የስጋው ሽታ እንዲደርሳቸው በማሰብ ነው (ከአቶ ገብረመስቀል ገ/ጊዮርጊስና ከአቶ እሸቴ ነጋሽ ጋር በ11/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡ ከታረደው በግና ቤት ውስጥ ተዘጋጅተው ከቀረቡት የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮች በተጨማሪም ቡና ተፈልቶ ይጠጣል፡፡ ቡናው እንደየሰው ፍላጎት ቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጪ ሊፈላና ሊጠጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ውጪ ማፍላቱ የሚመረጥ ሲሆን ቡና የማፍላቱም ስነስርዓት ከወትሮው በተለየ መልኩ ቁጤማ ተጎዝጉዞ፣ ሰንደልና ዕጣን እየተጨሰ የሚደረግ ይሆናል፡፡

ለሰዎች ምግብነት የተዘጋጁት ነገሮች ሁሉ ከመቀመሳቸው በፊት ከሁሉም ነገር ትንሽ ትንሽ ተቆንጥሮ ለግብር ከተዘጋጁት (የተቆላ ድፍን ምስር፣ ሶስት ሪሚጦ፣ ጓያ፣ ጉሽ ጠላ) ጋር ለማባያነት ተጨምረው እንዲሁም ከሁሉም የበጉ ብልቶች ተቀንጥቦ በአሮጌ ዕቃ ወይም ገል (የሸክላ ስባሪ) ተደርጎ ፉካ (በከብቶች በረት ቆሻሻ ማስወገጃ አነስተኛ መስኮት) አካባቢ ይደረጋል፡፡ ይህም ከቦታው የማይነሳ ሲሆን የሚደረገው መናፍስቱ ወደ ከብቶቹ በረት በተጠጉ ጊዜ የሚቀምሱት ነገር ካገኙ ከብቶቹን አይተናኮሉም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ካልተቀመጠላቸው ግን ወደከብቶቹ በረት ዘልቀው በመግባት ከብቶቹን ለሞት ሊዳርጉ፣ አካለ ስንኩል ሆነው አገልግሎት እንዳይሰጡ ሊያደርጉ፣ አመለኛ እንዲሆኑ ሊያነሳሱ ወይም እንዳይራቡ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በፉካው በኩል የሚደረግው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ መናፍስቱ የሰው እንቅስቃሴ በሚበዛበት አካባቢ አይገኙም፡፡ ስለዚህ በበር ከመግባት ይልቅ ሰው እንብዛም በማይንቀሳቀስበት ሰዋራ ስፍራ በመግባት ያጠቃሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ፉካም ቆሻሻ የሚወገድበት በመሆኑ የሰው እንቅስቃሴ በማይበዛበት በኩል ነው የሚሰራው፡፡ ሁለተኛ

መናፍስቱ ከንፁህ ስፍራ በይበልጥ አመድ፣ አተላ፣ ፈርስና እበት የመሳሰሉ ቆሻሻዎች የሚጣሉበትን ስፍራ ይመርጣሉ፡፡ ፉካ ስር መደረጉም ለሁለቱም ምክንያቶች አመቺ ስፍራ ስለሆነ እንዲሁም ወደ እንስሳቱ ብዙም ሳይቀርብ መገኛው ስፍራ ድረስ ወስዶ እንደመስጠት ስለሚቆጠር ነው፡፡

በረንትቻው ያለ እርድ የሚከናወንም ቢሆን ስርዓተ ክዋኔው በተመሳሳይ ነው፡፡ በግ ሲቀር ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ተሟልተው ቡና ከቤት ውጪ (ግቢ ውስጥ) ተፈልቶ ቤተሰብ ተሰብስቦ አስፈላጊም ከሆነ ጎረቤትና ወዳጅ ዘመድ ተጠርቶ ይበላል፤ ይጠጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ቡና ውጪ ማፍላት ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም በግ ባለመታረዱ ውጪ የሚጠባበስና የሚሸተት ነገር ባለመኖሩ ቢያንስ የቡና ሽታ እንዲደርሰውና ለክብሩ የሚገባው ነገር በተገኘው አቅም ልክ እንደተደረገ ለማመላከት ነው፡፡

### 4.1.5 አቴቴ (ፊጪሳ)

በዚህ ጥናት ከተካተቱት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች መካከል አምስተኛውና በመከወኛ ጊዜው የመጨረሻ የሆነው ሀገረሰባዊ ዕምነት አቴቴ (ፊጪሳ) ነው፡፡ አቴቴ በሴቶች የምትከወንና በሴት ዖታ የምትጠራ መንፈስ ስትሆን የተለየ ስርዓተ ክዋኔ ያላት ነች፡፡ አቴቴ የመንፈሷ ስያሜ ነው፤ የከበራ ሂደቱ ደግሞ ፊጪሳ ይባላል፡፡ 'አቴቴ' ቃሉ የኦሮሞኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም ጠባቂ/አዳኝ እንደማለት ነው (ደስታ ተክለወልድ: 1970፡605)፡፡

መኮንን ለገሰ አቴቴን በተመለከበተ በተጉለትና በቡልጋ አውራጃ በሰራው ጥናት ውስጥ ፍሰኃ ኃ/መስቀልን (1975) ጠቅሶ አቴቴ ሐራ፣ አቴቴ ግንቢ፣ አቴቴ ዱላ፣ አቴቴ ዱበራ፣ አቴቴ በረና፣ አቴቴ ወርቄና አቴቴ ጉራጌ የሚባሉ ሰባት ራሳቸውን የቻሉ የአቴቴ መናፍስት እንዳሉ በመግለፅ በእርሱ ጥናት አካባቢ ግን አቴቴ ሀራ፣ አቴቴ ግንቢ፣ አቴቴ ዱላና አቴቴ ወርቄ የሚባሉት ብቻ እንደሚታወቅ ጠቁሟል (1982፡ 8)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪው አካባቢ ግን አቴቴ በመንፈስ አንድ ስትሆን ሶስት መጠሪያ ስሞች አሏት፡፡ ይህ የሚያሳየው እንደየ ማህበረሰቡ አረዳድ በየአካባቢው የሚኖሩት አቴቴዎች በስያሜም በቁጥርም ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

የአቴቴን ከበራ አጀማመር በተመለከተ የተለያዩ ምንጮች የተለዩዩ ነጥቦችን ያነሳሉ፡፡ ለአብነት ያህል ደስታ ተክለወልድ ባዘጋጁት መዝገበ ቃላት ውስጥ 'ጨሌ' የሚለውን ቃል ሲፈቱ መነሻው ህንድ አገር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ የአንዳንድ ነገዶች ባላባቶችና ሚስቶቻቸው ሀፍረተ

ስጋቸውን ለመሸፈን ይጠቀሙበት እንደነበረና 'አረማውያን' የግንብ፣ የውሃና የዘመቻ አምላክ ተደርገው ይመለክባቸው እንደነበረ እንዲሁም የአማራው ማህበረሰብ ከኦሮሞ ማህበረሰብ እንደወረሰው ይገልፃሉ (1970፣149 እና 605)፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው አካባቢ ማህበረሰብም ለዕምነቱ ከየት መጣነት የሚቀጥለውን ቃላዊ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

> ከቀይ ባህር ነው የመጣችው፡፡ ከዚያ በኋላ ከዛፍ ላይ አረፈች በቀይ ባህር ዛፍ ላይ፡፡ ….. ውቃቢዎች እንደ እናት አድርገው ያምኑባታል፡፡ አቴቴ ግንቢ፣ አቴቴ ዱላ፣ አቴቴ ሃራ እያሉ እንደ ሶስቱ ስላሴዎች ያምኑባታል፡፡ ይህንን ተከትለው ህዝብ ሁሉ ያምኑባታል፡፡ እሷ ግን የምትገኘው ከዛፍ ላይ ነው ያለችው፡፡ የቀዬው ሰዎች ቀይ ባህርጋ ከሚገኘው ላይ ፍሬ ለቅመው ለአምልኮ እንዲመቻቸው ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ነጭና ዶቃ እንዲሁም ዝም ብሎ ይቀባል፡፡ ለእያንዳንዱ ስም ይሰጡታል፡፡ ከዚያ ወዲህ በሶስቱ ስም ይታመንበታል (ከወ/ሮ አየለች ስንሻው ጋር በ18/11/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

ጥቅሱ በማህበረሰቡ አረዳድ የአቴቴ መንፈስ በዛፍ ላይ የምትገኝ ሲሆን የመጣችው ከቀይ ባህር ውስጥ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ በዛው በቀይ ባህር አካባቢም አርፋበታለች ተብሎ ከሚታመነው ዛፍ ላይ ፍሬዎችን በመልቀምና ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ነጭና ዶቃ (ጥቁር ሰማያዊ) ቀለሞችን በመቀባት የዕምነቱ ክዋኔ እንደተጀመረ ከማህበረሰቡ ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህ ማህበረሰቡ ዕምነቱ ከየት እና እንዴት ተጀመረ ለሚሉት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ

ይህ ሀሳብ ደስታ ተክለወልድ አጀማመሩን በተመለከተ ካሰፈሩት ሀሳብ የተለየ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ምናልባትም ለህንዳውያኑም መነሻቸው ይኸው ቀይ ባህር ይሆናል የሚል እሳቤ በማህበረሰቡ ዘንድ አለ፡፡ ከህንዳውያኑ ደግሞ ደስታ ተክለወልድ በጠቀሱት መንገድ በሀገራችንም ተሰራጭቶ አሁን ያለበት ደረጃ ደርሷል (ከአቶ ሀይሉ እሩፌ ጋር በ19/11/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ዕምነት አቴቴ ወቅት ተጠብቆ ፌጫሳ ካልተከበረላት የህፃናትን፣ የአዛውንቶችንና የሴቶችን ጤንነት ትፈታተናለች፡፡ የእነዚህን ደህንነታቸውን ለመጠበቅም ከበራው በጥቅምት፣ በታህሳስ፣ በሚያዚያና በሀምሌ ወራት ይካሄዳል፡፡ በአካባቢው በአብዛኛው አቴቴ የምትከበረው በሀምሌ ወር ሲሆን ለከበራውም ማክሰኞ፣ ሀሙስና ቅዳሜ ቀናት ቅዱስ ቀናት እንደሆኑ ያታመናል፡፡

አቴቴ የሚከወንበት ቤት አዘውትረው ምግብ የሚያበስሉበት፣ የሚመገቡበትና ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ቤት ወይም ጫት ቅቀላና ለጭዳ በሚዘጋጀው አነስተኛ ጎጆ ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እኔ ምልከታ ባደረኩባቸው ሶስቱም ክዋኔዎች የተከወኑት ሁልጊዜም በሚጠቀሙበት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ቤቱ ዘወትር የሚጠቀሙበት ቢሆንም ለዚህ ዕለት የተለየ የቤት ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡ በተገኘሁባቸው ሁሉም ክዋኔዎች ላይ ይህንኑ መመልከት ችያለሁ፡፡ ስርዓተ ክዋኔው የሚደረገው ቅዱስ ቀናት ናቸው ተብሎ ከሚታመንባቸው መካከል አመቺ የሆነውን በመምረጥ ሲሆን አመሻሽ ላይ ከብት ከገባ በኋላ ይደረጋል፡፡

የአቴቴ ክዋኔን በተመለከተ ሰፊ መረጃ ያገኘሁበት ወ/ሮ ፈለቀች አልታዬ ቤት ማክሰኞ ቀን የተደረገው ነው፡፡ ከዋኟ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አካባቢ አቴቴ የሚሉበትን ቤት ለከበራው በሚያመች መልኩ ያሰናዱታል፡፡ ይህን ክዋኔ ያደረኩበት ቤት ምድር ቤት እና ዘወትር ለምግብ ማብሰያነትና መመገቢያነት የሚጠቀሙበት ሲሆን በአማካኝ 7 ሜትር በ5 ሜትር የሚሆን ስፋት አለው፡፡ ቤቱ ምድር ቤት እንደመሆኑ መጠን ጣሪያው ላይ የላይኛው ፎቅ ቤት ርብራብ በጉልህ ይታያል፡፡ መግቢያ በሩ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከበሩ በስተቀኝ አንድ አነስተኛ በቀርከሃ የተከፈለ ክፍል (ጓዳ) ይገኛል፡፡ በግድግዳው ስር ዙሪያውን መደብ በመኖሩ ታዳሚዎች እዛ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ከበሩ በስተግራ በኩል ባለው ግድግዳው ላይ ደግሞ አንድ ቆጥና ሁለት ዘረንጋዎች ይገኛሉ፡፡ ቆጡ ላይ የማገዶ እንጨት በጪስ እንዲደርቅ ተደርድሮበታል፡፡ ከሁለቱ ዘረንጋዎች መካከል አንዱ በምዕራባዊ ግድግዳው ላይ የሚገኝ ሲሆን የተለያዩ አነስተኛ መጠን ያላቸው መገልገያ ቅሳቁሶች ተደርድረውበታል፡፡ ሁለተኛው ዘረንጋ በደቡባዊው ግድግዳ ላይ ሲገኝ ከዋኟ ተቀምጠው ለሚሰሩበት ምድጃ ቅርብና ለምግብነት እንዲሁም ለክዋኔው የሚያገለግሉ ነገሮች የተደረደሩበት ነው፡፡

ቤቱ አስፈላጊው ፅዳት ተደርጎለታል፡፡ በቤቱ በምስራቃዊና በደቡባው ግድግዳዎቹ መጋጠሚያ ስር በክብ ቅርፅ መሬት ላይ በተሰራው ምድጃ ዙሪያ እርጥብ ቄጤማ ተጎዝጉዞ ቡና ቀራርቧል፡፡ ከዋኟ ከምድጃው እሳት ለመገልገልና ሌሎቹን የአቴቴ ክዋኔዎች ለማድረግ በሚያመቻቸው መልኩ በምድጃው ዙሪያ በተሰራው መደብ ላይ ተቀምጠው ለክዋኔው የተዘጋጁትን ነገሮች ያቀራርባሉ፡፡ ክዋኔውን ለመመልከትና ለመሳተፍ በቦታው የነበርነው 7 ሰዎች ስንሆን 3ቱ ልጆቻቸው፣ 2ቱ የልጅ ልጆች፣ 1 የእኔ ረዳትና እኔ ነበርን፡፡

ለክዋኔው የሚያስፈልጉት ሁለት ማሰሮ ቅንጬ፣ የቀለጠ ቅቤ፣ ሶስት ድፎ ዳቦ፣ ቂጣ፣ ሰባት ድፍን ቡና፣ ጭሳጭስ (ድኝ፣ ከርቤና ሌሎች የጭስ አይነቶች የተቀላቀሉበት)፣ ጠላ፣ ጠጅ ሳር፣ ሽቶ ሳር እና የሚፈላ ቡና ሲሆኑ ሁሉም በምድጃው ዙሪያ በተጎዘጎዘው ቄጤማ ላይ ይቀርባሉ። በጫት ቅቀላና በጭዳ ወቅት እንደሚደረገው ሁሉ በዚህም ዕምነት ውስጥ አምልኮው የሚደረገው በምሰሶ ስር ነው። ስለዚህ ክዋኔው የሚደረግበት ቦታ ከምሰሶው ባይርቅ ይመረጣል።

ከዚህ በኋላ የከበራ ክዋኔውን መጀመሪያ ጊዜ ነው። አቴቴ ለከበራ ቀኗ ብቻ የሚለበስ የክብር ልብስ አላት። ልብሱ ከጥጥ ፈትል የተዘጋጀ ጥቁር ጥለት ያለው ጥብቆ (ቁመቱ ከጉልበት የማያልፍ ቀሚስ)ና ከአንደኛው ጫፍ ጥቁር ጥለት ከሌላጫው ጫፍ ደግሞ ቀይ ጥለት ያለው የአንገት ልብስ ሲሆን ከከበራው በኋላ እስከ ቀጣዩ ከበራ ድረስ በክብር ተጠቅልሎ ሳጥን ውስጥ ይቀመጣል። ከልብሱ በተጨማሪም አቴቴ የምትመለክበት ዋነኛ መሳሪያዎች ሶስት ጨሌዎች ናቸው። ከዋፏ የክብር ልብሷን ከተቀመጠበት አውጥተው ከለበሱ በኋላ ጨሌዎቹ የቀለጠ ቅቤ ተነክረው አንገት ላይ ይጠለቃሉ። ነገር ግን የአቴቴ ከበራውን እራሳቸው ካልጀመሩት (ከቤተሰብ ከወረሱት) የክብር ልብሱን መልበስም ሆነ ጨሌዎቹን አንገት ላይ ማድረግ አይገደዱም።

ጨሌዎች የሚዘጋጁት በባህር ውስጥ ከሚገኝ ባልጩት የሚባል የድንጋይ አይነት ነው። ሶስቱም የተለያየ ቀለማት እና ስያሜዎች አሏቸው። በቁመት ከሁለቱ በተወሰነ መጠን ረዘም የምትለው ጥቁር ሰማያዊና ነጭ ቀለማት ካላቸው ዶቃዎችን የተዘጋጀች ስትሆን ስያሜዋም አቴቴ ግንቢ ይባላል። አረንጓዴ ቀለም ያላት ጨሌ አቴቴ ሐራ ስትባል ጥቁር ሰማያዊ፣ ነጭና ቀይ ቀለማት ካላቸው ጨሌዎች የምትዘጋጀው ደግሞ አቴቴ ዱላ በመባል ትታወቃለች። በቁጥር ይከፋፈሉና ገመዱ ይቋጠራል ወይም በመጠን ከፍ ያለ ዶቃ ይደረግበታል፤ ይህ መክተሪያ የሚባል ሲሆን በቁጥር የተለዩት ዶቃዎች እንዳይቀላቀሉ የሚያደርግ ነው። እነዚህን ዶቃዎች ቁጥር አመጣጥኖ የሚከትር፣ የሚያስርና ትርጓሜያቸውንም የሚያውቅ ሰው ጨሌ አሳሪ ይባላል።

እርጥብ ሳር በተጎዘጎዘበት ወንፊት ላይ የቀለጠ ቅቤ በጣባ (ትንሽ ሳህን መሳይ ሸክላ) ተደርጎ ይቀርባል። እጣኑና ሰንደሉ በደንብ ከተጨሰ በኋላ ጨሌዎቹ የጣባው ቅቤ ውስጥ ሶስት ጊዜ ይነከራሉ። ቅቤ ከተነከሩ በኋላ በአቴቴ ግንቢ፣ ሓራና ዱላ የተሰየሙት ጨሌዎች በቅደም ተከተላቸው መሰረት አንገት ላይ ይነገታሉ። በመቀጠል ለከዋፏ ጨሌዎቹ በቀረቡበት ወንፊት

ላይ ሳህን ተደርጎ የቀለጠ ቅቤ እና የተቆሉት ሰባት ድፍን ቡናዎች መካከሉ ላይ ተጨምሮበት ይቀርባል፡፡ ከወንፊቱ ላይም ሶስት ሳሮችን በቀኝ እጅ ሶስቱን ደግሞ በግራ እጅ በመያዝ ከቅንጬው ላይ በሳሩ ቅቤ እየተነከረ አንገት ላይ የተንጠለጠሉት ጨሌዎች ሶስት ግዜ ይቀባሉ፡፡ ይህን በሚያደርበት ወቅት "እሊሊሊሊሊሊ..... አቴቴ ግንቢ አቴቴ ሐራ አቴቴ ዱላ በሳርሽ በለምለምሽ በጨፌሽ ልጆቼንም ከብቶቼንም ቀዬውንም ጠብቂ ለአመቱ ደግሞ በሰላም ካደረስሽን ከዚህ በላይ ደግሰን እናከብርሻለን" እያሉ ያመሰግኗታል ይለምኗታልም፡፡ ከዋኗ ቡናዎቹን በጥርሳቸው እየሰባበሩ ወንፊቱ ላይ ወደሚገኘው ሳር ይበትኑታል፡፡ ትርጓሜውም ችግራችንን እንደዚህ አድቅቀሽ አስወግጂልን እንደማለት ነው፡፡

የተቀቀለው ቅንጬም ከሁለቱም ማሰሮዎች ተቀንሶ ለተሳታፊዎቹና ለከዋኟ ይቀርባል፡፡ ሁሉም ሰው ከመቅመሱ በፊት ለከዋኟ ከቀረበው ላይ መጀመሪያ ለመንፈሷ ሶስት ጊዜ ተቆንጥሮ ይጣል፡፡ ከመንፈሷ ቀጥሎ ከዋኟ ይቀምሱና ሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ ቡናና ጠላ እየተጠጣ ቅንጬው ይበላል፡፡ የጨሌዋ አምላክ ትቃጠላለች ተብሎ ስለሚታሰብ በርበሬና ጨው ነክ ነገር በክዋኔው ላይ ለምግብነት አይቀርብም፤ ከዋኟም መመገብ የለባትም፡፡

በምሽት አቴቴ ግንቢ አቴቴ ሐራ አቴቴ ዱላ ተብላ የተጠራችው መንፈስ ልጆቹንና ከብቶቹን በምህረት ስትጎበኝ ታድራለች፡፡ በማግስቱ ጠዋት ቡና ተፈልቶ፣ አንድ ድፎ ተቆርሶ ከሶስት ሪሚጦዎችና ኑግ ተደርጎ ማታ የተጎዘጎዘው ቄጤማ ተጠርጎ ይጣላል፡፡ ይህ ሂደት መንፈሷን መሸኛ ሲሆን ጨሌ ጠረጋ ይባላል፡፡ ጠረጋው ሲጠናቀቅ ለጨሌዎቹ ማስቀመጫነት በተዘጋጀው አነስተኛ ሙዳይ ውስጥ ሸቶ ሳር፣ ጠጅ ሳርና ቅቤ ተደርጎበት ይከተቱና ለቀጣዩ ከበራ ይቀመጣሉ፡፡

ከወ/ሮ እቴነሽ ጋር ባደረኩት ቃለ ምልልስ አቅም ያላቸው ሰዎች ለአቴቴ ቀይ ሴት በግ የሚያርዱ ቢሆንም ይህ በብዛት አይታይም፡፡ እኔም በምልከታዬ ይህንን አልተመለከትኩም፡፡ ነገር ግን ከበራውን ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ጨሌ የሚያደርጉ ሰዎች ግዴታ እንደሆነ ገልፀውልኛል፡፡ ምክንያቱም በጨሌዎቹ ላይ የምታድረው መንፈስ እንድትለምድ ጨሌዎቹ በቀይ ሴት በግ ደም መነከር አለባቸው፡፡ አንዳንዶች ጨሌዎቹን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በዚሁ ደም እንደሚነከሩም ገልፀውልኛል፡፡

አቴቴን የሚከውን ሰው ስርዓተ ክዋኔውን ማቋረጥ ከፈለገ ስርዓቱን ተከትሎ መሆን አለበት፡፡ ሁለት አይነት የማቋረጫ መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛው ጨሌዋን ለሚፈልጉ ሰዎች መሸኛ ሁለት ቁና እህልና ሃያ ብር አድርጎ መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ውሃ ወይም እሳት ውስጥ መጨመር ሲሆን ከዚህ በኋላ የጨሌዋ መንፈስ በእነርሱ ላይ ስልጣን እንደሌላት አጠንክረው የሚገልፁበት መንገድ ነው፡፡ የመጀመሪያው ተመራጭ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ ፈጫሳን ማቋረጥ በአዛውንቶችና በልጆች በተጨማሪም በከብት ላይ ችግር ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሚያስከትለው ችግር በከብቶች ላይ የመራባት ሂደትን ይቀንሳል እንዲሁም ለሞት ይዳርጋል፤ በልጆች ላይ ደግሞ የአይንና የልብ በሽታዎችን ያስከትላል በተጨማሪም ትዳር እንዳያገኙ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል (በ15/11/2006 ዓ.ም. የተደረገ ምልከታና ከወ/ሮ ፈለቀች፣ ከወ/ሮ ሙላቷና ከአቶ ዘውዴ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

## 4.2 ለሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ያለው አመለካከት በቀይት ንዑስ ወረዳ

በዚህ በተጠኚው አካባቢ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ሰውንና የቤት እንስሳትን ለሚተናኮሉ እርኩስ መናፍስት የሚቀርብ ግብር ነው፡፡ ከመረጃ ሰጪዎቹ መካከል ግማሽ የሚሆኑት እነዚህን ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን ‘ባዕድ አምልኮ’ ወይም ‘አምልኮ’ በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ ዕምነቶቹን በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያከብሯቸው ኖረዋል፤ አሁንም እያከበሯቸው ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዕምነቶች በሀይማኖትና በማህበረሰቡ ያላቸው ዕይታ በዚህ ንዑስ ክፍል ተዳሷል፡፡

### 4.2..1 ሀይማኖታዊ ዕይታ

ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ ከሚገኙት ማህበረሰቦች ውስጥ 99.2 ከመቶ የሚሆኑት የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 0.8 ከመቶ የሚሆኑት የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ በክፍል አንድ ስር ተገልጿል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ስር የሚነሳው ሀሳብም ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ ከሚከተለው ሀይማኖት ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚመለከት ነው፡፡

እነዚህ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች በኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ቅዱስ መፅሀፍት ውስጥ እንዲከወኑ አልታዘዘም፡፡ ከዋኞቹ በዚሁ ሀይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም ከትውልድ እየተወራረሱ እዚህ የደረሱ ናቸው፡፡ ከማህበረሰቡ ጋር ለረጅም ጊዜ የቆዩ ስለሆኑ እንደ ሃይማኖቱ አካል ቢታዩም መከወናቸውን በግልፅ የሚቃወሙ ሀይማኖታዊ መፅሀፍት አሉ፡፡

ከእነዚህ ውስጥ የሀይማኖቱ ቅዱስ ቃላት ከሰፈሩበት መካከል ዋነኛ የሆነው መፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተለውን ቃል እናገኛለን፡-

> እግዚአብሄርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡፡ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሄር አምላክህ ነኝ፡፡ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ፡፡ በላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡፡ አትስገድላቸው፣ አታምልክቸውምም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ፣ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሄር አምላክህ ቀኛተኛ ነኝና (ዘፀ 20÷1-6)፡፡

ይህ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ቃል የሀይማኖቱ ተከታይ ምዕመናኖች ለእግዚአብሄር ብቻ እንዲገዙ እንጂ ሌላ አምላክ እንዳያመልኩ የሚከለክል ነው፡፡ ከእርሱ ውጪ የሆኑ በምንም የተመሰሉ አማልክትን እንዳያምኑ እና እንዳያመልኩ ቢያመልኩ ግን ቅን አምላክ በመሆኑ ምንም ሳያሳጣቸው ወደሌላ በመሄዳቸው እስከ ሶስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ ምህረት እንደሌለው ቃሉን ያሰፈረበት ነው፡፡ በሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ውስጥ ደግሞ የሚመለኩት አካላት ከእግዚአብሄር ውጪ የሆኑ መናፍስት በመሆናቸው ከሀጢያት ይመደባሉ፡፡

ይህንን ትዕዛዝ መነሻ በማድረግም የሀይማኖቱ አባቶች ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ሀይማኖታዊ መሰረት የሌላቸውና በቅዱስ መፅሀፍትም የተወገዙ ልማዳዊ ድርጊቶች በመሆናቸው ክዋኔያቸው መቅረት አለበት የሚል አቋም ያንፀባርቃሉ፡፡

> እነዚህ አምልኮዎች በእግዚአብሄር ዘንድ የተወገዙ ናቸው፡፡ ጫትም ሲቀቀል፣ ጭዳም ሲባል፣ አድባርም፣ ቦረንትቻም፣ ፈጫሳም ላይ ባራኪ ቄስ ወይ ዲያቆን አይገኝም፡፡ የሚገኘውም የሚባርከውም ዳቢሎስ ነው፡፡ እግዚአብሄር ደግሞ ሁለት አምላክ አታምልኩ፤ ከእኔ ሌላ አታምልኩ ይላል፡፡ ከሁለት አንዱን መምረጥ እንጂ ሁለቱንም መከተል አይቻልም፡፡ ግብርም ለቤተክርስቲያን እንጂ በየዛፉ በየድንጋዩ ስር ለዳቢሎስ መገበር በሰማይ ቤት አሳት ውስጥ ነው የሚከተው፡፡ ዳቢሎስ ሆነ ብሎ እየለፈለፈ ለችግር ፈጥኖ ደራሽ በመምሰል የሰዎቹን ልቦና ይስባል፡፡ እነሱም እግዚብሄር ትግስተኛ ስለሆነ ወዲያው ስለማይደርስ

ወደሚለፈልፈው ያደላሉ፡፡ የሰይጣንንና የእግዚአብሄርን ሳይለዩ አንዴ እዛ አንዴ እዚህ ይላሉ፤ አስቀድሰው ጭዳ፣ ቦረንትቻ ይላሉ፤ አድባር ይወጣሉ፡፡ ደሞ እዛ አይቀሩም ቤተክርስቲያን ይመጣሉ (ከአባ ደመቀ ዘለቀ ጋር በ09/09/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

አባ ፈቃዱና ሊቀ ኅሩያን ሀ/ማርቆስ ይህንኑ ሀሳብ በመደገፍ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት እና ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ የሚዛመዱ ሳይሆኑ የሚቃረኑ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዚህ አይነት አስተምሮት በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሰጠት መጀመሩ ከዋኝ ምዕመናን ዕምነቶቹን 'ባዕድ አምልኮዎች' ናቸው እንዲሉና ክዋኔያቸውን እየተቀዛቀዘ እንዲሄድ እያደረጋቸው ነው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተካተቱት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች መካከል ከኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ጋር የተያያዘ መነሻ ያለው አድባር ብቻ ነው (በቅድስት ድንግል ማሪያም ልደት ምክንያት ስለተጀመረ)፡፡ ይህም ቢሆን በውልደቷ ዕለት ለአንድ ቀን ብቻ የተደረገ ሲሆን ይህን መንገድ ተከትለው ምዕመናኑ በየዓመቱ እንዲያከብሩ አልታዘዘም፡፡ እንዲያከብሩ ቢፈቀድም እንኳን ስርዓተ ክዋኔው ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀየረና ከሃይማኖታዊነት እያፈነገጠ እና አቅጣጫውን እየቀየረ (ዛፍና ድንጋይን ቅቤ በመቀባት እየተመለከ) በመሆኑ ከሀይማኖቱ ጋር ይጋጫል (ከሊቀ ኅሩያን ሀ/ማርቆስ ዘለቀና አባ ደመቀ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

የሀይማኖት አባቶች ለምዕመናኑ አስተምህሮት በቤተክርስቲያን በመስጠት ማህበረሰቡ እንዲተዋቸው ከማድረግ ባለፈም ዕምነታዊ ክዋኔዎች በሚደረጉባቸው ከበራዎች ላይ በመገኘትም ጭምር በግልፅ ይከለክላሉ፡፡ ክልከላቸው ከዚህም አልፎ እስከ ውግዘትና እንደ እድር ካሉ ማህበራዊ ግኝኙነቶች እስከማገድ ድረስ የሄደ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዕምነቶቹ በሀይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ መከወናቸውን የማይቃወሙ ወይም የሚደግፉና እነርሱም የሚከውኑ የሀይማኖት አባቶች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱት ዕምነቶቹ ሀይማኖታዊ መሰረት ባይኖራቸውም በአማኞቹ ዘንድ መከወናቸው ምንም አይነት ችግር የለውም የሚል ዕሳቤ ያላቸው ናቸው፡፡ ምንም እንኳ እግዚአብሄር እነዚህን እምነቶች ከውኑ ባይልም ለክፋት የሚደረጉ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ይጠቀመኛል የሚል ሰው መከወን ይችላል፡፡ በቤተክርስቲያን ለአስተምህሮት የሚጠቅሷቸው መፅሃፍትም የተለያዩ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ብለው ያዘጋጇቸው እንጂ በትክክል ሀይማኖቱን የሚያንፀባርቁ

አይደሉም የሚል ሀሳብ ይሰነዝራሉ (ከመሪጌታ ይልማሸዋ ከበደ ጋር በ21/11/2006 ዓ.ም. የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

ከላይ ከተነሱት ሁለት ሀሳቦች በመነሳት በሀይማኖት አባቶቹ መካከልም ቢሆን ሁለት አይነት አመለካከት እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የእምነቶቹን ስርዓተ ክዋኔ የማይቃወሙ የሀይማኖት አባቶች ይኑሩ እንጂ ሀይማኖቱ ይከወኑ ዘንድ እንደማያዝ እነርሱም ይገልፃሉ፡፡

### 4.2..2 ማህበረሰባዊ ዕይታ

በማህበረሰቡ ውስጥ ስለዕምነቶቹ የተለያየ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆን ክዋኔዎቹን የሚያደርጉትም ባላቸው የግንዛቤ ልክ ነው፡፡ አብዛኞቹ ለሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ያላቸው አዎንታዊ አስተሳሰብ የሚያፀባርቁ ናቸው፡፡ እነዚህን ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የሚከውኑት በሌሎች ላይ ክፉ ነገር ለማድረስ ሳይሆን ራስን፣ ቤተሰብና ንብረትን ከክፉ ነገር ለመከላከል የሚደረጉ መሆናቸውን እንደ አቢይ ነጥብ በመያዝ ተገቢና አስፈላጊ መሆናቸውን አበክረው ይገልፃሉ፡፡ ይህንን አመለካከት የሚጋሩት ሰዎች ዕምነቶቹን ከሚከተሉት ሀይማኖት ነጥለው አይመለከቱትም፡፡ አባቶቻችን ያቆዩልን ልማድ ነው በማለትም ወቅታቸውን እየጠበቁ አስፈላጊውን ነገር እያሟሉ ያከብሯቸዋል፡፡ ቤተሰቦቻቸው ዕምቶቹን ሲያከብሩበት የነበረውን መንገድ ተከትለው እንደልማዱ ይከውናሉ፡፡

ከዋኞቹ በሞት ሲለዩ ወይም እንደልብ ተንቀሳቅሶ የሚያስፈልገውን ነገር ለማዘጋጀት ጉልበታቸው ሲደክምና ከበራውን ሲያቋርጡ ቀሪው የቤተሰቡ አባል ሊረከብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የከዋኞቹ ቤተሰብ አባላት የራሳቸውን ጎጆ ሲመሰርቱ የቤተሰቦቻቸውን ወይም የሚኖሩበትን አካባቢ ልማድ በመከተል ያከብራሉ፡፡ እነርሱም በዚሁ መልኩ ለልጆቻቸው ያወርሳሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው ዕምነቶቹ እንደውርስ ትውልድ የሚቀባበላቸው መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን በቅብብሎሹ ወቅት ዘመኑን ተከትሎ በአከባበሩ ላይ የሚጨመሩና የሚቀነሱ ነገሮች አሉ፡፡

ከበራውን የሚቀጥሉት የወረሱት ልማድ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን የራሳችን፣ የቤተሰቦቻችንና የከብቶቻችን ደህንነት የተጠበቀው እነዚህን ዕምነቶች ወቅታቸውን ጠብቀን በመከወናችን ነው የሚል እሳቤ ስላላቸውም ነው፡፡ በሀይማኖት ተቋማት የዕምነቶቹን መከወን የሚያወግዙትንም የሚሞግቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከሀይማኖቱ ጋር የሚፃረር ከሆነ ለምን እስከዛሬ ድረስ አልተከለከለም? የሀይማኖት አባቶችስ ሲከውኗቸው የነበረው ለምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን

ያነሳሉ፡፡ መቅረት አለበት የሚሉት ወገኞች ለዚህ የሚሰጡት ምላሽ ከዚህ በፊት ሁሉም (የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት አባቶችም ጭምር) ሲከውናቸው የነበረው ባለማወቅና በግዕዝ ቋንቋ የተዘጋጁትን የሀይማኖቱ መፅሃፍት ካለመረዳት ነው የሚል ነው፡፡ አሁን ግን የሃይማኖቱ ሊቃውንት ቅዱሳን መፅሐፍቱን እየተመራመሩ በአካባቢው የሚከወኑት ሀገረሰባዊ ዕምነቶች የማይደገፉና በእግዚአብሄር ዘንድ የተወገዙ መሆናቸውን በመረዳት ለምዕመናኑ እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ አስተምሮት ግን ዕምነቶቹን በአግባቡ በሚከውኑት የማህበረሰቡ አካላት ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንብዛም ነው፡፡ (በ05/09/2006 ዓ.ም ከቡድን ውይይት የተወሰደ)

አሁን ላይ ባለው ሀይማኖታዊ አስተምህሮት ምክንያት ከዋኞቹ በሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ከበራ ላይ ያላቸውን አቋም በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ከላይ በሰፈረው ሀሳብ የሚስማሙና ለምድራዊ ሕይወታቸው ከሚከተሉት ሀይማኖት በበለጠ እንደጠቀማቸው ደፍረው የሚናገሩ ናቸው፡፡ በዚህ ምድብ የማህበረሰቡ አባላት ዕምነቶቹን ባህሪያቸው ያደረጉ በመሆናቸው ‘ባዕድ አምልኮ ነው ተውት’ የሚላቸውን አካል ምፅዓት እንደጠራባቸው የሚቆጥሩ ናቸው፡፡ “ተዉ ተዉ ይሉናል እንጂ አንድ ከብት ቢሞትብን ዞረው አያዩንም” (የቡድን ውይይትና ከወ/ሮ ተናኜ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

በሁለተኛው ምድብ የሚካተቱት የዕምነቶቹን ከበራ በመተውና ባለመተው መካከል ያሉ ከዋኞች ናቸው፡፡ ከዕምነቶቹ የምናገኛቸውን ጥቅሞች ከሀይማኖቱ እናገኛለን፣ ትርፉ ኩነኔ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ከበራቸውን አላቋረጡም፡፡ የአካባቢው ሰው ሙሉ በሙሉ ካላቋረጠ እነርሱ ብቻ ቢያቋርጡ ለሰፈሩ የመጣው የማያደርጉትን ሰዎች ልጆችና እንስሳት ይተናኮላል ብለው ስለሚያምኑ ሁሉም የመንደሩ ሰዎች ወጥ በሆነ መልኩ ማቆም ወይም መቀጠል ይኖርበታል (ከአቶ ብዙአየሁ ጋር በ15/08/2006 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡ በሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ያላቸው ዕምነት ዝቅተኛ ቢሆንም ከስጋት ነፃ ለመሆን የክዋኔዎቹ አካላት ይሆናሉ፡፡ በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉት ቢያንስ አንዱን ሀገረሰባዊ ዕምነት የሚከውኑ ናቸው፡፡

በሶስተኛው ምድብ ውስጥ የሚካተቱት ከዚህ በፊት ሁሉንም ወይም አብዛኞቹን ዕምነቶች ይከውኑ የነበሩ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ያቋረጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ለማቋረጣቸው በምክንያትነት የሚነሱት ወደሚከተሉት ሀይማኖት ጠልቆ መግባትና ከዕምነቶቹ የሚፈልጉትን ያህል ጥበቃ አለማግኘት ናቸው፡፡

በፊት ጫትም፣ ጭዳም፣ አድባርም ምንም እል ነበር፡፡ አሁን ግን የጠቀመኝ ነገር ስለሌለ ይኸው ከተወኩ ስድስት አመቴ ነው፡፡ እሱም (ባለቤታቸው) ከሞት አልቀረ፤ ሁለት ልጆቼንም ቀበርኩ፤ እኔም ጤና አላገኘሁ፤ ኑሮውም አልተለወጠ፡፡ ለምኑ ነው ታዲያ ለሱ ማኅብደዬ!? … እድሜዬም እየገፋነው ብቆርብ ይሻለኛል ብዬ ሁሉንም ትቸዋለሁ (ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር በ13/11/2006 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡

ክዋኔዎቹን የሚጀምሩባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ የሚኖሩበት አካባቢ የሚገኙት ሰዎች የዕምነቶቹ ከዋኞች በመሆናቸው የውዴታ ግዴታ መጣል፣ የቤተሰብ ጤና መቃወስ እና የእንስሳት እልቂት መደጋገም ለክዋኔዎቹ መጀመር ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከዋኞቹ ክዋኔዎቹን ከጀመሩ በኋላ እንዳሰቡት ከታመኑለት አካል ጥበቃ አለማግኘታቸው ተስፋ ያስቆርጣቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ላይ ለእነዚህ ዕምነቶች መገዛት ሀጢያት መሆኑን ከሀይማኖታዊ ተቋም የሚሰጠው ትምህርት ሲታከልበት ክዋኔያቸውን እንዲያቋርጡ ትልቅ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ በተጨማሪም የከዋኞቹ እድሜ እየጨመረ መሄድና ለክዋኔ የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሙሉ ለማሟላት የገንዘብ አቅም ማጣት፣ በሞት መለየት እንዲሁም ከዘመናዊ አኗኗር ዘዴ መላመድና ዘመናዊ ትምህርትን የቀመሱ ሰዎች የሚፈጥሩት አሉታዊ ተፅዕኖች ሌሎች ምክንያች ናቸው፡፡

አቶ ደስታ ግርማ እንደገለፁት ከሆነ ዕምነቶቹን በተመለከተ ማህበረሰቡ ውስጥ አምላክ ቁጣ እንዳመጣባቸው በማሰብ በማንኛውም ምክንያት የተፈጠረን ነገር ከዚሁ ጉዳይ ጋር የማያያዝ ሁኔታም ይታያል፡፡ “የቀዬው አባወራ ሁሉ እዛች አድባር ስር ይወጣ ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ማንም ሰው ሳይነካት አድባሯ በእሳት ጋይታ ተገኘች፡፡ እኛም የእግዜር ቁጣ ነው ብለን አድባር መውጣታችንን ተውን፡፡ ሰውም ራሷን ማዳን ያቃታት እኛን ልታድነን ኖሯል? እያለ እርግፍ አድርጎ ትቷታል” (በ05/09/2006 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ)፡፡ እንደነዚህ አይነቶች አጋጣሚ የሚፈጥራቸው ክስተቶች ማህበረሰቡ ጥቂዎችን እንዲያነሳና አካባቢውን እንዲመረምር ወይም መንፈሱ በሽብር እንዲዋጥ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በሁለቱም መልኩ ቢሆንም ግን ከዕምነቶቹ ይርቃል፡፡ ምክንያቱም ከዕምነቶቹ ክዋኔ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ቢነሳም ምላሹ መከወናቸውን የሚቃወም ነው፡፡ የመንፈስ መሸበሩም ቢሆን ‘አምላክ ተቆጥቶ ያመጣው ሊሆን ስለሚችል ቢቀርብን ይሻላል’ የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው አካባቢ ውስጥ የሚገኙት ነዋሪዎች አብዛኞቹ ከሚከተሉት የኦርቶዶክስ ሀይማኖት በተጨማሪ ከሚፈታተኗቸው (ከሚተናኮሏቸው)መናፍስት እራሳቸውን፣ ንብረታቸውን፣ ልጆቻቸውንና ቀዬያቸውን ለመከላከል በዋናት አምስት ሀገረሰባዊ ዕምነቶችን ይከውናሉ፡፡ እነዚህ ዕምነቶች የየራሳቸው ፋይዳ እና የአከዋወን ስርዓት ያላቸው ናቸው፡፡

ዕምነቶቹ በአካባቢው የሚከወኑበት ዋነኛ አላማ ማህበረሰቡ ክፉ ከሚላቸው ነገሮች በተለይም ደግሞ ከበሽታን፣ ተፈጥሯዊ አደጋን፣ ከሰዎችና ከእንስሳት ሞትን እንዲሁም ከሰብል በረከት ማጣትን ለመከላከል እና ከተከሰቱም በኋላ ምህረት ማግኘት ነው፡፡ ይህ የሁሉም ዋነኛ ፋይዳ መሆኑ ቢያመሳስላቸውም በዋናነት የሚጠብቁት ወገን ግን ይለያያል፡፡ አቴቴ በዋናነት ልጆችን ለመጠበቅ የምትከወን ሲሆን ቦረንታቻ ከብትን ለመጠበቅ ይከወናል፡፡ ጫት ቅቀላና ጭዳ ደግሞ የሚደረጉት ቀዬውን ከክፉ ነገር የመጠበቅ አላማ አላቸው፡፡ አድባር በማህበረሰቡ ውስጥ በሀይማታቸው ከሚያመልኩት አምላክ ያልተናነሰ ስልጣን አላት ተብሎ ስለሚታመን ሁሉንም እንድትጠብቅ ስርዓተ ክዋኔዋ በየአመቱ ይደረጋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ዕምነቶች ቢኖሩም እንኳን የሚገበርላቸው መናፍስት የተለያዩ ስለሆኑ እና የደህንነት ጉዳይ አስገዳጅ ስለሚያደርጋቸው አብዛኛው ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑትን ዕምነቶች ይከውናል፡፡

በእነዚህ ዕምነቶች ውስጥ ትልቁን ቦታ የሚወስደው ህሊናዊ ዕረፍቱ ነው፡፡ የዕምነቶቹ ከዋኞች የሚያስፈልገውን ሁሉ ባደረጉ ቁጥር በዕምነቶቹ ውስጥ ተመላኪ ከሆኑት ልዕለ ተፈጥሮ አካላት የሚፈልጉትን ጥበቃ እንደሚያገኙ ስለሚያምኑ ስጋታቸው ይቀንሳል፡፡

ከከዋኞች ማንነት አኳያ ሲታዩ የተመላኪ አካላቱን ጥበቃ የፈለገ ቤተሰብ ሁሉ ሊከውናቸው የሚችል ሲሆን በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሁለቱንም ፆታዎች ተሳትፎ ይጠይቃሉ፡፡ አድባርና አቴቴ በሴት ጾታ የሚጠሩ ዕምነቶች ሲሆኑ ከዋኞቻቸውም ሴቶች ናቸው፡፡ አድባር ላይ በሴት የማይከወኑ ለምሳሌ እርድ የወንዶች ተሳትፎን ቢጠይቅም ዋናዎቹ ከዋኞች ግን ሴቶች ናቸው፡፡ ቦረንታቻና ጭዳ ግን በወንዶች የሚከወኑ ሲሆን የሴቶች ተሳትፎም ይኖርበታል፡፡ ጫት መቀቀል በወንድም በሴትም ሊከወን ይችላል፡፡

ሁሉም ዕምነቶች ከምግብና ከመጠጥ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ከአምስቱ ውስጥ ሶስቱ (ጭዳ፣ ቦረንታቻና አድባር) ከዋኞቹ አቅም ካላጡ በስተቀር ዕርድን /ደም ማፍሰስን ይጠይቃሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ቡናና ደም እንዲሁም ጥራጥሬዎች ለአምሎኮዎቹ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡

ከምግብና ከመጠጥ ጋር በጣም የሚቆራኙበት ምክንያት ደግሞ ሰዎች በሚመገቡበት ወቅት መናፍስቱም በመለኮታዊ ሀይል ድርሻቸውን ይመገባሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ግብራቸውን ለማቅረብ ያመች ዘንድ ነው፡፡ ዕምነታዊ ከበራዎቹ ከሌሎቹ ወራት ይበልጥ በሚያዚያ እና በግንቦት ወራት ይጎላሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ መናፍስቱ በእነዚህ ወራት በይበልጥ ሀይል የሚያገኙባቸውና ለጥቃት የሚነሳሱባቸው ወራት በመሆናቸው ነው፡፡ ይኸንን ለመከላከል ደግሞ ዕምነቶቹን የሚከተሉ ሰዎች ወቅቶቹ ሲቃረቡ እራሳቸውን አጀጋጅተው አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

የዕምነቶቹ ከበራ ቀጣይነት ያለው መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም መናፍስቱ የለመዱት ከበራና ግብር ሲቋረጥባቸው ለክፋት በይበልጥ ይነሳሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ቢሆንም ግን በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ከዚህ በፊት ዕምነቶቹን ሲከውኑ ቆይተው ያቋረጡ ሰዎች አሉ፡፡ ምክንያቶቻቸው የሀይማኖታዊ ተቋማት ተፅዕኖ፣ የሌሎች ከዕምነቶቹ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ተፅዕኖና የጉልበት ማነስ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በተለይም ዕምነቶቹን በተመለከተ ከሀይማኖታዊ ተቋማትና ከበራዎቹን በማይከውኑ ሰዎች ነቀፌታ እየደረሰባቸው በመሆኑ በነፃነትና በይፋ ከበራዎቹን የመከወን አዝማሚያ በጣም እየቀነሰ ነው፡፡ ከዕምነቶቹ ሙሉ በሙሉ በመውጣትም ፊታቸውን ወደ ተቋማዊ ሀይማኖት የመለሱ በርካታ ናቸው፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ይከውኗቸው የነበሩትን ዕምነቶች በማቋረጣቸውም ደረሰብን የሚሉት የከፋ ችግር የለም፡፡ ችግሮች ቢገጥማቸውም በሃይማኖታቸው ከሚያምኑበት አምላክ ከለላን ይጠይቃሉ፡፡

ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹ ስያሜያቸው እና የከበራ ስርዓተ ክዋኔያቸው እንዲሁም የመከወኛ ጊዜያቸው ቢለያይም የሚከበሩበት ምክንያት ግን ተቀራራቢ ነው፡፡ የከበራዎቹ ዋነኛ ፋይዳ በሰውና በእንስሳት ላይ የሚከሰቱትን እንደ በሽታ፣ ሞትና ድርቅ የመሳሰሉትን መከራዎች ቀድሞ መከላከል ከተከሰተም በኋላም ቢሆን ምህረትን ማግኘት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ዕምነቶቹን Catherine Bell መሰረታዊ የከበራ አይነቶች መካከል  የልውውጥ እና የትስስር ከበራ (Rites of Exchange and Communion) እና የመከራ ጊዜ ከበራ (Rites of Affliction) በተሰኙት ምድቦች ውስጥ ማካተት ይችላል፡፡ የአንዱ ዕምነት በአንድ መልኩ በአንደኛው የከበራ አይነት የሚካተት ሆኖ በሌላ መልኩ ደግሞ ሌላኛው አይነት ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚያመዝነውን መገለጫዎቻቸውን በመውሰድ አምስቱም ሀገረሰባዊ ዕምነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከወኑት ጥበቃንና ድህነትን ለማግኘት በመሆኑ በእነዚህ ሁለት ምድቦች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

በተተኳሪው አካባቢ የሚገኙት የማህበረሰብ ክፍሎች ሀገረሰባዊ ዕምነቶቹን ከሚከተሉት የኦርቶክስ ሀይማኖት ጋር እያጣጣሙ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መገለጫዎቹ ሀይማኖታዊ ትዕምርቶችን በዕምነቶቹ ውስጥ አብዝተው መጠቀማቸው ነው፡፡ በሀይማኖታቸውም በዕምነቶቹም ውስጥ ከሚጠቀሙባቸው ትዕምርቶች መካከል ሶስት ቁጥርና ምስራቃዊ እይታ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተለይ ሶስት ቁጥር በዕምነቶቹ ውስጥ በተደጋጋሚ በትዕምርትነት ቆሞ ይገኛል፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች

### ሀ. የአማርኛ ዋቢ ፅሁፎች


መኮንን ለገሰ፡፡ <u>የአቴቴ ፈጫሳ ክዋኔና ስነቃላዊ ግጥሞች በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ፡፡</u> የቢ.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም፡፡

መኮንን በቀለ:: <u>በአማርኛ የሚነገሩ አምልኳዊ ዕምነቶች፡፡</u> ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1973 ዓ.ም፡፡

ሙሉቀን ዘውዱ:: <u>በባህርዳር አካባቢ በወንዞች ዳር የሚፈፀሙ የአምልኮ ስርዓቶችና ክዋኔያቸው፡፡</u> የኤም.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2001 ዓ.ም፡፡

ማሞ ተፈራ፡፡ <u>በመኸር ወቅት የሚፈፀሙ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች ፋይዳና የቃልግጥሞች ይዘት ትንተና፡፡</u> የኤም.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ነፃነት ሰጠኝ፡፡ <u>በደብረዘይት ከተማ በጎዴት ገበሬ ማህበር በወራአና ገልማ ውስጥ የሚከበሩ ዕምነታዊ ስርዓቶች፡፡</u> የቢ.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1996 ዓ.ም፡፡

ኮማንደር መሃመድ፡፡ <u>የበሪ ሃገረሰባዊ ዕምነት በደቡብ አሪ ወረዳ በምባመር አካባቢ፡፡</u> የኤም.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2005 ዓ.ም፡፡

ግርማ ቡኬ፡፡ <u>የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ዕምነት፡፡</u> የኤም.ኤ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ <u>መፅሀፍ ቅዱስ፡፡</u> ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1962 ዓ.ም፡፡

________________፡፡ የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣
1992 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣
አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1993፡፡

የባሶና ወራና ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት፡፡ የመጀመሪያ መንፈቀ አመት ገንዘብና ልማት ሪፖርት፡፡ ደብረብርሃን፣ ጥር 2006 ዓ.ም፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣
1962 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የስነቃል መምሪያ፡፡ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ ጥር 1991 ዓ.ም፡፡

**ለ. የእንግሊዘኛ ዋቢ ፅሁፎች**

Barnard, Alan and Spencer, Jonathan (ed). Encyclopedia of Social and Culural Antheropology, London and New York, 2002.

Behailu Gebrehiwot. "Omens in Ethiopia." Ethinological society bulletin vol.I nos. 1-10 and vol. II no1 Ed. Alula Pankhurst. Addis Abeba University, 1953.

Bell, Catherine. Ritual Perspectives and Dimensions. Oxford University Press, New York, 1997.

Boyer, Pascal and Lie´nard, Pierre. Why ritualized behavior? Precaution Systems and action parsing in developmental, pathological and cultural rituals. United state of America, 2006.

Cohen, Milton. Death Ritual: Anthropological Perspectives.

Ezekiel Gabissa. Consumption, contraband, and commodification: A History of khat in Harerge, Ethiopia c.1930-1991. Dissertation for degree of Ph.D, Michigan state of university,1997.

Fiseha Hailemeskel. "Atete." Ethinological society bulletin vol.I nos. 1-10 and vol. II no1 Ed. Alula Pankhurst. Addis Abeba University, 1953.

Nardose Seifu. chat consumption and its Impact on Social Security: The Case of Addis Abeba City. Partial Fulfilment for Degree of Masters of Arts, Addis Abeba University, June 2013.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. Living Folklore. Utah: Utah State University Press Logan, 2011.

Wehmeier, Sally and others (ed). Oxford Advanced Learner's Dictionary of Current English. 7th ed, Oxford University Press, 2006.

Yoftahie Kebede. "Genbot Ledata." Ethinological society bulletin vol.I nos. 1-10 and vol. II no1 Ed. Alula Pankhurst. Addis Abeba University, 1953.

## አባሪዎች

### አባሪ 1. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

ሀ. በቃለ ምልልስና በምልከታ የተሳተፉ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | የመኖሪያ አድራሻ (ቀበሌ) | ከዕምነቶቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ተናኜ ሀይሉ | 54 | ባሶደንጎራ | ከዋኝ |
| 2 | አባ ደመቀ ዘለቀ | 58 | ቀይት | የሀይማኖት አባት (ኦርቶዶክስ) |
| 3 | አባ ፈቃዱ ሀይሉ | 47 | ባሶ ደንጎራ | የሀይማኖት አባት (ኦርቶዶክስ) |
| 4 | አቶ ዘውዱ አሰፋ | 55 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 5 | ወ/ሮ ሙላቷ ማሞ | 38 | ባሶ ደንጎራ | ተሳታፊ |
| 6 | ወ/ሮ እቴነሽ ባዩ | 56 | ቀይት | በፊት ይከውኑ የነበሩ |
| 7 | ወ/ሮ አፀደ ኪዳኔ | 59 | ጉዶበረት ከተማ | በፊት ይከውኑ የነበሩ |
| 8 | አቶ ብዙአየሁ ሀይሉ | 29 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 9 | ወ/ሮ በላይነሽ ኪዳኔ | 53 | ቀይት | በፊት ይከውኑ የነበሩ |
| 10 | ወ/ሮ ፈለቀች አልታየ | 60 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 11 | ሊቀ ህሩያን ሀ/ማርቆስ ዘለቀ | 46 | ጉዶበረት ከተማ | የሀይማኖት አባት (ኦርቶዶክስ) |
| 12 | መሪጌታ ይልማሸዋ ከበደ | 47 | ባሶ ደንጎራ | የሀይማኖት አባት (ኦርቶዶክስ) |
| 13 | አቶ ሀይሉ እሩፌ | 72 | ባሶደንጎራ | ከዋኝ |
| 14 | ወ/ሮ አየለች ስንሻዉ | 43 | ጉዶበረት ዙሪያ | ከዋኝ |
| 15 | አቶ አዲሱ በትረ | 33 | ጉዶበረት ዙሪያ | ከዋኝ |
| 16 | አቶ ደስታ ግርማ | 29 | ቀይት | በፊት ይከውኑ የነበሩ |


ለ. በቡድን ውይይት የተሳተፉ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | የመኖሪያ አድራሻ (ቀበሌ) | ከዕምነቶቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ የሹምነሽ ወ/ፃዲቅ | 62 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 2 | አቶ እሸቴ ነጋሽ | 47 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 3 | አቶ ገ/መስቀል ገ/ጊዮርጊስ | 41 | ጉዶበረት ከተማ | ከዋኝ |
| 4 | አቶ ክፍሌ ገ/አማኑኤል | 63 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 5 | አቶ አስረስ ቦጋለ | 27 | ጉዶበረት ዙሪያ | ተሳታፊ |
| 6 | አቶ ነገሰ አለሙ | 30 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |
| 7 | አቶ በላቸው ዘበነ | 44 | ባሶ ደንጎራ | ከዋኝ |

❖ በሁለተኛው ሰንጠረዥ ውስጥ በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተጠቀሱት በቃለ ምልልስና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥም ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

አባሪ 2. የመረጃ አቀባዮች ምስል

❖ ሁሉም መረጃ ሰጪዎች ፎቶ ለመነሳት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት የሁሉንም ፎቶዎች በዚህ ስር ማስፈር አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የሰፈሩት ፎቶዎች ፈቃደኛ የሆኑት መረጃ ሰጪዎች የተነሷቸው ናቸው፡፡


አባ ደመቀ ዘለቀ          አቶ ብዟየሁ ሀይሉ          አቶ ደስታ ግርማ





መሪጌታ ይልማሸዋ ከበደ　　አቶ ዘውዴ አሰፋ　　አቶ ክፍሌ ገ/አማኑኤል





ወ/ሮ ሙላቷ ማሞ　　አቶ ነገሰ አለሙ　　አቶ እሸቴ ነጋሽ

አባሪ 3

የምስል መግለጫዎች



የአቴቴ ጨሌዎች (ግንቢ፣ ዱላና ሀራ ከግራ ወደ ቀኝ)



የአውዛ መቅጃ ባለጡት ጀበና




ለመናፍስቱ የሚሰጥ ግብር (ቦረንትቻ)

❖ ከዚህ በላይ የቀረቡት ፎቶዎች በሙሉ በአጥኚዋ እና በረዳቷ አስረስ አበበ በጥናቱ ወቅት የተወሰዱ ናቸው።